# አማርኛ
# (እንደ አፍ መፍቻ)

## የተማሪ መጽሐፍ



## ስምንተኛ (፰ኛ) ክፍል

የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ትምህርት ቢሮ

# አማርኛ
## (እንደ አፍ መፍቻ)

## የተማሪ መጽሐፍ
## ስምንተኛ (፰ኛ) ክፍል


**አስማሚዎች:-**

- ቴዎድሮስ ቦጋለ (MA)
- ሀብታሙ መስፍን (M.ED)
- እስከዳር ገበያው (MA)

**አርታኢ:-**

- ፍቅርተ መኮንን (MA)

**ዲዛይንና ሌይአውት:-**

- ሲሳይ ታገሠ



2014 ዓ.ም

በአዲስ አበባ ት/ቢሮ ተዘጋጅቶ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ትምህርት ቢሮ እና በዲላ መምህራን ት/ኮሌጅ የተስማማ

የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ትምህርት ቢሮ

# © ቅጂ መብት

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በሙሉ በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ሲሆን የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስተርና የደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ እና በዲላ ትምህርት ኮሌጅ የቴክኒክ ድጋፍ በአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጀ ሲሆን አጠቃላይ የሕትመት ወጪው በደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ተሸፍኗል።

የመጽሃፉ ሕጋዊ ቅጂ ባለቤት © 2014 ዓ.ም የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስተርና የደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ናቸው።

2014 ዓ.ም
ሀዋሳ

# ማውጫ


መግቢያ ........ v

**ምዕራፍ አንድ ........ 1**

**የስራ ሥነ ምግባር ........ 1**

ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ ........ 1
ክፍል ሁለት:- መናገር ........ 3
ክፍል ሶስት:- ማንበብ ........ 3
ክፍል አራት፡- መጻፍ ........ 7
ክፍል አምስት፡- ቃላት ........ 8
ክፍል ስድስት:- ሰዋስው ........ 10
ማጠቃለያ ........ 10
የክለሳ ጥያቄዎች ........ 11

**ምዕራፍ ሁለት ........ 12**

**ባህላዊ ቅርስ ........ 12**

ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ ........ 12
ክፍል ሁለት፡- መናገር ........ 15
ክፍል ሶስት፡- ማንበብ ........ 15
ክፍል አራት፡- መጻፍ ........ 20
ክፍል አምስት፡- ቃላት ........ 21
ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው ........ 22
ማጠቃለያ ........ 23
የክለሳ ጥያቄዎች ........ 23

**ምዕራፍ ሶስት ........ 24**

**ሰብዓዊ እሴቶች ........ 24**

ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ ........ 24
ክፍል ሁለት፡- መናገር ........ 25
ክፍል ሶስት፡- ማንበብ ........ 27
ክፍል አራት፡- መጻፍ ........ 32
ክፍል አምስት፡- ሰዋስው ........ 34
ማጠቃለያ ........ 36
የክለሳ ጥያቄዎች ........ 36

**ምዕራፍ አራት ........ 37**

**አጭር ልቦለድ ........ 37**

ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ ........ 37
ክፍል ሁለት፡- መናገር ........ 38
ክፍል ሶስት፡- ማንበብ ........ 40

ክፍል አራት፡- መጻፍ ....45
ክፍል አምስት፡- ቃላት ....46
ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው ....47
ማጠቃለያ ....49
የክለሳ ጥያቄዎች ....50

**ምዕራፍ አምስት ....51**
**ሥነ ህዝብ ....51**
ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ ....51
ክፍል ሁለት፡- መናገር ....53
ክፍል ሶስት፡- ማንበብ ....54
ክፍል አራት፡- መጻፍ ....58
ክፍል አምስት፡- ቃላት ....58
ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው ....59
ማጠቃለያ ....61
የክለሳ ጥያቄዎች ....61

**ምዕራፍ ስድስት ....62**
**በረሃማነት ....62**
ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ ....62
ክፍል ሁለት፡- መናገር ....64
ክፍል ሶስት ፡- ማንበብ ....65
ክፍል አራት፡- መጻፍ ....68
ክፍል አምስት፡- ቃላት ....70
ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው ....71
ማጠቃለያ ....72
የክለሳ ጥያቄዎች ....72

**ምዕራፍ ሰባት ....73**
**የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ....73**
ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ ....73
ክፍል ሁለት፡- መናገር ....75
ክፍል ሶስት፡- ማንበብ ....75
ክፍል አራት፡- መጻፍ ....80
ክፍል አምስት፡-ቃላት ....81
ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው ....83
ማጠቃለያ ....84
የክለሳ ጥያቄዎች ....84

**ምዕራፍ ስምንት ....................................................86**
**ሰላም.......................................................................86**
ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ ........................................86
ክፍል ሁለት፡- መናገር.........................................88
ክፍል ሶስት፡- ማንበብ.........................................89
ክፍል አራት፡- መጻፍ ..........................................94
ክፍል አምስት፡- ቃላት.........................................96
ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው ......................................97
ማጠቃለያ.........................................................99
የክለሳ ጥያቄዎች.................................................99

**ምዕራፍ ዘጠኝ..................................................100**
**አየር ንብረት ..............................................................100**
ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ ........................................100
ክፍል ሁለት፡- መናገር.........................................101
ክፍል ሶስት፡- ማንበብ.........................................103
ክፍል አራት፡- መጻፍ ..........................................109
ክፍል አምስት፡- ቃላት.........................................110
ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው ......................................112
ማጠቃለያ.........................................................113
የክለሳ ጥያቄዎች.................................................113

**ምዕራፍ አስር..................................................114**
**ተውኔት.......................................................................114**
ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ ........................................114
ክፍል ሁለት፡- መናገር.........................................116
ክፍል ሶስት፡- ማንበብ.........................................118
ክፍል አራት፡- መጻፍ ..........................................125
ክፍል አምስት፡- ቃላት.........................................125
ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው ......................................126
ማጠቃለያ.........................................................127
የክለሳ ጥያቄዎች.................................................128
**የቃላት ፍቺ ..............................................................129**
**ዋቢጽሑፎች ..............................................................131**
**የአማርኛ የፊደል ገበታ ...................................................132**
**የኢትዮጵያ ቁጥሮች .......................................................134**

# መግቢያ

ይህ መጽሐፍ አማርኛን በመጀመሪያ ቋንቋነት የሚማሩ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በቋንቋዉ በብቃት ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ እንዲችሉ፤ የቃላትና የሰዋስው ዕውቀት እንዲያገኙ ለማድረግ የተዘጋጀ የሥርዓተ ትምህርት አካል ነው:: ከዚህ በተጨማሪ ምመጽሐፉ ለዚህ የክፍል ደረጃ ሥርዓተ ትምህርትና ለሚሰጠው የትምህርት ሽፋን መረጃ ይሰጣል:: ከዚህም በላይ ተማሪዎችና ወላጆች በትምህርት ቤት የተከናወኑ ተግባራትን ለማስቀጠልና ይበልጥ ለማዳበር በጋራ እንዲሰሩ ያስችላቸዋል::

## መሰረታዊ መርሆዎች

- ተማሪዎች በማህበረሰብ ሕይወት ውስጥ አስፈላጊ ስለሆኑ የማዳመጥ ይዘቶችና ርዕሰ ጉዳዮች ይማራሉ::
- ለነዚህ የማዳመጥ ይዘቶችና ርዕሰ ጉዳዮች የተጻፉ ምንባቦችን ካዳመጡ በኋላ፣ በእነሱ ላይ በመመስረት ይናገራሉ::
- በቀጣይም በማሕበረሰቡ ውስጥ አስፈላጊ ስለሆኑ የምንባብ ይዘቶችና ርዕሰ ጉዳዮች የሚማሩ ሲሆን የተጻፉ ምንባቦችን ካነበቡ በኋላ፣ በዕነሱ ላይ በመመስረት ጽሁፍ ይጽፋሉ::
- አራቱን ክሂሎች ከላይ በተቀመጠው መሰረት ከተማሩ በኋላ በክፍል አምስትና ስድስት የቀረቡትን የቃላትና የሰዋስው ትምህርቶችን በየምዕራፉ በተገለጸው ዓላማ መሰረት ይማራሉ::
- ተማሪዎች በግላቸው ብቻ ሳይሆን አብረዋቸው ከሚማሩ ጓደኞቻቸው ውቀትን ይቀስማሉ::

## በቤት ውስጥ ከቤተሰብ ጋር መማር

ተማሪዎች በትምህርት ቤት የሚቀስሟቸውና በቤታቸው ከወላጆቻቸውጋር የሚሠሯቸው በርካታ ትምህርታዊ ተግባራት አሉ:: ከእነዚህ በርካታ ተግባራት ቢያንስ የተወሰኑትን ከልጆቻቸው ጋር በጋራ እንዲሠሩ ይጠበቃል::

፩. የየእለቱን ትምህርት ይዘት በተመለከተ ከቴሌቪዥን፣ ከሬዲዮ ወይም ከድረ ገጽ ስለርዕሰ ጉዳዩ አዳምጡ ወይም ተመልከቱ::

፪. ልጆች የተሰጣቸውን የቤት ሥራ ሲሠሩ፣ ራስን ወይም ሌሎች የቤተሰብ አባላትን በቃለመጠይቅ፣ ንግግርን በመጻፍ ወይም በንግግር ልምምድ ወቅት በመሳተፍ አብሮ መሥራት ተገቢነው።

፫. ወላጆች የሳምንቱን ወይም የዕለቱን የምንባብ ይዘት ወይምርዕሰ ጉዳይ ልጆቻችሁን በመጠየቅ ተረዱ። በትምህርት ቤት ያነበቧቸውን ምንባቦች በጋራ አንብቡ። ይህንንም ልጆች ወይም ወላጆች ለብቻ ወይም በየተራ በማንበብ ሊተገብሩት ይችላሉ፤

፬. ልጆቻችሁን የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ስለ ምንባቡ ተወያዩ፤

፭. ስለ ርዕሰ ጉዳዩ የሚያወሱ ሌሎች ጽሁፎችን ከመጻሕፍት፣ ከጋዜጦች ወይም ከመጽሔቶች ፈልጋችሁ አንብቡ።

፮. በግል ያንብቡ (ልጆች ራሳቸውን ችለው በግላቸው እንዲያነቡ አበረታቱ)፤ ከዚያም ስላነበቡት ጉዳይ ተወያዩ።

፯. ልጆች በክፍል ውስጥ ምን ምን እንደተማሩ ደብተራቸውን በጋራ ተመልከቱ፤ ስለ ምን እንደተማሩና ምን እንደተሰማቸው የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች በማንሳት ተወያዩ።

፰. የመጻፍ ችሎታቸውን ለማዳበር የተማሯቸውን ዝርዝር ክሂሎች በመረዳት ምን እንደተማሩ ለማወቅ የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ልጆቹን ጠይቋቸው። ለምሳሌ:- የቃላቱ ፊደላት በተገቢ ሁኔታ ተጽፈዋል/ ተሰድረዋል ወይ? በአረፍተ ነገሮች ውስጥ /መካከል/ ያሉትሥርዓተ ነጥቦች (አራትነጥብ፣ ነጠላሰረዝ፣ ድርብ ሰረዝና የመሳሰሉት) በተገቢ ቦታቸው ገብተዋል ወይ? ወዘተ…

፱. ልጆች አጫጭር ደብዳቤዎች (ለምሳሌ:- ለቤተሰብ አባላት ወይም ለጓደኞች) እንዲጽፉ ወይም በዕለቱ ወይም በሳምንቱ ስለተከሰቱ ጉዳዮች ወይም ስለአንድ ጉዳይ ያላቸውን አስተያየት ወዘተ. እንዲጽፉ አበረታቷቸው።

# ምዕራፍ አንድ

# የስራ ሥነ ምግባር

## የሚጠበቁ ውጤቶች፣

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ፡-

- በጥሞና አዳምጣችሁ በተነገረበት ዐውድ መሰረት ትመልሳላችሁ፤
- የስራ ሥነ ምግባር ጽንሰ ሃሳብ ትገልፃላችሁ፤
- አዳዲስ ሀሳቦችን አካታችሁ ጽሑፍ ትጽፋላችሁ፤
- ቃላትን በተለያየ አውድ ውስጥ በአረፍተ ነገር ታሳያላችሁ፤
- የቋንቋውን ትክክለኛ የሰዋስው አወቃቀር ትጠቀማላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### ሰው ለስራ

### ቅድመ ማዳመጥ

**ተግባር**


ሀ. ስራ ለሰው በሚል ርዕስ ስር ምን ምን ጉዳዮች የሚነሱ ይመስላችኋል?


ለ. የስራ ስነ ምግባራትን ዘርዝሩ፡፡

ሐ. ከዚህ በታች ያለውን ስዕል በማየት የተረዳችሁትን ሀሳብ ግለፁ፡፡









## ጊዜ ማዳመጥ

### ተግባር

ሰው ለስራ በሚል ርእስ የቀረበውን የማዳመጥ ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን በማስታወሻ ደብተራችሁ በመጻፍና በንቃት በማዳመጥ መምህራችሁ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ስጡ።

## ድህረ ማዳመጥ

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት በቃላችሁ መልሱ።

፩. ንፁህ አዕምሮ ያለው ሰው ዛሬ ላይ የሰራውን ስህተት ነገ ላይ አይደግመውም ማለት ምን ማለት ነው?

፪ “ሰው የተፈጠረው በስራና ለስራ ነው” የሚለውን አባባል አብራርታችሁ ተናገሩ።

፫. አንድ ሰው ስራው ስኬታማ እንዲሆን ምን አይነት የግል ምርጫዎችና ውሳኔዎች ሊኖሩት ይገባል?

፬. ስራን በዕውቀት ላይ ተመስርቶ መስራትና ስራን መውደድ ምን ምን ጠቀሜታዎች እንዳሏቸው ዘርዝሩ፡፡
፭. ስራ መስራት እንዴት ራስን፣ ቤተሰብን፣ ሀገርንና ዓለምን እንደሚቀይር አብራሩ?

## ክፍል ሁለት:- መናገር

ተግባር

ከዚህ በታች በቀረቡላችሁ ጥያቄዎች ላይ በቡድን ተወያይታችሁ በተወካያችሁ አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ፡፡

፩. ተማሪዎች! ስታድጉ በምን አይነት የሙያ መስክ መሰማራት ትፈልጋላችሁ? ለምን?
፪. የመረጣችሁት ሙያ ምን አይነት የስራ ስነምግባር የሚጠይቅ ይመስላችኋል? እንዴትና በምን አይነት ሁኔታስ ልትወጡት አሰባችሁ?
፫. ጠንካራ የስራ ባህል ምን ምን ጉዳዮችን የሚያካትት ይመስላችኋል?

## ክፍል ሶስት:- ማንበብ

### የአውራምባ ማኅበረሰብና መገለጫው







## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

**ተግባር**

፩. ጠንካራ የስራ ስነምግባር መገለጫዎች ምን ምን ይመስሏችኋል?

፪. ስዕሉን በመመልከት የአውራምባ ማህበረሰብ ምን አይነት የስራ ባህል ያለው ይመስላችኋል?

## የአውራምባ ማኅበረሰብና መገለጫው

በኢትዮጵያ የእኩልነት፣ የመከባበር፣ የመደማመጥና የመቻቻል ተምሳሌት የሆነው የአውራምባ ማህበረሰብ በዙምራ ኑሩ አማካኝነት በ1964 ዓ.ም የተመሰረተ ሲሆን በሥራና ሰርቶ በማደግ ብቻ የሚያምንና ለዘላቂ ሕይወቱ መለወጥም ጠንክሮ የሚሰራ ነው፡፡ አቶ ዙምራ ከፆታ ክፍፍል የፀዳና ጠንካራ የስራ ስነ ምግባር ያለው ማህበረሰብ ለመፍጠር የነበራቸውን ምኞት እውን ለማድረግና አዲሱን አስተሳሰባቸውን የሚጋራ ሰው ለማግኘት ምቆላ መውረድ፣ ደጋ መውጣት፣ እንዲያም ሲል ከማህበረሰቡ ጋር መጋጨትና መገለል ግድ በመሆኑ በቤተሰቦቻቸውና በአካባቢው ነዋሪ ህብረተሰብ ሳይቀር እንደአፈንጋጭ ወይም እንደ እብድ ይቆጠሩ ነበር፡፡ ድካምና ልፋቱ ሳይበግራቸው ገና በጨቅላነት ዕድሜያቸው ወሎን፣ ጐንደርንና ጐጃምን በማካለል ሀሳባቸውን የሚቀበል ሰው ፍለጋ ሌት ተቀን ባትለዋል፡፡

**ተማሪዎች! እስካሁን ካነበባችሁት ሀሳብ በመነሳት**

**አቶ ዙምራየገጠማቸውንውጣውረድስትመለከቱምንተሰማችሁ?**

**በቀሪው የጽሁፍ ክፍልስ የአቶ ዙምራ አስተሳሰብ እውን የሚሆን ይመስላችኋል?**

ለአሥራ ሰባት ዓመታት መውጣት መውረዱ ቀጥሎ የኋላ ኋላ ልፋትና ድካማቸው መና ባለመቅረቱ ፎገራ ወረዳ ውስጥ ጥቂት ተከታዮችን ከጐናቸው ማሰለፍ ቻሉ:: እና ምዙምራ የተመኙትና የናፈቁትን ብሎም በልጅነት እድሜያቸው ብዙ የደከሙለትና እጅግ ከፍተኛ የሆነ መስዋዕትነትም የከፈሉለት አስተሣሰብና የሚከተሉት ፍልስፍና ተቀባይነት በማግኘቱ መተሳሰሪያውን ፍቅር ህይወቱን ሥራ ያደረገ ማህበረሰብ በይፋ ተመሠረተ::

የአውራምባ ማህበረሰብ አባላት የስራ ባህል ከሌላው ሕብረተሰብ በብዙ መልኩ እንዲለዩ ያደርጋቸዋል:: ማህበረሰቡ በአስተሣሰብና በእምነት ፍጹም ለየት ያለ በመሆኑ እምነቱን ፍቅር፣ ሐይማኖቱን ደግሞ ሥራ ያደረገ እስኪመስል ድረስ የሚንቀሳቀስ መሆኑ ብቻ ሣይሆን ይህ ሥራ የሴት ይህ ኛው ደግሞ የወንድ የሚባል የሥራ ክፍፍልንም ሆነ ልዩነትን አይቀበልም:: ሴቶች በሬዎችን ጠምደው ያርሣሉ፤ ሽማይሠራሉ፤ በአጠቃላይም በተለምዶ የወንድ ሥራ ተብሎ በሚታወቀው ማንኛውም ዓይነት እንቅስቃሴ ውስጥ ሁሉ በእኩልነት ይሣተፋሉ:: ወንዶች ደግሞ እንጀራ ይጋግራሉ፤ ወጥ ይሠራሉ፤ ጥጥ ይፈትላሉ ወዘተ. ብቻ ስራን ሳይንቁና ወደሌላ ሳይገፉ በኩራት ይሰሩታል እንጅ ይኸ የሴት ስራ ነው በማለት ሀፍረት ብሎ ነገር አይስተዋልባቸውም::

ስለሆነም አውራምባዎች ሥራ ያሉትንና ለህይወታቸው ጠቃሚ ነው ብለው የሚያምኑበትን ሁሉ ተግባብተው ይሠሩታል፤ ሁሉም የማህበረሰቡ አባላት ከድህነትና ኋላ ቀርነት መላቀቅ የሚቻለው በሥራና በስራ ብቻ እንጅ ቁጭ ብሎ ከሰማይ መና እንዲወርድለት በመጸለይ እንዳልሆነ በጽናት ያምናሉ:: እናም ኑሮአቸውን ለማሻሻል ሌት ተቀን ተግተው ይሠራሉ፤ ለለውጥና ለሥራ ማነቆ የሆኑ ኋላ ቀር አስተሣሰቦችን በጽናት ይታገሏቸዋል እንጅ ጊዜ ሰጥተው በጭራሽ ለማስታመም አይሞክሩም ብቻ ሳይሆን ለማደናቅፍ ለሚሞክሩ ስራ ፈቶች ጊዜና ቦታ መድበው ሀሳባቸውን እንዲያደናቅፉባቸው ዕድል አይሰጧቸውም::

በእርግጥም የአውራምባ ማህበረሰብ መተሳሰሪያ ገመዱን ፍቅር የለውጥ መሳሪያውን ደግሞ ሥራ እንዲሁም እምነቱንም በፈጣሪ አድርጐ ከአራት አሥርት ዓመታት በላይ በጽናት ዘልቋል:: መላ የማህበረሰቡ አባላትም እርስ በርስ ከመዋደድና ከመከባበር አልፈው ድህነትን በሥራና በሥራ ብቻ በማሸነፍ ኑሯቸውን ለመለወጥ ሌት ተቀን ተግተው መንቀሳቀስን የሕይወታቸው አካል አድርገውታል:: ሥራን ይወዳሉ ወይም ያፈቅራሉ ማለት ብቻ የአውራምባዎችን ጠንካራ የስራ ባህል ለመግለጽ በቂ ቃል ሊሆን አይችልም፤ ምክንያቱም ያመልኩታልና:: ይህም ሆኖ ሲሠሩ ያያቸው የአገሬው ሰው በመደመምና በመደነቅ ጭምር ለምን ይህን ያህል

ሥራን እንደሚያፈቅሩና እስከማምለክም ድረስ መዝለቃቸውን ሲጠይቃቸው ምኑን ሠራነው! ገና ምኑስ ተያዘና ድህነት ከላያችን ላይ ሙሉ ለሙሉ እስከሚወገድ ድረስ ሁልጊዜም ቢሆ ንጠንክረን እንሰራለን የሚል እፁብ ድንቅ የሚያሰኝ መልስ ይሰጡታል፡፡

(በሲሳይ መንግስቴ፣ 2006 ዓ.ም ለባህልና ቱሪዝም ኢንስቲቲዩት የፓናል ውይይት የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፣ መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ)

## ድህረ ንባብ

### መልመጃ አንድ

ምንባቡን መሰረት በማድረግ የሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ "እውነት"፣ ስህተት ከሆኑ ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡

፩. ዙምራ ኑሩ የተመኙትን ማኅበረሰብ መፍጠር ችለዋል፡፡

፪. የአውራምባ ማህበረሰብ የስራ ባህል፣ የአኗኗር ዘይቤና የሚከተሉት ፍልስፍና ከሌላው ህብረተሰብ የተለየ አይደለም፡፡

፫. የአውራምባ ማህበረሰብ አስተሳሰብ ከኢትዮጵያ አልፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነትን አግኝቷል፡፡

፬. ዙምራ በቤተሰቦቻቸውም ሆነ በአካባቢው ነዋሪ ህብረተሰብ ዘንድ እንደ አፈንጋጭ ወይም እንደ እብድ ይቆጠሩ ነበር፡፡

፭. ምንባቡ በሶስት አንቀፆች የተደራጀ ነው፡፡

### መልመጃ ሁለት

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሰረት ተስማሚውን መልስ ምረጡ፡፡

፩. በ1964 ዓ.ም በተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ዘንድ ተቀባይነትን በማግኘቱ መተሳሰሪያውን ፍቅር፣ ሕይወቱንም ስራ በማድረግ የተመሰረተው ማህበረሰብ የቱ ነው?

ሀ. የአዊ ማህበረሰብ
ሐ. አንፌሎ ማህበረሰብ
ለ. የአውራምባ ማህበረሰብ
መ. የሳሆ ማህበረሰብ

፪. የምንባቡ አጠቃላይ ሀሳብ ምንድን ነው?

ሀ. የአቶ ዙምራን የህይወት ታሪክ መተረክ

ለ. የአውራምባ ማህበረሰብን ፆታዊ አድልዎ ማመልከት

ሐ. የአውራምባ ማህበረሰብን የስራ ባህል ማስቀኘት

መ. ሁሉም

፫. ከሚከተሉት አንዱ የአውራምባ ማህበረሰብ ወንዶች የሚሰሩት ስራ አይደለም።

ሀ. የእንጀራ መጋገር

ለ. ወጥ መስራት

ሐ. ጥጥ መፍተል

መ. መልስ የለም

፬. በምንባቡ ውስጥ የተገለፀው ማህበረሰብ መተሳሰሪያ ገመዱ ፍቅር መሆኑን የሚያስገነዝበው ስንተኛው አንቀጽ ነው

ሀ. አምስተኛው

ለ. ሁለተኛው

ሐ. ሶስተኛው

መ. አራተኛው

፭. የአውራምባ ማህበረሰብ አባላት ከድህነትና ከኋላቀርነት መላቀቅ የሚቻለው በምንድን ነው ብለው ያምናሉ?

ሀ. በስራ

ለ. በመለመን

ሐ. በእምነት

መ. በመፀለይ

፮. አውራምባዎች ሁልጊዜ ጠንክረው በመስራት ከላያቸው ላይ ሙሉ ለሙሉ ለማስወገድ የሚመኙት የስልጣኔያቸው ተግዳሮት ምንድን ነው?

ሀ. ሀሜት

ለ. ደካማ የስራ ባህል

ሐ. ድህነት

መ. ኋላቀርነት

## ክፍል አራት፦ መጻፍ

### መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች ቅደም ተከተል በማስተካከል አንቀጽ ፃፉ።

ሀ. ሰዎች አቅደውም ይሁን ሳያቅዱ ከስራ ተለይተው አያውቁም።

ለ. “ይህን አቀብይኝ፣ ያንን ዝጋው፣ ውሃ ስጠኝ ወዘተ.” ሲባል ስራ ተጀምሯል ማለት ነው፡፡

ሐ. ስራ ከዕለት ተዕለት ህይወት ጋር የተቆራኘ ነው፡፡

መ. ሰዎች ስራ የሚጀምሩት ምንነቱን ሳይረዱት ገና በህፃንነት ዕድሜያቸው ነው፡

ሠ. በዕለት ከዕለት የሚያከናውኗቸው እንደ መመገብ፣ መራመድ፣ የግልና የአካባቢ ንጽህና መጠበቅ የመሳሰሉት ተግባራት ህይወት በስራ የተጠመደች መሆኗን ያመለክታሉ፡፡

## መልመጃ ሁለት

ከዚህ በታች የቀረበውን ጅምር አንቀጽ ሀሳብ ተረድታችሁ በራሳችሁ አገላለጽ ጨርሳችሁ ፃፉት፡፡

ዕለቱ ሰኞ ጠዋት ነው፡፡ ከምንኖርበት ገጠራማ ክፍል ከተማ ለገበያ ተልኬ በሄድኩበት ነው ወሬውን የሰማሁት፡፡ የታዘዝኩትን ገዝቼ ከጨረስኩ በኋላ ወደቤቴ ገሰገስኩ፡፡ አስናቀችን ከሩቅ አየኋት፡፡ ምንም እንኳ ወላጆቿ በዝቅተኛ ኑሮ ውስጥ ሆነው የፈለገችውን ባያሟሉላትም አስራ ሁለት አመት አብረን ስንማር አንድም ቀን አንደኛ ደረጃዋን ለቃ አታቅም፡፡ ጠርቼ በእጄ ምልክት ሰጠኋት፡፡ እየሮጠች መጣችና ሰላምታ ሰጠችኝ፡፡ በናፍቆት ስንጠብቅ የነበረው ውጤት መውጣቱን አበሰርኳት፡፡ የመደንገጥ ስሜት ፊቷ ላይ ይታይ ነበር፡፡ ተያይዘን ሩጫችንን ወደ ትምህርት ቤት ቀጠልን...

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### ማታወሻ

#### የቃላት አውዳዊ ፍቺ

አንድ ቃል በተለያዩ አውዶች ውስጥ ሲገኝ የሚኖረው ፍቺ እንደየአገባቡ ይለያያል፡፡ የአንድ ቃል ትክክለኛ ፍቺ የሚታወቀው በአረፍተ ነገር ውስጥ ገብቶ ከሌሎች ቃላት ጋር በመሆን መልዕክት ሲያስተላልፍ ነው፡፡

ለምሳሌ፡- “**አገልግል**” የሚለውን ቃል ወስደን በተለያዩ አረፍተ ነገሮች ውስጥ ያለውን ዐውዳዊ ፍቺ እንመልከት፡-

እናቴ ከአርባ ምንጭ <u>አገልግል</u> ላከችልኝ፡፡
ፍቺ፡- ምግብ መያዣ
ወታደሩ ሀገርህን <u>አገልግል</u> ተባለ፡፡
ፍቺ፡- እርዳ፣ አግዝ
ከላይ ማየት እንደሚቻለው "አገልግል" የሚለው ቃል በሁለቱ አረፍተ ነገሮች ውስጥ የተለያዩ ፍቺዎችን ይዟል፡፡

## መልመጃ አንድ

ከዚህ ቀጥሎ ከምንባቡ የወጡ ቃላት ቀርበውላችኋል፡፡ በአረፍተ ነገር ውስጥ በማስገባት አውዳዊ ፍቻቸውን አመልክቱ::

ሀ. ባተሌ
ለ. ማነቆ
ሐ. መጎናፀፍ
መ. መና
ሠ. ማሰላሰል
ረ. እውን

## መልመጃ ሁለት

ክፍል ሶስት በቀረበው ምንባብ መሰረት በ "ሀ" አምድ ለተሰጡት ቃላት ተመሳሳያቸውን በ"ለ" አምድ ካሉት በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| ፩. መባከን | ሀ. መሰናክል |
| ፪. እፁብ ድንቅ | ለ. ወጣት |
| ፫. መደመም | ሐ. መልፋት |
| ፬. ማጋበስ | መ. መሰብሰብ |
| ፭. ጉብዝና | ሠ. ወጣ ያለ |
| ፮. አረጋዊ | ረ. መደነቅ |
| ፯. አፈንጋጭ | ሰ. አስገራሚ |
| ፰. እንቅፋት | ሸ. ወጣትነት |
| | ቀ. የእድሜ ባለፀጋ |

## ክፍል ስድስት:- ሰዋስው

### ማስታወሻ

#### የቋንቋ መዋቅር

የቋንቋ መዋቅር፡- ድምጽ ከድምጽ ጋር ተቀናጅቶ ቃልን፣ ቃል ከቃል ጋር ተገጣጥሞ ሐረግን፣ ሀረግ ከሀረግ ጋር ተዋቅሮ አረፍተ ነገርን፣ አረፍተ ነገር ከአረፍተ ነገር ጋር ተቀናጅቶ አንቀጽን፣ አንቀፆች ደግሞ በጋራ ስርዓት ባለው መንገድ ተቀናጅተው ድርሰት ደረጃ በደረጃ የሚፈጥሩበትን ስርዓት የሚያመለክት ጥበብ ነው። የማንኛውም ቋንቋ መዋቅር መሰረቱ ደግሞ ድምጽ ነው።

አንድ የቋንቋ መዋቅር እርስ በርሱም ሆነ ከሌላ የቋንቋ መዋቅር ጋር ተቀናጅቶ አዲስ መዋቅር ሲፈጥር ስርዓት ባለው መልኩ መሆን ይኖርበታል እንጂ የተደረደሩ ድምፆች ሁሉ ቃላትን፣ ቃላትም ሀረጋትን ወዘተ ይፈጥራሉ ማለት አይደለም።

ለምሳሌ፡- /ብ-ኤ-ት/ የሚሉት ድምፆች በስርዓት ስለተቀናጁ "ቤት" የሚል ትርጉም አዘል ቃል ሰጥተውናል። ነገር ግን /ት-ብ-ኤ/ አይነት የድምፆች ቅደም ተከተል ቢኖር ምንም እንኳ ፊደሎቹ ተመሳሳይ ቢሆኑም "ትቤ" የሚል በአማርኛ ቋንቋ አጠቃቀም ትርጉም አልባ የድምጾች ቅንጅት ነው የምናገኘው። ሌሎች መዋቅሮችም እንዲሁ ስርዓታዊ ቅንጅታቸውን ካልጠበቁ የትርጉም ልዩነት ያመጣሉ ወይም ደግሞ ትርጉም አልባ ይሆናሉ።

#### ተግባር

የቋንቋውን ተገቢ መዋቅር ጠብቃችሁ "የመምህርነትን የስራ ሥነምግባር" በተመለከተ አጭር ድርሰት ፃፉ።

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ አውዳዊ ፍቺ ማለት ቃላት በተለያዩ ዓ.ነገሮች ውስጥ ሲገቡ የሚያስገኙት ፍቺ እንደሆነና የቃላት ትክክለኛ ትርጓሜ የሚታወቀው በዓ.ነገር ውስጥ ገብተው አውድን መሰረት አድርገን ስንፈታቸው እንደሆነ ተመልክተናል።

በመጨረሻም የቋንቋ መዋቅር መሰረቱ ድምጽ እንደሆነና ድምፆች ተቀናጅተው ቃላትን፣ ቃላት ተቀናጅተው ሀረግን፣ ሀረጋትም ተቀናጅተው ዓ.ነገርን ወዘተ እንደሚያስገኙ እና ሲቀናጁ ግን የቋንቋን ስርዓት መሰረት ባደረገ መልኩ መሆን እንደሚኖርበት ለመረዳት ችለናል።

# የክለሳ ጥያቄዎች

## መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ቃላት በተስማሚው አረፍተ ነገር ውስጥ በማስገባት አረፍተ ነገሩን የተሟላ አድርጉ።

| | | |
|---|---|---|
| የስራ እድል | የስራ ባህል | ስራ |
| ፍቅር | ለማስተንጎል | ድህነት |

1. ከ _____________ መውጫ መንገዱ ስራና ስራ ብቻ ነው።
2. ሰዎች የራሳቸውን ኑሮ እንዲያሻሽሉ ከተፈለገ _____________ መፈጠር ይኖርበታል።
3. ዓላማችንን _____________ጥረት ለሚያደርጉ ሰዎች ጆሮ መስጠት ተገቢ አይደለም።
4. ለሁሉም ነገር መሰሪያ ገመዱ _____________ነው።
5. ጠንካራ _____________ ያለው ማህበረሰብ ምንጊዜም ቢሆን ለድህነት እጅ አይሰጥም።
6. የአውራምባ ማህበረሰብ _____________ ይወዳሉ ብቻ ሳይሆን ያመልኩታል ቢባል ማጋነን አይሆንም።

# ምዕራፍ ሁለት

## ባህላዊ ቅርስ

### የሚጠበቁ ውጤቶች፣

ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፣ ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ፡-

- የሌሎችን ሀሳብ በጥሞና ታዳምጣላችሁ፤
- የባህላዊ ቅርስን ምንነት ታብራራላችሁ፤
- አዳዲስ ቃላትን በተለያየ አገባብ ውስጥ ትጠቀማላችሁ፤

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### ቅርሶች በኢትዮጵያ









## ቅድመ ማዳመጥ

### ተግባር

ሀ. በሀገራችን ከሚገኙ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ቅርሶች ውስጥ የምታውቋቸውን ተናገሩ።

ለ. ከዘረዘራችኋቸው ቅርሶች ውስጥ በተባበሩት መንግስታት የባህል፣ የትምህርትና የሳይንስ ማዕከል የተመዘገቡት የትኞቹ ይመስሏችኋል?

## ድህረ ማዳመጥ

### መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክል ከሆኑ "እውነት"፣ ስህተት ከሆኑ ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልሱ።

፩. የጦርነት ጊዜ ሽለላዎች በቅርስነት ለመመዝገብ የሚያስችላቸውን መስፈርት ሊያሟሉ አይችሉም።

፪. ቅርሶች ከምንጭ አንፃር ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ።

፫. የጢያ ትክል ድንጋይ በዩኔስኮ ከተመዘገቡ ቅርሶች መካከል አንዱ ነው።

፬. የቀድሞ አባቶቻችንና እናቶቻችን ሰርተው እና ተጠቅመውበት ያለፉት ሀብት ቅርስ ሊሆን አይችልም።

፭. በዩኔስኮ ከተመዘገቡ የስነጽሁፍ ቅርሶች መካከል ስምንቱ የብራና ላይ ጽሁፎች ናቸው።

### መልመጃ ሁለት

የሚከተሉትን ጥያቄዎች የተነበበላችሁን የማዳመጥ ምንባብ መሰረት በማድረግ ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ።

፩. ______________ የህዝቦች ማንነት የሚገለጽበትና የረጅም ዘመን ባህላቸውንና ታሪካቸውን እንዲገነዘቡ የሚረዳ ቁሳዊና መንፈሳዊ ሀብት ነው፡፡

ሀ. ውርስ ሐ. ቅርስ

ለ. ስጦታ መ ኑዛዜ

፪. የተባበሩት መንግስታት የሳይንስና የባህል ማዕከል በዓለም ቅርስነት ከመዘገባቸው ቅርሶች መካከል ከፍተኛውን ቁጥር የያዘችው አፍሪካዊት ሀገር ማን ናት?

ሀ. ሱዳን ሐ. ኡጋንዳ

ለ. ኢትዮጵያ መ. ታንዛንያ

፫. ከሚከተሉት ውስጥ የማይዳሰስ ባህላዊ ቅርስ ተብሎ በዩኔስኮ የተመዘገበው የትኛው ነው?

ሀ. መስቀል ሐ. ፊቼ ጨምበላላ

ለ. የገዳ ስርዓት መ. ሁሉም

፬. ከኢትዮጵያ በዩኔስኮ የተመዘገቡ እና በብራና ላይ የተፃፉ የስነ ጽሁፍ ቅርሶች ስንት ናቸው?

ሀ. ስምንት ሐ. ሰባት

ለ. ዘጠኝ መ. አስራሁለት

፭. በዩኔስኮ የቅርስ መዝገብ የሚዳሰሱ ቅርሶች ተብለው ከተመዘገቡ የኢትዮጵያ ቅርሶች ውስጥ የማይካተተው የትኛው ነው?

ሀ. አክሱም

ለ. ላሊበላ

ሐ. የጀጎል ግንብ

መ. መልስ አልተሰጠም

፮. ከሚከተሉት አንዱ በዩኔስኮ ከተመዘገቡ የሥነጽሑፍ ቅርሶች ውስጥ አይመደብም፡፡

ሀ. አፄ ቴዎድሮስ ለእንግሊዟ ንግስት የፃፉት ደብዳቤ

ለ. ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ለአሜሪካው ፕሬዝደንት የፃፉት ደብዳቤ

ሐ. ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ለሞስኮው ንጉስ የፃፉት ደብዳቤ

መ. ንጉስ ሳህለሥላሴ ለእንግሊዟ ንግስት የፃፉት ደብዳቤ

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ተግባር

ከዚህ በታች በቀረቡላችሁ ጥያቄዎች ላይ በቡድን ተወያይታችሁ በተወካያችሁ አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ፡፡

፩. ተማሪዎች! ባህላዊ ቅርስ ማለት ምን ማለት ነው?

፪. በባህላዊ ቅርስ ውስጥ የሚካተቱት ሀገር በቀል ቅርሶች ምን ምን ይመስሏችኋል?

፫. ቅርስን የመጠበቅ ሀላፊነት ያለበት ማን ይመስላችኋል? ለምን?

፬. በኢትዮጵያ ቅርስን ባህላዊና ዘመናዊ ብሎ የመመደብ ስልጣን ያለው አካል ማን ነው?

- ባህላዊና ዘመናዊ ብሎ ለመፈረጅስ መስፈርቱ ምን ይመስላችኋል? (በአካባቢያችሁ ካለ የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት በመጠየቅ መልሱን ለክፍል ጓደኞቻችሁ የአመዘጋገብ ሂደቱን ቅደም ተከተል በሚያሳይ መልኩ በቃል አቅርቡ)፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ማንበብ

### ቡሄና ቃላዊ ግጥሞቹ



## ቅድመ ንባብ

### ተግባር

፩. በቡሄ በዓል ግንባር ቀደም ተዋናዮች እነማን ይመስሏችኋል?

፪. በቡሄበዓል የሚደረደሩ ቃላዊ ግጥሞችን እያነሳችሁ ተወያዩ።

፫. በድሮ ጊዜ እና አሁን በሚደረደሩ የቡሄ ቃላዊ ግጥሞች ላይ ልዩነት የሚኖር ይመስላችኋል? ለምን? በማስረጃ ለማሳየት ሞክሩ።

# ቡሄና ቃላዊ ግጥሞቹ

ቡሄ ከባዱ የክረምት ወራት ዝናቡ፣ ብርዱና ደመናው ተወግዶ የብርሃን ወገግታ ሲታይ የሚከበር በዓል ነው። ሰማይ ከጭጋጋማነት ተላቆ ወደ ብሩህነት ይሸጋገራልና ሳይጠያየቅ የቆየው ዘመድ አዝማድ ወደ ነበረው ማህበራዊ ህይወቱ የሚመለስበት ጊዜም ነው። በዚህም ሆያ ሆዬ…ሆ… በማለት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክታቸውን የሚያስተላልፉ ልጆች ከቤተሰቦቻቸው ፈቃድ አግኝተው በየቤቱ እየተዘዋወሩ ይጨፍራሉ። በዓሉ በየዓመቱ ነሐሴ 13 ቀን ጅራፍ በማጮህ፤ ችቦ በማብራት፤ ሙልሙል ዳቦ በማዘጋጀትና በልጆች ጭፈራ ይከበራል። የቡሄ በዓል ከሌሎች በዓላት በፊት የሚከበርና የሌሎች በዓላት መነሻ በመሆንም ያገለግላል። ቀዳሚና የበዓላት መነሻ መሆኑም በስነቃል አማካኝነት እንዲህ ይገለፃል።

የበዓል መነሻ ቡሄ ነውና
በጋራ እናክብረው ሰብሰብበሉና።

በዓሉ በተለያዩ ክልሎች በተለያየ ስያሜ ይከበራል። ለምሳሌ፡- በኦሮሚያ ክልል "ኡኬ"፣ በአማራ ክልልና በአዲስ አበባ ደግሞ ደብረታቦር ወይም ቡሄ በመባልይ ታወቃል። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ደግሞ ደብረ ታቦር (የክርስቶስ መገለጥ ቀን) ተብሎ ይጠራል። በቡሄ በዓል ጊዜ ቀድሞ ይደረደሩ የነበሩት ቃላዊ ግጥሞች በአሁኑ ሰዓት በተለይም "ቡሄ" በከተማዎች አካባቢ ቅርፃቸውን ከመቀየራቸውም ባሻገር የትርጉም ለውጥም ይስተዋልባቸዋል። ይህ ደግሞ ትክክል አይደለም። ልጆች ድሮ፡-

ክፈት በለው በሩን
የጌታዬን፤
ክፈት በለው ተነሳ
ያንን አንበሳ---

እያሉ በመጨፈር በአቀንቃኙ መሪነት ወደሚጨፍሩበት ቤት ያመራሉ:: ከዚያም

ዝና ጠይቆ የመጣ እንግዳ
እራቱ ሙክት ምሳው ፍሪዳ...

እያለ አቀንቃኙ ሲያዜም ተቀባዮችም ይህንን ይደግማሉ:: አያይዘውም

ሆያ ሆዬ፣
ወይ የኔ ጌታ ዋርካ ነህ ዋርካ
ቢጠለሉብህ የማታስነካ---

ሲል አቀንቃኙ፣ ተቀባዮቹም “ሆ” እያሉ አባወራውን ያሞግሳሉ:: በዚያም ሳይበቃቸው ለእማወራዋም እንዲህ ሲሉ ይገጥሙላታል::

የኔማ እመቤት መጣንልሽ
የቤት ባልትና ልናይልሽ::
የኔማ እመቤት ብትሰራ ዶሮ
ሽታው ይጣራል ገመገም ዞሮ---

እያሉ ወይዘሪቷን በሙያዋና በባልትናዋ ያወድሷታል:: ይህንን ሁሉ ብለው የዳቦ ስጦታው የዘገየ ከሆነ የሚሉት ነገር አይጠፋቸውም:: ለምሳሌ፡-

አንዱን አምጭው አታማርጭው
ወደጓዳ አታሩጭው፤ ይላሉ::

ከዚያ የልጆቹ መምጣት የምስራች ማብሰር ሆኖ ስለሚቆጠር ባለቤቱ በደስታ ይቀበላቸዋል:: መርቆ ሙልሙል ዳቦ ሰጥቶም ይሸኛቸዋል:: ወጣቶችም በተራቸው እንዲህ እያሉ ይመርቋቸዋል::

ክበር በስንዴ ክበር በጤፍ
ምቀኛህ ይርገፍ--- እያሉ ይመርቋቸዋል::

ይህ ሁሉ በከተማውም በገጠሩም ቀደም ሲል የነበረ የቡሄ አከባበር ነው:: አሁንስ ከተባለ ገጠሩ ላይ ብዙም ለውጥ አይታይም፤ የቃል ግጥሙ ልዩነት የመጣው ወደ ከተማው ሲገባ ነው:: ለአብነት በአዲስ አበባ ከተማ የሚደረደሩ ቃላዊ ግጥሞችን ስንመለከት፡-

አስዮ ቤሌማ ሆሆ
አስዮ ቤሌማ የቤሌማ እናት
ሆሆ አስር ...ፎቅ አላት...

በማለት ጉዞ ወደ እሚጨፍሩበት ቤት ያደርጋሉ:: ከዚያ እንደደረሱም፡-

መጠለሉንስ ተጠልያለሁ
ያችን ስሙኒ የት አገኛለሁ። እያሉ ያዜማሉ። ቀጥለ ው ደግሞ ወደ ሙገሳው ይገባሉ።
እዚያ ማዶ አንድ ሻሽ
እዚህ ማዶ አንድ ሻሽ
የኔማ እገሌ ወርቅ ለባሽ---
እዚያ ማዶ አንድ ጀሪካን
የኔማ ጋሽዬ ሊሄድ ነው አሜሪካን---

በማለት ስደትንና ውጭ ናፋቂነትን የሚያበረታታ ይዘት ያለው ግጥም ይደረደራሉ፡ ይህ ደግሞ ጥሩ መልዕክት ስለሌለው መስተካከል ይኖርበታል።

ተማሪዎች እስካሁን ካነበባችሁት ሀሳብ በመነሳት ስለ ቡሄ በዓል አከባበር ምን ተረዳችሁ?

በቀሪው የምንባቡ ክፍልስ ስለ ቡሄ ምን የሚነሳ ይመስላችኋል?

የሁለቱን ዘመናት ግጥሞች በዋናነት አንድ የሚያደርጋቸው የሚባሉበት አውድ ሲሆን የሚከወኑበት ጊዜና ቦታም ተመሳሳይ ነው። ጭፈራውን የሚያከናውኑት ልጆች የዕድሜ ሁኔታም ቢሆን ተመሳሳይነት አለው። ምንምእንኳ የሰንጎ መገን እና የወል ቤት ቅርጽ ያላቸው አንዳንድ ስንኞች ቢኖሩም በሐረግ ያላቸው የቀለም ምጣኔ ተመሳሳይነትም አንድ ያደርጋቸዋል። በየዘመናቱ የተጠቀሱ ግጥሞች በቃላት አጠቃቀምና በግጥም አፈጣጠር ደግሞ ልዩነት አላቸው። በአንደኛው ዘመን የሌሉ የቃላት አጠቃቀሞች በሌላኛው ዘመን ላይ ይስተዋላሉ። በተለይም በቀደምት የቡሄ በሉ ግጥሞች ውስጥ ያሉ ቃላት በአሁኑ ዘመን ላይ አይታዩም። ከእነዚህም ውስጥ አጋፋሪ፣ ጥጃ፣ ገመገም፣ የንብእንጀራ፣ የሽረሪት ድር የሚሉት ቃላት በአሁን ዘመን ላይ ካሉት ግጥሞች ውስጥ አይታዩም። የዘመናት ልዩነት የቡሄ ቃላዊግ ጥሞችን ለውጥ ማምጣቱ ተፈጥሯዊ ቢሆንም ባህል፣ ወግና ማንነትን ባለቀቀ መልኩ ቢሆን የተሻለ ነው።

(በጽጌረዳ ጫንያለው፣ ነሃሴ 12/2011፣ አዲስዘመን ለዚህ የክፍል ደረጃ ተሻሽሎ የቀረበ)

## ድህረ ንባብ

### መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆኑ “እውነት”፣ ስህተት ከሆኑ ደግሞ “ሀሰት” በማለት መልሱ፡፡

፩. ከይዘት በስተቀር ወግና ማንነትን ባለቀቀ መልኩ በዘመናት ልዩነት በቡሄ ቃላዊ ግጥሞች የቃላት አጠቃቀም ላይ ለውጥ ቢታይ ችግር የለውም፡፡

፪. የቡሄ በዓል ልጆች እየዞሩ በመጨፈር የሚያከብሩት ነው፡፡

፫. ቀድሞም ሆነ በአሁኑ ጊዜ በቡሄ ወቅት የሚደረደሩ ቃላዊ ግጥሞች ይዘታቸው (የሚያስተላልፉት መልዕክት) ተመሳሳይ ነው፡፡

፬. በየዘመናቱ የተጠቀሱ የቡሄ ቃላዊ ግጥሞች የቃላት አጠቃቀምና የግጥም አፈጣጠር ልዩነት አላቸው፡፡

፭. በቡሄ ጊዜ የሚደረደሩ ቃላዊ ግጥሞች በሀረግ ያላቸው የቀለም ምጣኔ ሁል ጊዜም ተመሳሳይ ነው፡፡

### መልመጃ ሁለት

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሰረት ተስማሚውን መልስ ምረጡ፡፡

፩. ቡሄ የሚለው በዓል ከበዓላት አኳያ በየትኛው እንመድበዋለን?

ሀ. ከህዝባዊ    ሐ. ከድል

ለ. ከባህላዊ    መ. መልስ አልተሰጠም

፪. የቡሄ በዓል ሲከበር ከሚከናወኑ ተግባራት ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው?

ሀ. ጅራፍ ማጮህ

ለ. ችቦ ማብራት

ሐ. ሙልሙል ዳቦ ማዘጋጀት

መ. የአዛውንቶች ጭፈራ

፫. በቡሄ ጊዜ በሚደረደሩ ቃላዊ ግጥሞች ላይ በአብዛኛው ልዩነት እየታየ ያለው የት ነው?

ሀ. በገጠር    ሐ. በትምህርት ቤት

ለ. በከተማ    መ. በቀበሌ

**ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዳጠያየቃቸው ቃላዊ ምላሽ ስጡ፡፡**

1. በምንባቡ አንቀጽ ሁለት ላይ "ቀዳሚ የበዓላት መነሻ" ተብሎ የተገለፀው ለምንድን ነው?
2. የኔማ እመቤት ብትሰራ ዶሮ
   ሽታው ይጣራል ገመገም ዞሮ ሲል ምን ለማለት ተፈልጎ ነው?
3. በሁለቱ ትውልድ መካከል የባህል ውርርስ ላይ ልዩነት እንዲፈጠር ያደረገው ነገር ምንድ ነው?

## ክፍል አራት፡- መጻፍ

### ማስታወሻ

#### ድርሰት

ድርሰት በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የሚያጠነጥኑ አንቀፆችን የያዘ ጽሑፍ ነው፡፡ የተለመዱ የድርሰት አይነቶች አራት ናቸው፡፡ እነሱም፡- ተራኪ ድርሰት፣ ስዕላዊ ድርሰት፣ አመዛዛኝ ወይም አከራካሪ ድርሰትና ገላጭ ወይም አስረጂ ድርሰት ናቸው፡፡ ከነዚህ የድርሰት አይነቶች በዋናነት የምናየው አመዛዛኝ ወይም አከራካሪ ድርሰትን ይሆናል፡፡

አከራካሪ ድርሰት፡- ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ተቃራኒ ሀሳቦችን በማመዛዘን የትኛው እንደሚሻል የሚያሳይ የድርሰት አይነት ነው፡፡

ለምሳሌ፡- አንድ ደራሲ በአንድ መድሃኒት ቀማሚ ይመሰላል፡፡ ምክንያቱም መድሃኒት ቀማሚ ሳይማርና ልምድ ሳይኖረው መድኃኒት ቀማሚ እሆናለሁ ቢል ተቀባይነት እንደማይኖረው ሁሉ ደራሲም አንድ ጽሁፍ ከማዘጋጀቱ በፊት የጽሁፉን ስርዓት ጠንቅቆ ማጥናት ይጠበቅበታልና፡፡

#### ተግባር

ቅርሶችን የመጠበቅ ሀላፊነት የመንግስት ብቻ ወይስ የእያንዳንዱ ግለሰብ? በሚል ርዕስ ባለ ሶስት አንቀጽ ድርሰት ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተራ በተራ አንብቡላቸው፡፡

# ክፍል አምስት፡- ቃላት

## ዐውዳዊ ፍቺ

### መልመጃ አንድ

ከዚህ ቀጥሎ ከምንባቡ የወጡ ቃላት ቀርበውላችኋል፡፡ አረፍተ ነገር በመመስረት ዐውዳዊ ፍቻቸውን አመልክቱ፡፡

ሀ. ጓዳ
ለ. እማወራ
ሐ. አባወራ
መ. ማበርከት
ሠ. ዝና
ረ. መጠለል
ሰ. ባልትና
ሸ. ሙልሙል

### መልመጃ ሁለት

በ “ሀ” አምድ ለተሰጡት ቃላት ተመሳሳያቸውን በ’ለ” ካሉት በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| ፩. ወገግታ | ሀ. ቦታ፣ ሁኔታ |
| ፪. ቀዳሚ | ለ. ሀያ አምስት ሳንቲም |
| ፫. መገለጥ | ሐ. ምሳሌ |
| ፬. አውራጅ | መ. መታየት |
| ፭. ማብሰር | ሠ. አቀንቃኝ |
| ፮. ስሙኒ | ረ. መጀመሪያ |
| ፯. አውድ | ሰ. ፀዳል |
| ፰. አብነት | ሸ. መንገር |

# ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

## ማስታወሻ

### ጊዜ

ጊዜ አንድ ድርጊት መቼ እንደተፈጸመ ወይም መቼ እንደሚፈጸም የሚገልጽ የግስ ባህሪ ሲሆን በሶስት ይከፈላል፡፡ እነሱም፡-

፩. የሀላፊ ጊዜ

፪. የአሁን ጊዜ

፫. የትንቢት ጊዜ ናቸው፡፡ ከነዚህ ሶስት የግስ አይነቶች ውስጥ የአሁን ጊዜ ግስን በዚህ ርዕስ እናያላን፡፡

የአሁን ጊዜ፡- በአሁን ጊዜ የሚፈጸም ወይም በመፈጸም ላይ ያለ ድርጊትን ወይም ሁነትን የሚገልጽ የጊዜ አይነት ነው፡፡ አሁን የሚበለው አንድ ሰው ስለ አንድ ድርጊት ወይም ሁነት ንግግር የሚያደርግበት ጊዜ ስለሆነ ነው፡፡ የአሁን ጊዜ ግሶች "እየ-" የሚል ምእላድ ሊያስቀድሙና "ነው" የሚል ረዳት ግስ ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡

ምሳሌ፡- ፋጡማ ምሳዋን እየበላች ነው፡፡

ደያሶ ቡና እየጠጣ ነው፡፡

## መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንብባችሁ የአሁን ጊዜ የሚያመላክት ግስ የያዙ አረፍተ ነገሮችን ፊደል ክበቡ፡፡

ሀ. ኦፋይሴ የተሰጣትን የቤት ስራ እየሰራች ነው፡፡

ለ. አልገዮ ከቱርሚ እየመጣ ነበር፡፡

ሐ. ትምህርት ቤታችን የተመሰረተበትን አስረኛ ዓመት ዘንድሮ እያከበረ ነው፡፡

መ. የወንድሜ ልጅ ጅንካ ዩንቨርሲቲ እየተማረች ነው፡፡

ሠ. መሐመድ በሚቀጥለው ዓመት ይመረቃል፡፡

## መልመጃ ሁለት

የአሁን ጊዜ ግሶችን በመጠቀም አምስት አምስት አረፍተ ነገሮችን ስሩ።

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የተለመዱ የድርሰት አይነቶች ተራኪ ድርሰት፣ ስዕላዊ ድርሰት፣ አከራካሪ ወይም አመዛዛኝ ድርሰት እና ገላጭ ድርሰት እንደሆኑና አከራካሪ ድርሰት የሚባለው ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ተቃራኒ ሀሳቦችን በማመዛዘን የትኛው እንደሚሻል የምናሳይበት የድርሰት አይነት እንደሆነ ተገንዝበናል።

በመጨረሻም የአሁን ጊዜ፣ የሀላፊ ጊዜ እና የትንቢት ግሶች እንዳሉና የአሁን ጊዜ ግሶች በአሁን ጊዜ የሚፈፀም ወይም በመፈፀም ላይ ያለን ድርጊት የሚገልፁ መሆናቸውን አይተናል።

## የክለሳ ጥያቄዎች

ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የአሁን ጊዜ ግስ የያዙት አረፍተ ነገሮችን ፊደል በማክበብ አመልክቱ።

ሀ. ዘይነባ ወደትምህርት ቤት እየመጣች ነው።

ለ. ዳንቺሌን ትናንትና መርካቶ አየኋት።

ሐ. ዓባይ በኢትዮጵያውያን የተባበረ ክንድ እየተገደበ ነው።

መ. ቡሎወደ ገበያ እሄዳለሁ ብሎኝ ነበር።

ሠ. ቃለአብ የቤት ስራውን እየሰራ ነው።

ረ. ዳዊት በሚቀጥለው ሳምንት ከይርጋ ጨፌ ወደዲላ ይመለሳል።

ሰ. ወደፊት በሥነ ምግባር የታነፀ፣ በእውቀት የጎለበተ ጥሩ መምህር መሆን እፈልጋለሁ።

# ምዕራፍ ሶስት

## ሰብዓዊ እሴቶች

### ከዚህ ትምህርት የሚጠበቁ ውጤቶች፣

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ፡-

- አዳምጣችሁ የጽሑፉን መልእክት ትመዝናላችሁ፤
- ስለ ሰብዓዊ እሴት ምንነት ታብራራላችሁ፤
- ከሌሎች ጋር ምልልስ ታደርጋላችሁ፤
- በሰብዓዊ እሴት ውስጥ የሚካተቱ ነገሮችን ትዘረዝራላችሁ፤
- የቀረበላችሁን ጽሑፍ በመመዘን የተገነዘባችሁትን በአራት አንቀጽ ትጽፋላችሁ

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### ዶክተር ካትሪን ሀምሊን

**ቅድመ ማዳመጥ**

**ተግባር**

- ተማሪዎች በጎነት ለራስ ነው የሚባለው ለምን ይመስላችኋል?
- በሀገራችን በበጎ አድራጎት ስራ ላይ የተሰማሩ ግለሰቦችን ወይም ድርጅቶችን ስም ጥቀሱ፡፡
- ዶክተር ካትሪን ሀምሊንን ከፊስቱላ በሽታ ጋር የሚያገናኛቸው ምን ይመስላችኋል?
- ከዚህ በታች የቀረበውን ስዕል አይታችሁ የተረዳችሁትን ግለፁ፡፡




## ድህረ ማዳመጥ

### መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት በጽሑፍ መልሱ፡፡

፩. የምንባቡ አጠቃላይ ሀሳብ ምንድን ነው?

፪. ዶክተር ካትሪን ሀምሊን የየትሀገር ተወላጅ ናቸው?

፫. በምንባቡ ውስጥ በሥራቸው የተዳሰሰላቸው ዶክተር የምን ሙያ ባለቤት ናቸው?

፬. ባለታሪኳ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲቆዩ ያስገደዳቸው ምክንያት ምንድን ነው?

፭. ምንባቡ ባለስንት አንቀጽ ነው?

፮. ዶክተር ካትሪን ሀምሊን ሴቶችን በህክምና ከመርዳት ባለፈ ምን ምን ጉዳዮች ያከናውኑ ነበር?

፯. የዶክተሯ አስተዋጽኦ በዋጋ የሚተመን ይመስላችኋል? እንዴት?

፰. የበጎ ስራ ባለቤት ለሆኑት ዶክተር ሀምሊን ከተበረከቱላቸው ሽልማቶች መካከል ቢያንስ ሶስቱን ዘርዝሩ፡፡

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ማስታወሻ

**ጭውውት**

ጭውውት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች እርስ በእርስ የሚያካሂዱት ምልልስ ነው፡፡ በጭውውት ወቅት አንዱ ከሌላው የችግርን መፍቻ ሀሳብ ያገኝበታል፤ ልምድም ይጋራበታል፡፡ በጭውውት ጊዜ የእርስ በእርስ መደማመጥና መከባበር እንደተጠበቀ ሆኖ ቀልዶችን ጣል ጣል እያደረጉ ዘና ማለት የተለመደ ነው፡፡

## መልመጃ አንድ

አራት አራት ሆናችሁ በመቧደን ከዚህ በታች የቀረበላችሁን ጭውውት በተግባር ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

(እናት ወ/ሮ ታጸኔ እርጅና የተጫጫናቸው ከመሆናቸውም በላይ፣ አብዛኛዎቹ ጥርሶቻቸው ወልቀው ከቀሩት ጥቂት ጥርሶች መካከል የመንጋጋ ጥርሳቸውን አሟቸዋል፡፡ ዛሬ ደግሞ የሆስፒታል ቀጠሮ አላቸው፡፡ ልጃቸው ኤርቆጮ ባለቤቱዲቦራን ወደ እናቱ ቤት ልኮ እሱ ሀኪም ቤት የሚወስዳቸውን መኪና ለማፈላለግ ወደኋላ ቀርቷል፡፡ ዲቦራ አማቷ ቤት በደረሰች ጊዜ ወ/ሮ ታጸኔ ፊት ለፊት ተቀምጠው ከጎረቤታቸው ከአቶ ጋንኪሲ ጋር እየተጫወቱ ነበር፡፡)

ዲቦራ፡- “ሰላም ለዚህ ቤት! እንደምን አደራችሁ!”

አቶ ጋንኪሲ፡- “ፈጣሪ ይመስገን እንዴት ሰነበትሽ?”

ዲቦራ፡- “እማማ! እንዴት ነዎት ዛሬ?” አለች ከአቶ ጋንኪሲ ጋር ሰላምታ ከተለዋወጠች በኋላ ወደ አማቷ ጠጋ ብላ፡፡

ወ/ሮ ታጸኔ፡- “በጎ ነኝ ልጄ! መቼም ከትናንትናው ዛሬ መለስ ብሎልኛል” ካሉ በኋላ ወዲያውኑ “ኤርቆጮን የት ጥለሽው መጣሽ?” ብለው ጠየቋት፡፡

ዲቦራ፡- “ከቤት አብረን ወጣንና “አንቺ ቀድመሽ እማማን አዘጋጃት እኔ መኪና አፈላልጌ ልምጣ’ ብሎኝ ነው የተለያየነው፤ አሁን ይመጣል፡፡” ካለች በኋላ፣ ፊታቸውን የተሸፋፈኑበትን ነጠላ ገልጣ ለማየት እየሞከረች፣ “እረ ተመስገን ነው፤ ዛሬማ እብጠቱም ቀንሷል እኮ! አለች፡፡”

ወ/ሮ ታጸኔ፡- “እኔማ መቼም ሲይዘኝ “ኖሮ ኖሮ ከመሬት፣ ዞሮ ዞሮ ከቤት’ ነውና መሞቴ ካልቀረ ለምን እድሜ ሰጥተህ ታሰቃየኛለህ? እያልኩ፣ ፈጣሪየን አማረርኩት፡፡ የሱ ቸርነት አያልቅም፤ አሁን ደግሞ ተንፈስ አደረገኝ፡፡”

አቶ ጋንኪሲ፡- “አይ እሜቴ! ለምን ሆደ ባሻ ይሆናሉ? በትንሽ በትልቁ ፈጣሪን ማማረር የለብዎትም “እግዜር በትር ሲቆርጥ ቆላ አይወርድም’ ሲባል አልሰሙም?”

ወ/ሮ ታጸኔ፡- “አይ ጋንኪሲ! በጊዜ በሰበሰበኝ ምንኛ ደግ ነበር? አየህ! የሰጠኝን በሽታ ሁሉ ሆዴን አስፍቼ ችየው ነበር፡፡ አሁን ግን የማልችለውን እየሰጠኝ ነው፡፡ “ልጅ ከጠረው ጥርስ የጦረው’ ይባላል እኮ!” እንዳሉ ኤርቆጮ ወደ ቤት ይገባል፡፡

አቶ ኤርቆጮ:- "እንዴት አደራችሁ? ምነው ዲቦራ፣ እማማን አላዘጋጀሻትም እንዴ!?" ካለ በኋላ፣ መለስ ብሎ "እማማ! ተሽሎሽ አደረ?" አላቸው።

ወ/ሮ ታጸኔ:- "በጎ ነኝ ልጄ! ምንም አልል። ና እንግዲህ መኪናውን ካመጣህ ደገፍ አድርገኝና እንሂድ።"

አቶ ኤርቆጮ:- "እሺ! አይዞሽ እማማ ትድኛለሽ" እያለ ደግፎ ያነሳቸዋል። "አይዝዎት! አይዝዎት! ይድናሉ" እያሉ ወይዘሮ ዲቦራና አቶ ጋንኪሲም እየደገፏቸው ይወጣሉ።

## መልመጃ ሁለት

**ጥንድ ጥንድ በመሆን ከዚህ በታች በቀረበላችሁ ርዕስ ጉዳዮች ላይ ውይይት አድርጉ።**

ሀ. ሰዎችን ማክበር ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. በሰብአዊ እሴት ውስጥ የሚካተቱትን ነገሮች ዘርዝሩ።

ሐ. በአካባቢያችሁ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶችንና ግለሰቦችን በመዘርዘር የሚያከናውኑትን ተግባር አስረዱ።

- ከሁለት አንዳችሁ ከላይ በተወያያችሁባቸው ርዕሰ ጉዳዮች ላይ መረጃ ሰጪ ንግግር አድርጉ።

## ክፍል ሶስት:- ማንበብ

### ጉርብትና





## ቅድመ ንባብ

### ተግባር

፩. ሰዎች ከጎረቤቶቻቸው ጋር ምን አይነት ግንኙነት ሊኖራቸው ይገባል ብላችሁ ታስባላችሁ?
፪. "ከሩቅ ዘመድ የቅርብ ጎረቤት" የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ምንን የሚያበረታታ ይመስላችኋል?
፫. "ጉርብትና" የሚለውን ምንባብ ርዕሱንና ስዕሉን በመመልከት ይዘቱን ገምቱ?

## ጉርብትና

በአንጉል ጨዋታዎች ላይ መሆናችንን የሚያስጠነቅቀን ዞርበሉ፣ ልብ አድርጉ፣ አንተ ስድ፣ አንተ ወሸካታ የሚል የለመድነው የዘይነባ ሰኢድ ድምጽ ነው። ጉፍታዋን ተከናንባ፤ እህል ከእንክርዳድ እየለየች፤ አይኖቿን ወደምንጫወትበት እየሰደደች፤ ዋልጌነታችንን በተግሳጽ ትከረክማለች። የዘይነባን "አን" ትርጉም ግን ጥቂት ከታገለችኝ በኋላ ደረስኩባት ለካ ዘይነባ "ወሎዬ" ናት። በተወለደችበት ቀዬ አንተ ባለጌ ለማለት "ተ" ፊደል የስሜታቸውን ድምጽ ትሰብር ስለነበር "ተ" ን እየገደፉ "አን ሌባ" ማለትን ቀጠሉበት የሚል የራሴ ድምዳሜ ላይ ደረስኩ።

ምነው እሜቴ! ትለኛለች ከትምህርት ቤት ስመጣ ከቤታችን ምሳ ባለመድረሱ ከሷ ቤት ሂጄ ወጥ ለማስጨመር አንከርፍፌ የያዝኩትን ደረቅ እንጀራ ወደ ሰሃኑ እያስጠጋችና እንደ ባለ መብት ከፊቷ የተገተርኩትን እኔን እያየች። ድንች በስጋን ሳድግ ወይ ሳገባ የዘወትር ቀለቤ አደርገዋለሁ የሚል ምኞት ያደረብኝ ብርሃኔ ያለስስት እንጀራዬ ላይ ደፍታበት የጣቶቼ ግማሽ እና የከንፈሬን ክፈፍ በወዝ ያራሰችበት ቀን የእርካታዬ መጠን ወደፊት ድንች በስጋ ከእቅዴ ውስጥ እንዲገባ አስገደደው። ይህ ለአንድ አጋጣሚ የተሰራ ደግነት ሳይሆን ባስፈለገኝ ጊዜ ሁሉ የብርሃኔ ቤት ቤቴ ነው።

ፋጡማ መንሱር ከውቅሮ ከመጣች ከ40 ዓመት በላይ ሆኗታል፤ እጇ መድሃኒት ነው። ወላጆቻችን እኛን ሀኪም ቤት ከመውሰድ ይልቅ በእርሷ ባህላዊ የህክምና ዘዴ ተጠቅመው ከህመማችን ይገላግሉናል። ከሁሉ የሚገርመኝ አፍ መፍታት ላልቻለ ህጻን፣ ለጆሮ ደግፍ፣ ለቦሃ፣ ጸጉር አላበቅል ላለ ጭንቅላት የምታዛቸው መንፈሳዊ ምክርና ከእጽዋትና ከስራስር የምታዘጋጃቸው መድሀኒቶች ውጤታማነት ነው።

ፋጡማ ለኔ በልዩ ስፍራ የማስቀምጣት በየምክንያቱ የምገልጻት መጽሃፈ ምሳሌዬ ናት፡፡ ምክንያቱም እሷ ሰጥታ የማትጠግብ፣ ካዘነው ጋር የምታዝን፣ ፈጣሪን መፍራት በየእለት እንቅስቃሴዋ የምትተገብር ሰው ናትና፡፡

በጥፋቶቻችን የምንገረፍባት "ዘነበች" የምትባል አለንጋ ነበራቸው ጋሽ ዘሪሁን ጉዴ፡፡ የመንደሩ ህጻናት ከወላጆቻቸው ይልቅ የሚፈሩት እርሳቸውን ነው፡፡ ህጻናቱ የመንደሩን መተዳደሪያ ደንብ ሳያጓድሉ የመኖር ግዴታ አለባቸው፡፡ ትንሽ ቅብጠት ካሳየን ጋሽ ዘሪሁን "ፊልድ" ሄደዋል ማለት ነው፡፡ ያም ቢሆን ጥፋታችንን ገልጠው የሚያስለጠልጡን ወላጆቻችን ነበሩ፡፡ እኛም በርሳቸው በመገረፋችን የምንቋጥረው የቂም ዶሴ አልነበረንም፡፡ የፍቅር ልምጭ እንደሆነ የልጅነት ንጹህ ልባችን መስክሮልናል ባይ ነኝ፡፡ አንዳንዴ ባንዳችን ጥፋት ሁላችንም ታጉረን የምንለጠለጥበት ምክንያት ግር ይለን ነበር፡፡ ቆይተን አጥፊው እንዳያጠፋ የኛ ተግሳጽ ያስፈልግ እንደነበር ገባን፡፡ ቸልተኝነት፣ ምናገባኝነት፣ እኔ የለሁበትም ማለት ለካ ጥፋትን መተባበር ነው አልን፡፡ በጋራ እንዳንገረፍ ጥፋትን በጋራ መከላከልን ለመድንበት፡፡ አሁን አሁን በቸልታ፣ በእኔ የለሁበትም የሚጠፉ ጥፋቶችን ሳይ በጋሽ ዘሪሁን አለንጋ **ማስለጥለጥ** ነበር የሚል ቁጭት ይይዘኛል፡፡

በበርበሬና ዘይት የታሸ የጤፍ እና የስንዴ ቅይጥ ዳቦ ቆሎ ጆሮ ግንዳችንን እስኪያመን ከበላን "እታተይ" ከወልድያ አምጥታልን ነው፡፡ ክረምቱን ከእርሷ ቤት በራፍ ተቀምጠን ዳንቴል በመስራት እንሽቀዳደማለን፡፡ ሰብሰብ ብለን ስንቀመጥ እየመጠኑ መሳቅን፣ ከንፈር ገጥሞ ማላመጥን፣ ኳደኛ አለማብዛትንና ንጽህና መጠበቅን ደጋግማ በመናገሯ ይሰለቸን ነበር፡፡ በኋላ ላይ ተማሪን ("ረ"ትጠብቃለች) አስቴር ብለን የኮድ ስም ሰጠናት፡፡ ልክ ለምክር ስትጠራን በሹክሹክታ በሉ አስቴር ሙዚቃዋን ልትከፍትብን ነው ብለን እንሳሳቅ ነበር፡፡ እታቴ (የወርቅ ውሃ) ለኔ የክርስትና እናቴ ለልጅ ፊት የማሳየት ልምድ ባይኖራትም እንኳ በልጅነት ምኞታችን ድፍረት በካርቦን (ጉሎ) የተዘፈዘፈ ነጠላዋን ደብቀን በመልበሳችን የማገር ስባሪ መዛብን እስክትረሳው አያቴ ሰፈር ከርሜያለሁ፡፡ ኡ----ጵ-----ላ----ስ! ተባብለን የሰቀለችውን ቋንጣ ቆረጥመን አለቀልን ስንል ራርታልናለች፡፡ ሳል ሲያመኝ ኑግና አጃ የምታፈላልኝ እርሷ ናት፡፡

*ተማሪዎች እስካሁን ካነበባችሁት ሀሳብ በመነሳት ጉርብትናን በተመለከተ ምን ተረዳችሁ?*

*በቀሪው የምንባቡ ክፍልስ ጉርብትናን በተመለከተ ምን የሚነሳ ይመስላችኋል?*

እኔ እንግዲህ የነኚህ ሰዎች ሰፈር ሰው ነኝ፡፡ ሰፈሬ ማንነቴ ነው፡፡ ይህ ማንነቴ

በመንፈስም ሆነ በአካል እንዲጠረቃ ጎረቤቶቼን የሰበሰበልኝ፤ በተዋጣ ፍቅር፣ በተዋጣ ምግብ፣ በተዋጣ ምርቃትና በተዋጣ ተግሳጽ እንዳድግ የተመረጥኩ እድለኛ ሰው ነኝ። በነኚህ ሰዎች ምክንያት ህብረት፣ እኩልነትንና እኛነትን ተምሬያለሁ። ሰብዓዊነትን፣ ኢትዮጵያዊነትንና የአስተሳሰብ ልህቀትን ቀስሜበታለሁ። ለኔ የሀገር ትርጉም ከዚህ በላይም አይደለም። እኔነቴ በእያንዳንዳቸው ቋንቋ፣ በእያንዳንዳቸው ባህል፣ በእያንዳንዳቸው ሀይማኖት ተገጥግጧል።

በተረፈ ከዛጉ ጣሪያዎች ስር አዕላፋትን የሚገነቡ ንጹህ ልቦች እንዳሉ ምስክር ነኝ። አሳሳች ሀሳቦችን የምንመክትበት ጥሩር ላስታጠቁን ጎረቤቶቻችን ወሰን የለሽ ክብር አለኝ። እኔና እኩዮቼ በተለያዩ ከተማና አለማት ተበትነናል፤ ነገር ግን ውላችንን እንዳንስት ወደኛ የሚወነጨፉትን አፍራሽ አመለካከቶች ለማክሰም ቃል አለን።

(ምስራቅ ተረፈ፣ 2009፣ ጨው በረንዳ፣ ለማስተማሪያነት እንዲያገለግል ተሻሽሎ የቀረበ)

## ድህረ ማዳመጥ

### መልመጃ አንድ

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሰረት ተስማሚውን መልስ ምረጡ።

፩. በትረካው የተገለጸችው ዘይነባ ሰኢድ "አንተ" ለማለት "አን" የምትለው ለምንድን ነው?

ሀ. በተፈጥሮዋ ኮልታፋ ስለነበረች

ለ. "ተ" ፊደል የስሜቷን ድምጽ ትሰብር ስለነበር

ሐ. በአማርኛ መነጋገር ስለሚከብዳት

መ. መልስ አልተሰጠም

፪. በምንባቡ ውስጥ የተጠቀሰችው ፋጡማ መንሱር ምን አይነት ልዩ ችሎታ ነበራት?

ሀ. ሰውን ማስተናገድ

ሐ. ድንች በስጋ ወጥ መስራት

ለ. ባህላዊ መድሃኒት መቀመም

መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው

፫. የጋሽ ዘሪሁን ጉዴ አለንጋ ምን ተብላ ትጠራለች?

ሀ. ዘነበች ለ. አስናቀች ሐ. አበበች መ. ዘረፈች

፬. "ባንዳችን ጥፋት ሁላችንም ታጉረን የምንለጠለጥበት ምክንያት ግር ይለን ነበር" ስትል ምን ማለቷ ነው?

ሀ. በወቅቱ ልጆችን ለማስተካከል ይሰጥ የነበረውን ፍትሀዊ ያልሆነ ቅጣት ማመልከት ነው፡፡

ለ. "ምናገባኝነት" እና "እኔ የለሁበትም" ማለት ጥፋት መሆኑን ማሳየቷ ነው፡፡

ሐ. ጎረቤቶቿ ልጆች እንዳይበላሹ ለማድረግ የሚጠቀሙበትን ዘዴ ማመልከቷ ነው፡፡

መ. ለ ና ሐ

## መልመጃ ሁለት

ከዚህ በታች ከምንባቡ ውስጥ የወጡ አዳዲስ ቃላት ቀርበዋል፡፡ ቃላቱ በምንባቡ ውስጥ ባላቸው አገባብ መሰረት ፍቻቸውን ስጡ፡፡

ምሳሌ፡-

ዋልጌ፡- ባለጌ

ወሽካታ፡- ለፍላፊ

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ቀዬ | መ. እየገደፉ | ሰ. ኦጵላስ |
| ለ. ትከረክማለች | ሠ. አንከርፍፌ | |
| ሐ. ቦሃ | ረ. ክፊፍ | |

## መልመጃ ሶስት

ከዚህ በታች ከምንባቡ የወጡ ቃላት በሰንጠረዥ ቀርበዋል፡፡ ከቀረቡት ቃላት በመምረጥና ባዶ ቦታው ውስጥ በማስገባት አረፍተ ነገሩን አሟልታችሁ ፃፉ፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ጉፍታ | ማገር | ቀዬ | የቂም ዶሴ | ዋልጌ |
| ፊት ማሳየት | ወሽካታ | ልህቀት | ጥሩር | የምንለጠለጥበት |

፩. አዛውንቶችን የማያከብር ልጅ በማህበረሰቡ________ተብሎ ሊነቀፍ ይችላል፡፡

፪. ልጆች ሲያጠፉ በጎረቤቶቻቸው ቢገሰጹ____________ አይቋጥሩም፡፡

፫. የዘምዘም ________ ሰማያዊ እና ለስላሳ ነው፡፡

፬. ብዙ ሰዎች በተለያየ ምክንያት ከኖሩበት ______ሊሰደዱ ይችላሉ፡፡

፭. ያለ የሌለውን ነገር የሚለፈልፍ ሰው __ተብሎ በሰዎች ሊገሰጽ ይችላል፡፡

፮. የአእምሮ ________ መኖር አካባቢንና ሀገርን ያሳድጋል፡፡

፯. ለልጅ _________________ ልጅን ማቅበጥ ነው ብለው ያስባሉ፡፡

፰. ወታደሮቹ ወደ ጦር ሜዳ ሲሄዱ ------------ለበሱ፡፡

## ክፍል አራት፡- መጻፍ

### ማስታወሻ

#### ቢጋር /አስተዋጽኦ/ መንደፍ

ቢጋር ወይም አስተዋጽኦ አንድ ድርሰት ከመፃፋችን በፊት በውስጡ ሊገኙ የሚችሉ ዋና ዋና ነጥቦችን አካቶ የሚይዝ ቅርጽ ነው፡፡ በተጨማሪም የሃሳብ ቅደም ተከተልን በቅድሚያ ለመወሰንና በወጉ ለማቀናበር ያግዛል፡፡

#### የቢጋር ጥቅሞች

- አላማን ግልጽ ለማድረግና ሀሳብን ከአላማ ጋር ለማዛመድ ያግዛል፤
- ድርሰቱ ከመጻፉ በፊት የሀሳቡን ቅንጅት ለማየትና ለማስተካከል ይጠቅማል፤\
- መልዕክትን ለማስተላለፍ ራሱን የቻለ መሳሪያ በመሆን ያገለግላል፤
- ጽሁፍ በሚጻፍበት ጊዜ ከዋናው ሀሳብ ላለማፈንገጥ ይረዳል፡፡

ምሳሌ ፡- ርዕስ፡- የጎዳና ሕይወት

ርዕሱ ሰፊ ስለሆነ መጥበብ ይኖርበታል፡፡

1. ለጎዳና ተዳዳሪነት የሚዳርጉ ምክንያቶች

1.1 ከመጥፎ ጓደኛ ጋር መወዳጀት

1.2 በአጉል ሱሶች መጠመድ

1.2.1. በሲጋራ

1.2.2. በጫት

1.2.3. በአልኮል መጠጥ

## መልመጃ አንድ

በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ ያሉ ጥምርቃላትን ተጠቅማችሁ ከታች ያሉትን አረፍተ ነገሮች አሟልታችሁ ፃፉ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| መቅረፀ-ድምጽ | ሰላማዊ ሰልፍ | አውራ ጎዳና |
| ብርድ ልብስ | ቤተ-መንግስት | ትምህርት ቤት |
| ብረት ምጣድ | ሸክላ ድስት | አየር መንገድ |

፩. ኢትዮጵያውያን የህዳሴ ግድብ ግንባታ ስላስደሰታቸው______________አካሄዱ፡፡

፪. አሜሪካ ኢምባሲ ቅጥር ግቢ ውስጥ_______________ይዞ መግባት አይቻልም፡፡

፫. እናቴ ዶሮ ወጥ የምትሰራበት_________________ገዛች፡፡

፬. ሀሴት የገብስ ቆሎ ለመቁላት ከጎረቤቷ__________________ተዋሰች፡፡

፭. ጽዱ እና ውብ የሆነው የአንድነት ፓርክ መገኛ ቦታው_______________ነው፡፡

፮. ከአዲስ አበባ ወደ ሀዋሳ የሚወስደው_____________በመፍረሱ እየተጠገነ ነው፡፡

፯. የኢትዮጵያ_________________ሰራተኞች ስራቸውን በአግባቡ እየተወጡ ነው፡፡

## መልመጃ ሁለት

በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ ያሉ ውስብስብ ቃላትን ተጠቅማችሁ ከታች ያሉትን አረፍተ ነገሮች አሟልታችሁ ፃፉ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ይፈጥርላቸዋል | ተማሪዎቻቸው | አገልግሎታቸውን |
| ይገነዘቡበታል | ኑሯቸውን | ከተከታተልናቸው |
| መልዕክቶችን | እየጨፈጨፉ | ምጣኔ ሀብታዊ |

፩. የአንድ ሀገር________እድገት በዜጎች ኑሮ ላይ ለውጥ ማምጣት ይኖርበታል፡፡

፪. ሰዎች ደኖችን______________የአካባቢ መራቆት እንዲፈጠር ያደርጋሉ፡፡

፫. ደብዳቤ _______________ለማስተላለፍ ያገለግላል፡፡

፬. ሰዎች ለሰዎች መልካም ነገሮችን ሲያደርጉ የህሊና እርካታ_____________፡፡

፭. በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን_____________ለማሻሻል ሌት ተቀን በርካታ ስራዎችን ይሰራሉ፡፡

፲. አንዳንድ መስሪያ ቤቶች ______________ለህዝብ ይፋ ያደርጋሉ፡፡

፲. መምህራን ለ______________ሁልጊዜ አርአያ መሆን አለባቸው፡፡

፲. አረጋውያንን ትኩረት ሰጥተን ካዳመጥናቸው እና______________ጠቃሚ ምክሮችን ያስጨብጡናል፡፡

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

### ማስታወሻ

#### ቁጥር

ስሞች ተቆጣሪና ኢተቆጣሪ (የሚቆጠሩና የማይቆጠሩ) ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡ ተቆጣሪ ስሞች ነጠላና ብዙ ተብለው እንደገና በሁለት ይከፈላሉ፡፡ ነጠላ ቁጥር የሚባሉት በቁጥር አንድ ብቻ ወይም አንድ ፍሬ ብቻ መሆኑን የሚያመለክቱ ስሞች ናቸው፡፡ ብዙ ቁጥር የሚባሉት ደግሞ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ነገሮችን ለመግለጽ የምንጠቀምባቸው ስሞች ናቸው፡፡ ማንኛውም ስም የሆነ ቃል ተቆጣሪ ነገሮችን የሚጠቁም ከሆነ የቁጥር ምዕላድ ይባላል፡፡

| ምሳሌ፡- | ነጠላ . | ቅጥያ ምዕላድ | ቃል (ብዙ) |
|---|---|---|---|
| | ልጅ.. | -ኦች .. | ልጆች |

“-ኦች” ብዛትን የሚገልጽ ጥገኛ ምዕላድ ሲሆን ነጠላነትን ለማመልከት ግን ምንም አይነት ምዕላድ አንጠቀምም፡፡ ይህ ምዕላድ በተነባቢ ከሚጨርሱ ምዕላዶች ጋር ሲገባ በአናባቢ የሚጨርሱ ምዕላዶች ላይ ግን “-ዎች” የሚልቅርጽ ይይዛል፡፡

ከግዕዝ ወደ አማርኛ የገቡ ስሞች የግዕዙን የብዙ ቁጥር ምዕላድ ያስከትላሉ፡፡ ግዕዝ ብዙ የቁጥር ምዕላዶች አሉት ከነዚህ አንዱ -ኣት የሚለው ምዕላድ ነው፡፡ የሚከተለውን ለአብነት ተመልከቱ፡፡

| ምሳሌ፡- | ነጠላ | ቅጥያ ምዕላድ | ቃል (ብዙ) |
|---|---|---|---|
| | ቀን . | -ኣት.. | ቀናት |

## መልመጃ አንድ፡

የሚከተሉትን ስሞች "-ኣት" የሚለውን ምዕላድ በመጨመር ወደ ብዙ ቁጥር ለውጡ፡፡

| ተራ ቁጥር | ነጠላ | ብዙ |
|---|---|---|
| ፩. | ዓመት | |
| ፪. | ዲያቆን | |
| ፫. | ወር | |
| ፬. | ካህን | |
| ፭. | ቃል | |

## መልመጃ ሁለት

የሚከተሉትን ምሳሌዎች መነሻ በማድረግ ከታች የተደረደሩትን ነጠላ እና ብዙ ቁጥር አመልካች ስሞች ተጠቅማችሁ አረፍተ ነገር ስሩ፡፡

ምሳሌ፡- ልጅ - ነጠላ

የሁሴን ልጅ በሥነ ምግባር የታነፀ ነው፡፡

ልጆች --- ልጅ-ኦች

የኛ ሰፈር ልጆች በትምህርታቸው ጎበዞች ናቸው፡፡

፩. ሴት

ሴቶች

፪. ላም

ላሞች

፫. ተማሪ

ተማሪዎች

፬. መምህር

መምህራን

፭. ዘመን

ዘመናት

# ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ጭውውት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች እርስ በዕርስ የሚያካሂዱት ምልልስ መሆኑን አይተናል፡፡በተጨማሪም ቢ.ጋር አንድ ድርሰት ከመፃፋችን በፊት በውስጡ ሊገኙ የሚችሉ ዋና ዋና ነጥቦችን አካቶ የሚይዝ ቅርጽ እንደሆነ ተመልክተናል፡፡

የተለያየ ትርጉም ያላቸው ቃላት በአንድ ላይ ሆነው አንድ ለየት ያለ ትርጉም የሚያስገኝበት የቃላት ቅንጅት ጥምር ቃል እንደሚባል አይተናል፡፡ በመጨረሻም በቁጥር አንድ ብቻ ወይም አንድ ፍሬ ብቻ መሆኑን የሚያመለክቱ ስሞች ነጠላ ቁጥር ሲባሉ፤ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ነገሮችን ለመግለጽ የምንጠቀምባቸው ስሞች ብዙ ቁጥር እንደሚባሉ ተመልክተናል፡፡

# የክለሳ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በትኩረት በማንበብ ትክክለኛውን መልስ በክፍት ቦታዎች ላይ አስቀምጡ፡፡

፩. ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚካሄድ ኢ-መደበኛ ውይይት _______________ ይባላል፡፡

፪. የተለያየ ትርጉም ያላቸው ቃላት በአንድ ላይ በመጣመር ለየት ያለ ትርጉም የሚያስገኙበት የቃላት ቅንጅት_______________ይባላል፡፡

፫. ተቆጣሪ ስሞች______________እና______________ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡

፬. _______________ ስሞች በቁጥር አንድ ብቻ ወይም አንድ ፍሬ ብቻ መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

፭. አንድ ድርሰት ለመፃፍ እንደ አቅጣጫ ጠቋሚ ኮምፓስ የምንጠቀምበት መሳሪያ_______________ይባላል፡፡

፮. የሚያስጠጋው ነፃ ምዕላድ የመጨረሻ ፊደል ሳድስ ሲሆን የምንጠቀመው አብዥ ቅጥያ ምዕላድ_______________ ነው፡፡

# ምዕራፍ አራት

# አጭር ልቦለድ

## የሚጠበቁ ውጤቶች፣

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ፡-

- አዳምጣችሁ ተመሳሳይ ታሪክ ትናገራላችሁ፤
- የአጭር ልቦለድን ምንነት ታብራራላችሁ፤
- በጽሁፍ ውስጥ መሸጋገሪያ ቃላትን ትጠቀማላችሁ፤
- የአጭር ልቦለድ አላባውያንን ትዘረዝራላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### የሕይወት ቅዳጆች

### ቅድመ ማዳመጥ

**ተግባር**

፩. በሕይወታችሁ የማትረሱት አሳዛኝ ገጠመኝ ካለ እስኪ ለጓደኞቻችሁ ንገሯቸው?

፪. "የሕይወት ቅዳጆች" በሚል ርዕስ ስር ምን ምን ጉዳዮች የሚዳሰሱ ይመስላችኋል?

## ድህረ ማዳመጥ

### መልመጃ አንድ

**ያዳመጣችሁትን ጽሑፍ መሰረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን መልስ በመምረጥ መልሱ።**

፩. ባዳመጣችሁት ምንባብ ውስጥ እንባው አንዴ እየጠቆረና እየወፈረ፣ አንዴ እየቀጠነና ውሃ እየመሰለ ክረምት ከበጋ ግቢውን አቋርጦ ይፈሳል የተባለው ምንድን ነው?

ሀ. ውሃ
ለ. ወንዝ
ሐ. መጸዳጃ ቤት
መ. ጎርፍ

፪. ሰለሞን የምን መርሃ ግብር ተማሪ ነው?

ሀ. የመጀመሪያ ዲግሪ
ለ. የሶስተኛ ዲግሪ
ሐ. የሁለተኛ ዲግሪ
መ. የዲፕሎማ ተማሪ

፫. ወይኗ "መልሱንስ ጋሽ ሰለሞን" ብላ የጠየቀችው ለምንድን ነው?

ሀ. ውሰጇው እንደሚላት ስላወቀች
ለ. በመልሱ የምትገዛው ነገር አሳስቧት
ሐ. መልሱ ብዙ ስለነበር እንዳይጠፋባት በመስጋት
መ. መልሱ አልተሠጠም

፬. ሰለሞን የሚኖረው የት አካባቢ ነው?

ሀ. ፒያሳ መሐሙድ ሙዚቃ ቤት አጠገብ
ለ. ስድስት ኪሎ አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ጀርባ
ሐ. አራት ኪሎ ከዳግማዊ ምኒልክ ት/ቤት ፊት ለፊት
መ. ስድስት ኪሎ ያሬድ ሙዚቃ ቤት ፊት ለፊት

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

**ማስታወሻ**

**የንግግር መመሪያ**

በመድረክ ላይ የሚቀርብ ንግግር የመድረክ ንግግር ሊባል ይችላል። በሚከተሉት መመሪያዎች መሰረት ይዘጋጃል፤ ለመድረክም ይቀርባል።

ሀ. የንግግር አዘገጃጀት

- የንግግር ርዕስ መምረጥ
- ንግግር ርዕስ መወሰን ወይም ማጥበብ
- የንግግሩን ዓላማ በግልጽ መረዳት
- የአድማጭን ማንነት መለየት
- ንግግር በሚደረግበት ርዕስ ላይ ሰፋ ያለ መረጃ ማሰባሰብ
- መረጃን የሚያመለክት ሀሳብ በአስተዋጽኦ መልክ ማዘጋጀት
- በመድረክ ላይ የሚቀርበውን ንግግር እንዴት እንደሚቀርብ መለማመድ

ለ. የንግግር አቀራረብ

- አድማጮችን በሚያረካ መንገድ ንግግር ማድረግ
- ንግግር በማቅረብ ሂደት ውስጥ የአድማጮችን ሁኔታ በመከታተልና የንግግሩ ሀሳብም ሆነ አቀራረቡ ማራኪ እንዲሆን ማድረግ
- በንግግሩ ማቅረብ ሂደት የመግቢያ እና የዝርዝር ሐሳብ እንዴት ያለ አቀራረብ ሊኖረው እንደሚገባ አስታውሶ መተግበር።

## መልመጃ አንድ

የአጭር ልቦለድ አላባውያንን በተመለከተ አምስት አባላት ያለው ቡድን በመመስረት ተወያዩ።

## መልመጃ ሁለት

“እውቀት ለመለወጥ” በሚል ርዕስ በየተራ ክፍል ውስጥ እየወጣችሁ ንግግር አድርጉ።

## መልመጃ ሰስት

ከዚህ ቀደም ካነበባችሁት ልቦለድ ታሪክ ወይም በሬዲዮና በቴሌቪዥን ከሰማችሁት ትረካ ውስጥ የምታስታውሱትን በየተራ እየወጣችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተርኩላቸው።

# ክፍል ሶስት፡- ማንበብ

## ቅድመ ንባብ

### ተግባር

፩. የአጭር ልቦለድን ምንነት አብራሩ፡፡

፪. የልቦለድ አለባውያን የሚባሉት ምን ምን ይመስሏችኋል?

፫. “መምሰልና መሆን” ከሚለውን የምንባብ ርዕስ በመነሳት ምንባቡ ስለምን የሚያወራ ይመስላችኋል?

## መምሰልና መሆን

ዛሬ የሴቶች ቀን የሚከበርበት ማርች 8 ነው፡፡ በዕለቱና በሰሞኑ ከጸጉር የበዙ ሴቶችን ስለማብቃትና ከጥቃት ስለመከላከል ብዙ ብዙ ነገሮች ይባላሉ፡፡ ጓደኛዬ መቅደስ ከነዚህ መድረኮች በብዙዎቹ እየተገኘች “ሴትን ልጅ ለማብቃት ቁልፉ ነገር ትምህርት ነው፡፡ ካልተማረች ምርጫ ታጣለች፡፡ በኢኮኖሚ ጥገኛ፣ ትሆናለች፡ ፡ ካልተማረች ሁሌም እስረኛ ነች፡፡ ዕድል አግኝታ ራሷን እንድትለውጥ ማገዝ ነው፡፡ ስለዚህ ደግሞ ሁላችንም የድርሻችንን ልንወጣ ይገባል፡፡” በማለት ያማረና የተዋጣለት ንግግር ታደርጋለች፡፡ እንደተለመደው ኮርቹባት ሳላበቃ ፕሮግራሙ አበቃና አዳራሹ በር ላይ ተገናኘን፡፡

“ተናገርሽው መቼም...! ደስ ይል ነበር” አልኳት፡፡ አጥብቄ ካቀፍኳትና ሞቅ አድርጌ ከሳምኳት በኋላ፡፡

“አመሰግናለሁ፤ አመሰግናለሁ... አወራሽ ነበር ግን መሮጥ አለብኝ...” አለችኝ ጥድፍ ጥድፍ እያለች፡፡

“ምነው ከመሸ ወዴት ነው የሚያሮጥሽ?” አልኳት ጥድፊያዋ ተጋብቶብኝ እኔም እየፈጠንኩ፡፡

“ገና ገብቼ እለፋለሁ ...እራት መስራት አለብኝ ...” ፊቷ ቅጭም አለ፡፡

“ምነው ሰራተኛ የለሽም እንዴ...?”

“የለኝም ባክሽ ኤዱ ...እነሱ መች ይቀመጣሉ...? በናትሽ እስኪ ከሰማሽ አፈላልጊልኝ... ስራ ውዬ ወደ ስራ ...መሞቴ ነው እኮ...” ሳቅ አልኩና “ውይ ጓደኛዬ ‹ድርብ ጭቆና› ገደለሽ አይደል? ...ከሰማሁ እነግርሻለሁ” ብያት ተለያየን፡፡

ተማሪዎች እስካሁን ከቀረበው የአጭር ልቦለዱ ታሪክ ምን ተረዳችሁ?

የዚህ አጭር ልቦለድ ታሪክ መጨረሻው ምን የሚሆን ይመስላችኋል?

ከሶስት ቀን በኋላ ስራ ስለምትፈልግ ልጅ ስሰማ ፈጠን ብየ ደወልኩላት፡፡ ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ፣

“ስሚ መቅዲ.... ሰው አላገኘሽም አይደል?” አልኳት፡፡

“ኧረ በጭራሽ ...በ´ናትሽ ኤደንዬ አገኘሽልኝ እንዴ...? ጉጉቷ ግልጽ ሆኖ ይሰማል፡፡

“ አዎ...”

“ምን አይነት?”

“አነስ ያለች ልጅ ናት፡፡ ...ገና መምጣቷ ነው አሉ ከክፍለ ሀገር፣ ...ምስኪን ...ታማኝ ልጅ ናት፡፡

“ወይኔ ታድዬ! ታማኝ ሰው እኮ ነው የቸገረን ዘንድሮ! መቼ ትመጣለች ታዲያ?”

“ነገ ወይ ከነገ ወዲያ፡፡ የዘመዷን ስልክ አሁኑኑ ቴክስት አደርግልሻለሁ... እዛ ነው ያለችው ተብያለሁ፡፡”

“ውይ ተመስገን ...! ምሳ አለብኝ የኔ ቅመም... ሀይለኛ ምሳ ነው የምጋብዝሽ፡፡”

“ችግር የለውም... በነገርሽ ላይ

“ እ...”

አቋርጣ ነው እንጂ “ሰባተኛ ክፍል ናት፡፡ ዘንድሮ ያው ...እዚህ ስትመጣ ትማራለች፡ ፡ የቤተሰብ ችግር ምናምን ነው እንጂ ጎበዝ ተማሪ ናት አሉ፣ መሸኛ አምጥታ ለሚቀጥለው ትመዘገባለች፡፡ እድለኛ ናት አንቺ ቤት ከገባች ብዙ ቦታ ልትደርስ ትችላለች፣ እሱን አስቤ ነው እኔም ቶሎ የደወልኩልሽ” አልኩኝ በተስፈኛ ድምጽ፡፡

“እ... ትማራለች?” ከድምጽዋ የደነገጠች መሰለኝ፡፡

“አዎ... ትማራለች...ትንሽ ልጅ እኮ ናት... እንዳልኩሽ አቋርጣ ነው... ምነው?”

“ኤጭ! በናትሽ እኔ መማር የምትፈልግ ሰራተኛ አልፈልግም፡፡ ...ሌላ ... ሌላ

...መማር የማትፈልግ ከሰማሽ ደውይልኝ በቃ ...አሁን ስራ ቢዚ ነኝ ... ቻው ...”

ከአስራ ሶስት አመታት ላለፈ ጊዜ በሴት ልጅ ትምህርት ዙሪያ ደከመኝ፣ ታከተኝ ሳትል ስትታትር የኖረችው የሴት ልጆች መብት ተሟጋች ወዳጄ ...፣ ለስንብት እንኳን እድል ሳትሰጠኝ ስልኩን ጆሮዬ ላይ ስትደረግመው ትዝ ያለኝ አንድ ነገር ብቻ ነው፣ “ማንኛዋንም ሴት የትምህርት እድል አግኝታ ራሷን እንድትለውጥ ማገዝ ያስፈልጋል:: ለዚህ ደግሞ ሁላችንም የድርሻችንን ልንወጣ ይገባል::” ብላ በአደባባይ የተናገረችው:: ወይ መምሰልና መሆን! ለካ መምሰል እንደ መሆን ቀላል አይደለም::

(ከሕይወት እምሻው፣ ፍቅፋቂ፣ 2010 ለማስተማሪያነት ተሻሽሎ የቀረበ)

## ድህረ ንባብ

### መልመጃ አንድ

የሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ “እውነት”፣ ስህተት ከሆኑ ደግሞ “ሀሰት” በማለት ከመለሳችሁ በኋላ ምክንያታችሁን በአጭሩ ግለፁ::

፩. ሴት ልጅን ማስተማር ህብረተሰብን ማስተማር ነው::

፪. ሴት ልጆችን ለማብቃት ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ ይገባል::

፫. በምንባቡ ውስጥ መቅደስ የተባለችው ገጸባህርይ የምታወራው እና የምትሰራው ነገር የተጣጣመ ነው::

፬. በምንባቡ መሰረት ድርብ ጭቆና የሚለው ሀሳብ ባለታሪኳ ያለባትን ጫና የሚገልጽ ነው::

፭. ሰዎች የቤት ሰራተኞቻቸውን ትምህርት ቤት መላክ የለባቸውም::

፮. የቤተሰብ ችግር ለልጆች ትምህርት እንቅፋት ሊሆን ይችላል::

፯. በምንባቡ ውስጥ የተጠቀሱት ገጸባህሪያት ሶስት ናቸው::

**ማስታወሻ**

**አጭር ልቦለድ**

አጭር ልቦለድ ከልቦለድ ዘውጎች ውስጥ አንዱ ሲሆን ከረጅም ልቦለድ የሚለይበት የራሱ የሆኑ ባህሪያት አሉት:: እነዚህ መሰረታዊ ባህሪያት ቁጥብነት፣ ጥድፊያና ነጠላ ውጤት ናቸው::

በሌላ መልኩ አጭር ልቦለድ ተሰናስለው የሚቆሙ ሰባት አላባውያን ያሉት ሲሆን በዚህ ክፍል እንመለከታቸዋለን፡፡

የልቦለድ አላባውያን፡- ሰባት አይነት የልቦለድ ዓላባውያን አሉ፡፡እነሱም፡-

፩. ታሪክ፡- በጊዜ /በቦታ/ ቅደም ተከተል የተደረደሩ ሁነቶች ትረካ ነው፡፡

፪. ገፀ ባህርይ፡-በልቦለድ ጽሁፍ ደራሲ ከልቡ አመንጭቶ የሚፈጥራቸው የገሀዱ ዓለም ሰዎች ወኪሎች ናቸው፡፡

፫. መቼት፡- "መቼ" እና "የት" ከተሰኙ ሁለት ቃላት የተመሰረተ ሲሆን የልቦለዱ ታሪክ የተፈፀመበትን ጊዜና ቦታ ያመለክታል፡፡

፬. ግጭት፡- አንዱ ገፀባህርይ ከሌላው ገፀባህርይ ጋር የሚፈጥረው እሰጣ ገባ ነው፡፡ ዋና ዋና የግጭት አይነቶች የሚባሉትሰው ከራሱ ጋር፣ ሰው ከተፈጥሮ ጋር፣ ሰው ከሰው ጋር፣ ሰው ከማህበረሰቡ ጋርእና ሰው ከዓምላኩ ጋር የሚያደርጓቸው ግጭቶች ናቸው፡፡

፭. ጭብጥ፡- በልቦለዱ ሊተላለፍ የተፈለገው መልዕክት ወይም ፍሬ ነገር ነው፡፡

፮. ትልም (ሴራ)፡-በምክንያትና ውጤት የተሳሰሩ ሁነቶች ወይም ድርጊቶች ቅደም ተከተል ነው፡፡

ምሳሌ፡- ውሻው ይጮሃል፤ህፃኑም ያለቅሳል፡፡----ታሪክ ሲሆን በውሻው መጮህ ምክንያት ህፃኑ ያለቅሳል፡፡ይህ ትልም/ሴራ/ ነው፡፡

፯. አንፃር፡- ደራሲው ታሪኩን የሚያቀርብበትን የትረካ አቅጣጫ የሚመለከት ነው፡፡ ይህም ታሪኩ የቀረበው በስንተኛ መደብ ነው? 1ኛ መደብ ወይም 3ኛ መደብ መሆኑን የሚመለከት ነው፡፡

## መልመጃ ሁለት

ቀጥሎ የቀረቡትን አረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ስህተት ከሆኑ ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡

፩. በአንድ አጭር ልቦለድ የአንድን ሰው ገጠመኝ ፈጠራዊ በሆነ መንገድ ማቅረብ ይቻላል፡፡

፪. የልቦለድ ገፀባህርያት የገሀዱ ዓለም ሰዎች ምስለኔዎች ናቸው፡፡

፫. አጭር ልቦለድ በባህርዩ መጠነሰፊ በመሆኑ ደራሲው ከአንድ በላይ ጭብጥ የማሳየት እድል ይኖረዋል፡፡

፬. የልቦለድ ታሪክ በመረጃ ሊረጋገጥ የሚችል መሆን ይኖርበታል፡፡

፭. ልቦለድ ተደራሲው እራሱን በታሪኩ ውስጥ እንዲፈትሽና ንቃተ ህሊናውን እንዲያዳብር የሚያስችል ነው፡፡

## መልመጃ ሶስት

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን በመምረጥ መልሱ፡፡**

፩. ከሚከተሉት ውስጥ የአጭር ልቦለድ ባህርይ ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ቁጥብነት ሐ. ጥድፊያ

ለ. ነጠላ ውጤት መ. መልሱ አልተሰጠም

፪. ከአጭር ልቦለድ አላባውያን መካከል የልቦለዱ ታሪክ የተፈፀመበትን ጊዜና ቦታ የሚያመለክተው አላባ የቱ ነው?

ሀ. ግጭት ለ. ሴራ ሐ. መቼት መ. ጭብጥ

፫. ከሚከተሉት አረፍተነገሮች መካከል ስለአጭር ልቦለድ ትክክል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. የአጭር ልቦለድ ገፀባህርያት በታሪኩ ውስጥ በርካታ ግጭቶች ይገጥሟቸዋል፡፡

ለ. አጭር ልቦለድ የደራሲውን ፍልስፍና ዘርዘር አድርጎ እንዲያቀርብ ያስችለዋል፡፡

ሐ. አጭር ልቦለድ የረጅም ልቦለድ አንድ ቅንጫቢ ሊሆን ይችላል፡፡

መ. የአጭር ልቦለድ ጭብጥ ነጠላ ወይም አንድ ነው፡፡

፬. ከሚከተሉት ውስጥ የምክንያትና ውጤትን ትስስር የሚያመለክተው የልቦለድ አላባ የትኛው ነው?

ሀ. ታሪክ ሐ. ትልም (ሴራ)

ለ. ግጭት መ. መቼት

፭. ከሚከተሉት ውስጥ ስለልቦለድ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ድርሰት የመፃፍ ፍላጎት ያለው ሁሉ የሚጽፈው ነው፡፡

ለ. በመረጃ የተደገፈ እንዲሆን አይጠበቅም

ሐ. የዕለት ተዕለት ገጠመኝን መነሻ በማድረግ የሚቀርብ የፈጠራ ጽሑፍ ነው፡፡

መ. ማስዋብ ወይም ማጋነን ይፈልጋል፡፡

## መልመጃ አራት

ለሚከተሉት ፈሊጣዊ አነጋገሮች ፍቺከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ስጡ፡፡

፩. ሀብቷ ቀና

ሀ. እድለኛ ሆነች    ሐ. ሀብታም ሆነች

ለ. ታጨች    መ. ገንዘብ አገኘች

፪. ጥራዝ ነጠቅ

ሀ. ግልብ    ሐ. ጥልቅ ትምህርት የሌለው

ለ. ያልተማረ    መ. ሁሉም

፫. የአዞ እንባ

ሀ. የለበጣ ሀዘን    ሐ. መከፋት

ለ. እውነተኛ ሀዘን    መ. ማልቀስ

፬. አይነ ልም

ሀ. ቆንጆ    ለ. ምቀኛ    ሐ. ተንኮለኛ    መ. የዋህ

፭. አገም ጠቀም

ሀ. ሁሉን መጥቀም    ሐ. ዓይንአፋር

ለ. ያዝ ለቀቅ    መ. ሄድ መጣ

## ክፍል አራት፡- መጻፍ

### ማስታወሻ

#### መሸጋገሪያ ቃላት (ሀረጋት)

የሀሳብ ተመሳሳይነት ያላቸውን አረፍተ ነገሮችና አንቀፆች በማያያዝ እንደድልድይ ሆኖ የሚያገለግል ቃል ወይም ሀረግ ነው፡፡ ከነዚህ ቃላትና ሀረጋት መካከልም የተወሰኑት፡ ከዚህም በላይ፣ ብሎም፣ ከዚህም በተጨማሪ፣ እንደዚሁም፣ በተመሳሳይም፣ ስለሆነም ፣ይሁን እንጂ፣ በተቃራኒው ግን፣ በአንፃሩምወዘተ. ናቸው፡፡

## መልመጃ አንድ

በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎች ከዚህ በታች ከቀረቡት መሸጋገሪያ ቃላት ወይም ሀረጋት መካከል በመምረጥ አሟልታችሁ ፃፉ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ከዚህ በማያያዝ | ከዚህ ቀጥሎ | በሌላ ጊዜ |
| በመቀጠል | እስከዚህ ድረስ | ወደፊት |

፩. ተጋባዡ እንግዳ መጻሕፍት የማንበብ ልምድን በሚመለከት ገለፃ አደረጉ፤------ስለሚያነቧቸው መጻሕፍት በራስ አባባል ማስታወሻ መያዝ ጠቃሚ እንደሆነ ተናገሩ፡፡

፪. እስካሁን ያለው የንባብ ልምዳችን ብዙ የሚያኮራን ላይሆን ይችላል፤--------ግን አስፈላጊነቱን ስለተረዳን ጠንክረን ልናሻሽለው እንችላለን፡፡

፫. የጤና ባለሙያው የኤች አይ ቪ ኤድስን የመተላለፊያ መንገዶች በሚመለከት ዋነኛ የሆኑትን በዝርዝር አቀረቡ፤-------------በዚህ ጉዳይ ላይም ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸውን ነጥቦች ለይተው ገለፃ በመስጠት ንግግራቸውን ጨረሱ፡፡

፬. ሁሉም ኢትዮጵያዊ የየድርሻውን በተሰማራበት ተግባር ለሀገሩ እድገት ማበርከት አለበት፤------------------የተሰሩት ስራዎች በቂ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡

፭. አጭር ልቦለድን በሚመለከት የአላባውያኑን ምንነት ተምረናል፤----------መሸጋገሪያ ቃላትን ወይም ሀረጋትን እንማራለን፡፡

## መልመጃ ሁለት

መሸጋገሪያ ቃላትን በመጠቀም "ታሪኬ" በሚል ርዕስ ባለ አራት አንቀጽ ተራኪ ድርሰት ፃፉና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

# ክፍል አምስት፡- ቃላት

### ማስታወሻ

**ያልተለመዱ ቃላት**

በዕለት ከዕለት የቋንቋ አጠቃቀማችን ውስጥ የማንገለገልባቸው አዳዲስ ወይም ኢ-ተዘውታሪ ቃላትን የሚመለከት ነው፡፡

**ምሳሌ፡-**

- መረን--------ባለጌ፣ ስድ
- ሌጣ---------ነጠላ፣ ብቸኛ
- ሎጤ-------ቀላዋጭ

## መልመጃ አንድ

በ "ሀ" ስር የቀረቡትን ኢ-ተዘውታሪ ቃላት በ "ለ" ስር ከቀረቡት ፍቺዎቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
| --- | --- |
| ፩. ለሆሳስ | ሀ. የአበባ ወቅት |
| ፪. ለበጣ | ለ. ድርስ እርጉዝ |
| ፫. ሙዋጥ | ሐ. ጌሾ ያልበዛበት ለጋ ጠጅ |
| ፬. ቆንዳላ | መ. ድምጽ አልባ፣ ሹክሹክታ |
| ፭. በተሀ | ሠ. አዘጋጀ፣ አሰናዳ |
| ፮. ወረግቡ | ረ. ሹሩባ |
| ፯. ከወነ | ሰ. የጀንያ መስፊያ መርፌ |
| | ሸ. ፌዝ፣ ሹፈት፣ ቀልድ |

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

### ማስታወሻ

**ሀረግ**

ሀረግ ከቃል የሰፋ ከአረፍተ ነገር ያነሰ፤ ቃላት እርስ በዕርስ በስርዓት በመቀናጀት የአንድ አረፍተነገር አካል ሆነው የሚፈጥሩት መዋቅር ነው፡፡

አንድ ሀረግ ምን አይነት ሀረግ እንደሆነ የሚወሰነውም በሀረጉ ውስጥ መሪ ሆኖ /ከሀረጉ በስተቀኝ/ የቀረበው ቃል በሚመደብበት የቃል ክፍል ነው፡፡

አንድ ሀረግ ምን አይነት ሀረግ እንደሆነ የሚወሰነውም በሀረጉ ውስጥ መሪ ሆኖ /ከሀረጉ በስተቀኝ/ የቀረበው ቃል በሚመደብበት የቃል ክፍል ነው፡፡

ከመስተዋድዳዊ ሀረግ ውጭ የሁሉም ሀረጎች መሪያቸው ቀኝ መሪ ነው፡፡

ሀረግ በዓይነቱ ስማዊ ሀረግ፣ ግሳዊ ሐረግ፣ ቅጽላዊ ሀረግ፣ ተውሳከ ግሳዊ ሀረግና መስተዋድዳዊ ሀረግ በመባል ይታወቃል፡፡

የሀረጉ መሪ ቃል፡-

ስም ከሆነ ----ሀረጉ ስማዊ ሐረግ

ግስ ከሆነ -------ሀረጉ ግሳዊ ሐረግ

ቅጽል ከሆነ ---- ሀረጉ ቅጽላዊ ሐረግ

ተውሳከ ግስ ከሆነ-----ሀረጉ ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ

መስተዋድድ ከሆነ----ሀረጉ መስተዋድዳዊ ሀረግ ይሆናል፡፡

**ምሳሌ፡-**

የብር ቀለበት-----ስ.ሀ

እጅግ በጣም ጎበዝ ------ቅ.ሀ

በድንገት መጣ፡፡----ግ.ሀ

ልጁ ክፉኛ---------ተ.ግ.ሀ

መስተዋድዳዊ ሀረግ ቀኝ መሪም ግራ መሪም መሆን ይችላል፡፡

**ምሳሌ፡-**

ወደ ቤት--- መ.ሀ

ከልጁ ጋር----መ.ሀ

## መልመጃ አንድ

በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ሀረጎች አይነት በምሳሌው መሰረት ጥቀሱ፡፡

**ምሳሌ፡-**

ዘይነባ አክስቷን ለመጠየቅ ወደ ዲላ ሄደች፡፡

ወደ ዲላ-----------መስተዋድዳዊ ሀረግ

ሁሉን ነገር በሆዱ የሚይዝ ሰው እራሱን ይጎዳል፡፡

ሁሉን ነገር በሆዱ ሚይዝ ሰው---------ስማዊ ሀረግ

፩. ልጁ ወደሆስፒታል ተወሰደ፡፡

፪. ኤርጎጌ በጣም ጎበዝ ተማሪ ናት፡፡

፫. የፈራረሱ ቤቶች በአዲስ መልክ እንደገና ተሰሩ፡፡

፬. ትናንት የታመመው ተማሪ ተሻለው፡፡

፭. ሄኖክ የእግር ኳስ ለመመልከት ስቴድየም ገባ፡፡

## መልመጃ ሁለት

የተለያዩ የሀረግ አይነቶችን ተጠቅማችሁ አምስት አረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

# ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ መሸጋገሪያ ቃላት (ሀረጋት) የሀሳብ ተመሳሳይነት ያላቸውን አረፍተ ነገሮችና አንቀፆች በማያያዝ እንደድልድይ ሆኖ የሚያገለግል ቃል ወይም ሀረግ እንደሆነ አይተናል፡፡

ያልተለመዱ ቃላት በዕለት ከዕለት የቋንቋ አጠቃቀማችን ውስጥ የማንገለገልባቸው አዳዲስ ወይም ኢ-ተዘውታሪ ቃላት መሆናቸውን ተረድተናል፡፡ በመጨረሻም ሐረግ ከቃል የሰፋ ከአረፍተ ነገር ያነሰ፣ ቃላት እርስ በእርስ በስርዓት በመቀናጀት የአንድ አረፍተ ነገር አካል ሆነው የሚፈጥሩት መዋቅር መሆኑን ተመልክተናል፡፡

# የክለሳ ጥያቄዎች

## መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ሀረጋት የሀረግ አይነት ለዩ፡፡

፩. የወርቅ ቀለበት

፪. እንደ ወንድሙ ክፉኛ

፫. ከእህቷ ጋር

፬. በጣም ቆንጆ

፭. ትምህርት ቤት መጣ፡፡

## መልመጃ ሁለት

ለሚከተሉት ቃላት መዝገበቃላዊ ፍቺ ስጡ፡፡

፩. ህዳግ

፪. ሀኬት

፫. ሙዳ

፬. ህፀጽ

፭. መግነጢስ

# ምዕራፍ አምስት

## ሥነ ህዝብ

### የሚጠበቁ ውጤቶች፣

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ፡-

- በአትኩሮት አዳምጣችሁ የጽሑፉን ይዘት ትገልጻላችሁ፤
- ስለ ህዝብ ብዛት ተጽዕኖ ታብራራላችሁ፤
- የህዝብ ብዛት በኢኮኖሚ ላይ የሚያሳድረውን ተጽእኖ ትተነትናላችሁ፤
- ተራኪ ጽሑፍ ትጽፋላችሁ፤

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### የህዝብ ቁጥር መጨመር እንደ መልካም አጋጣሚ







## ቅድመ ማዳመጥ

**ተግባር**

፩. የህዝብ ብዛት መኖር ለአንድ ሀገር ምንምን ጠቀሜታ ያለው ይመስላችኋል?

፪. የህዝብ ብዛትና የሀገር ሀብት ተመጣጣኝ ካልሆነ በሀገር ላይ ምን ጉዳት የሚያስከትል ይመስላችኋል?

፫. ርዕሱንና ስዕሉን ተመልክታችሁ ምንምን ጉዳዮች ይነሳሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ?

## ድህረ ማዳመጥ

### መልመጃ አንድ

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክለኛ መልስ በቃል ስጡ።

፩. የውጭ አገር ኩባንያዎችና የተለያዩ ሀገራት ባለሀብቶች መዋዕለ ንዋያቸውን በኢትዮጵያ ለማፍሰስ ፍላጎት እያሳዩ ያለው ለምንድን ነው?

፪. ከህዝብ ቁጥር መጨመር ጋር ተያይዞ ምን ምን ነገሮች ሊከሰቱ ይችላሉ?

፫. የህዝብ ቁጥር መጨመር እንደመርገም ሳይሆን እንደበረከት ሊቆጠር የሚችለው መቼ ነው?

፬. ለድህነት መባባስ በምክንያትነት የተጠቀሰው ምንድን ነው?

፭. የህዝብ ቁጥር እንዳይጨምር ከመስራት ይልቅ ምን ላይ ቢሰራ የተሻለ ይመስላችኋል?

### መልመጃ ሁለት

ለሚከተሉት ከምንባቡ የወጡ ቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ስጡ።

ሀ. መነመነ

ለ. ደለደለ

ሐ. በረከት

መ. ኮተኮተ

ሠ. ትኩረት

# ክፍል ሁለት፡- መናገር

## ማታወሻ

### ምክንያትና ውጤት

የአንድ ነገር ውጤት ከእሱ በፊት በሚኖር ምክንያት ወይም መንስኤ ላይ የተመሰረተ ነው። አንድ ምክንያት ብዙ ውጤት ሊያስመዘግብ ይችላል። ብዙ ምክንያቶቹም እንዲሁ አንድ ውጤት ሊያስመዘግቡ ይችላሉ።

ምሳሌ፡- የሜላት አባት መጠጥ እየጠጡ ከእናቷ ጋር ተጣልተዋል። ሜላትም በቤተሰቦቿ ፀብ ተበሳጭታ ትምህርቷን ሳታጠና ስለቀረች ፈተናውን ወደቀች።

ምክንያት ....... ውጤት

- የሜላት አባት መጠጥ መጠጣት
- የባልና የሚስት ፀብ
- የሜላት መበሳጨት
- የሜላት አለማጥናት
- የባልና ሚስት ፀብ
- የሜላት መበሳጨት
- ትምህርቷን አለማጥናት
- ፈተና መውደቅ

### ተግባር

በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ በመንስኤና ውጤት የተገለፁ ሀሳቦችን እየለያችሁ በቃል አስረዱ።

፩. ቋንቋ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ አደጋ ተናጋሪ ሲያጣ ይጠፋል።

፪. የሀይል እጥረት ለደኖች መመናመን ዋነኛ መንስኤ እየሆነ ነው።

፫. ረሂማ እናቷ ስለታመሙ አዘነች።

፬. የደኖች መጨፍጨፍ የአየር ንብረት መዛባትን አስከትሏል።

፭. ሳሙኤል ጠንክሮ በማጥናቱ አንደኛ ወጣ።

# ክፍል ሶስት፡- ማንበብ



## ቅድመ ንባብ

**ተግባር**

፩. የሥነ ህዝብ ፖሊሲ ማለት ምን ማለት ነው? ለምን የሚያስፈልግ ይመስላችኋል?

፪. የህዝብ ብዛታቸውን ለልማት የተጠቀሙ ሀገራትን ጥቀሱ?

፫. የህዝብ ብዛት በኢኮኖሚ ላይ ምን አይነት ተጽእኖ የሚያሳድር ይመስላችኋል?

፬. የቀረበውን ስዕል አይታችሁ የተረዳችሁትን ግለፁ፡፡

## የኢትዮጵያ የሥነ- ሕዝብ ፖሊሲ

በአገራችን ለሚታዩ ውስብስብ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች አንዱ ምክንያት ከኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እድገታችን ጋር ያልተመጣጠነ ፈጣን የህዝብ ቁጥር እድገት መኖር እንደሆነ ይታመናል፡፡ ለዚህ ደግሞ ዋነኛው መንስኤ ከፍተኛ የውልደት ምጣኔ መኖር ነው፡፡ ይህንን በመረዳት የኢትዮጵያ መንግስት በ1985 ዓ.ም የስነሕዝብ ፖሊሲ አውጥቶ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

የዚህ ፖሊሲ አጠቃላይ ዓላማ የሕዝብ ቁጥር እድገትና የኢኮኖሚ ልማት እድገትን በማጣጣም በአገሪቱ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት እንዲረጋገጥ ማስቻል ነው፡፡ ይህም ተግባራዊ የሚሆነው በሕዝቡ ሙሉ ፈቃደኝነትና ተሳትፎ ላይ በመመስረት ከፍተኛ የሆነውን የወሊድ መጠን ደረጃ በደረጃ በመቀነስ እና አዝጋሚ የሆኑትን የኢኮኖሚና ማህበራዊ የልማት ዘርፎችን ደግሞ አቅም በፈቀደ መጠን በፍጥነት በማሳደግ ይሆናል፡፡ የኢትዮጵያ የስነ ህዝብ ፖሊሲ አብይ ግብ "የሕዝብ ቁጥር እድገት ምጣኔን ከሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ልማትና ከተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ጋር እንዲጣጣም በማድረግ ከረጅም ጊዜ አኳያ የህዝቡ የኑሮ ደረጃና አጠቃላይ ደህንነት እንዲሻሻል ማድረግ ነው፡፡"

የኢትዮጵያ የስነሕዝብ ፖሊሲ አጠቃላይ አላማዎችም፡- የኢኮኖሚ ግንባታውን በማጠናከርና የህዝብ ቁጥር እድገት ምጣኔን በዕቅድ በመቀነስ በሕዝብ ቁጥር እድገትና በዝቅተኛ ኢኮኖሚ መካከል ያለውን ልዩነት ማስወገድ፤ በተቀናጁ የልማት ፕሮግራሞች አማካኝነት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴውን ማስፋፋትና የስራ እድል እንዲፈጠር ማድረግ፤ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማትን ማፋጠን፤ ከገጠር ወደከተማ የሚደረገውን የሕዝብ ፍልሰት መጠን መቀነስ፤ የአካባቢ ጥበቃንና እንክብካቤን የሚያጠናክሩ ተገቢ እርምጃዎችን በመውሰድ በተለይ የገጠሩ አካባቢ ሰዎችን የማኖር አቅም እንዲጠበቅ ወይም እንዲሻሻል ማድረግ፤ ሴቶችን ከባህላዊ ተጽዕኖዎች፣ ከከባድና አሰልቺ ስራዎች በማላቀቅና ማህበረሰቡ ውስጥ ምርታማ ሆነው እንዲሳተፉ በማድረግ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ደረጃቸውን ከፍ ማድረግ፤ በቀላሉ በአደጋ ሊጠቁ የሚችሉትን ማለትም የህፃናትን፣ የወጣቶችን፣ የሴቶችንና የአረጋውያንን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ማሻሻል ናቸው፡፡ እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የህዝብ ልማት ወይም ማህበረ ኢኮኖሚያዊ እድገት ወሳኝ ነው፡፡ በዕውቀት፣ በአመለካከትና በክህሎት አቅሙ የጎለበተ ሕዝብ ለአገር እድገት ወሳኝ ግብዓት ሲሆን በአንፃሩ ደግሞ አቅሙ ያልጎለበተ ሕዝብ የልማት ፈተና መሆኑ እሙን ነው፡፡

የሥነ ህዝብ ፖሊሲ ዓላማዎች ተብለው የተገለፁት ምን ምን ናቸው?

የሀገር ልማት ሲታሰብ ምን ምን ነገሮች ላይ ትኩረት ማድረግ የሚያስፈልግ ይመስላችኋል?

በመሆኑም ልማት ሲታሰብ ቅድሚያየህዝቡን አሰፋፈር ሁኔታ ማለትም ብዛቱን፣ ዓመታዊ የዕድገት ምጣኔውን፣ መልክዓ ምድራዊ ስርጭቱን እና የፆታና የዕድሜ ስብጥሩን እንዲሁም የውልደት፣ የሞትና የፍልሰት ምጣኔውን በሚገባ ማጤንና

ከማህበራዊ፣ ከኢኮኖሚያዊ እና ከአካባቢያዊ ጉዳዮች ጋር ያላቸውን ትስስር መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የስነህዝብ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ያላስገቡ የልማት እንቅስቃሴዎች ዘላቂና አስተማማኝ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ በአንድ አገር ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ስልቶች ውስጥ የስነህዝብ ጉዳዮችን ማካተት ዘላቂ ልማትን ለማምጣትና ድህነትን ለመቀነስ በሚደረገው ጥረት ወሳኝ መሆኑን ያሳያል፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት በስነህዝብና ልማት መካከል ያለውን ትስስር ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የስነሕዝብ ፖሊሲ አውጥቶ በስራ ላይ እንዲውል አደርጓል፡፡ የስነሕዝብ ጉዳዮች ተግባራት ደግሞ ዘርፈ ብዙ በመሆናቸው በአንድ በተወሰነ ተቋም ጥረት ብቻ የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት የሚቻል አይደለም፡፡ በመሆኑም ሌሎች ተቋማትና ባለድርሻ አካላት በተቀናጀ እና በተጠናከረ መልኩ የስነሕዝብ ጉዳዮችን በየእቅዶቻቸው እንዲካተት ተደርጎ መስራት ይገባል፡፡

(ከአብክመ ፕላን ኮሚሽን የሥነ ህዝብና ልማት ቅንጅት ዳይሬክቶሬት፣ ታህሳስ 2012 ዓ.ም፣ ለማስተማሪያነት ተሻሽሎ የቀረበ)

## ድህረ ንባብ

### መልመጃ አንድ

የሚከተሉት አረፍተ ነገሮች በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆኑ "እውነት" ስህተት ከሆኑ "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡

፩. የሀገራችን የህዝብ ቁጥር እድገት ከኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገታችን ጋር የተጣጣመ ነው፡፡

፪. ከኢትዮጵያ የስነ ህዝብ ፖሊሲ ዓላማዎች ውስጥ አንዱ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገውን ፍልሰት መቀነስ ነው፡፡

፫. ከፍተኛ የሆነ የወሊድ መጠን መጨመር ለህዝብ ቁጥር እድገት ምንም አስተዋጽኦ የለውም፡፡

፬. ልማት ሲታሰብ የህዝብን ዲሞግራፊያዊ ባህርያት በሚገባ ማጤን ያስፈልጋል፡

፭. የስነሕዝብ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ያላስገቡ የልማት እንቅስቃሴዎች ዘላቂ እና አስተማማኝ ሊሆኑ አይችሉም፡፡

### መልመጃ ሁለት

ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን በመምረጥ መልሱ፡፡

፩. በምንባቡ አንቀጽ አንድ ውስጥ በአገራችን ለሚታዩ ውስብስብ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ምክንያት ተብሎ የተጠቀሰው ምንድን ነው?

ሀ. የህዝብ ቁጥር እድገት | ሐ. የውልደት ምጣኔ
ለ. የልማት ፖሊሲ | መ. የሀብት ብክነት

፪. በምንባቡ መሰረት የኢትዮጵያ መንግስት ያወጣው ፖሊሲ የትኛው ነው?

ሀ. የትምህርት ፖሊሲ | ሐ. የስነህዝብ ፖሊሲ
ለ. የጤና ፖሊሲ | መ. የግብርና ፖሊሲ

፫. የኢትዮጵያ የሥነሕዝብ ፖሊሲ አብይ ግብ ምን እንደሆነ የተገለፀው በየትኛው አንቀጽ ነው?

ሀ. በአንቀጽ አንድ | ሐ. በአንቀጽ አራት
ለ. በአንቀጽ ሁለት | መ. በአንቀጽ ሶስት

፬. በአንቀጽ ሶስት ላይ የአገር እድገት ወሳኝ ግብዓት ይሆናል ተብሎ የተገለፀው በምን የጎለበተ ህዝብ ነው?

ሀ. በዕውቀት | ሐ. በክህሎት
ለ. በአመለካከት | መ. ሁሉም

፭. በምንባቡ መሰረት የስነህዝብ ሁኔታዎችን ከግምት ያላስገባ ምንድን ነው ዘላቂ እና አስተማማኝ ሊሆን አይችልም የተባለው?

ሀ. ጥረት | ሐ. ልማት
ለ. ውልደት | መ. ብዛት

## መልመጃ ሶስት

በምሳሌው መሰረት ከምንባቡ የምክንያትና ውጤት ትስስር ያላቸውን አምስት አረፍተ ነገሮች አውጥታችሁ አመልክቱ።

ምሳሌ፡-

> ያልተጣጣመ ፈጣን የህዝብ ቁጥር እድገት መኖር ምክንያቱ ከፍተኛ የውልደት ምጣኔ ነው።

ምክንያት፡- ያልተጣጣመ ፈጣን የህዝብ ቁጥር እድገት

ውጤት፡- ከፍተኛ የውልደት ምጣኔ

## ክፍል አራት፡- መጻፍ

### ማታወሻ

#### ምክንያትና ውጤት

በጣም ከተለመዱት አራት ዋና ዋና የድርሰት አይነቶች ውስጥ አንዱ ሲሆን በጊዜ ቅደም ተከተል ስላለፈ ድርጊት የሚተርክ ወይም የሚያትት ጽሁፍ ተራኪ ድርሰት ተብሎ ይጠራል፡፡ ተራኪ ድርሰት የሁነቶችን የድርጊት ቅደም ተከተል ጠብቆ እንዲህ ሆነ፣ እንዲህ ተደረገ---እያለ የሚተርክ ጽሁፍ ነው፡፡ ታሪኩን የሚነግረን እራሱ የድርጊቱ ተካፋይ ወይም ተመልካች ሊሆን ይችላል፡፡

ምሳሌ፡- አቶ ጨምቡሮ ከአባታቸው ከአቶ ኡርካቶ ጨፋ እና ከእናታቸው ከወ/ሮ ኡፋይሴ ሎአ ሶዶ ከተማ ታህሳስ 12/1984 ዓ.ም ተወለዱ፡፡ እድሜያቸው ለአቅመ ትምህርት ሲደርስ በአካባቢያቸው ከሚገኘው ቦጋለ ዋለሉ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ገብተው ትምህርታቸውን ተከታተሉ፡፡ ከዚያም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በሊጋባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተምረዋል፡፡

### መልመጃ አንድ

አንድ የምታውቁትን ታዋቂ ሰው የሕይወት ታሪክ በአምስት አንቀጽ ፃፉ፡፡

### መልመጃ ሁለት

የራሳችሁን የሕይወት ታሪክ በሶስት አንቀጽ በመፃፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### ማታወሻ

#### የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ

አንዳንድ የአማርኛ ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ አላቸው፡፡

**እማሬያዊ ፍቺ:-** የቃላት ቀጥተኛ ወይም መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ነው፡፡ የቃላት የተለመደ ወይም የተዘወተረ ትርጉም ነው፡፡ ቃላቱ ሲነገሩ ወደ አዕምሯችን በፍጥነት የሚመጣው ፍቺ ነው፡፡

**ፍካሬያዊ ፍቺ:-** ከዕማሬያዊ ፍቹ በተደራቢነት የምናገኘው ፍቺ ነው፡፡ ከቀጥተኛ ፍችው ባሻገር የምናገኘው ትርጉም ነው፡፡ የቃላት ድብቅ ወይም ስውር ፍቺ ነው፡፡

ምሳሌ፡- ቤት

እማሬያዊ ፍቺ---ጣራና ግድግዳ ያለው የሰው ልጅ መኖሪያ

ፍካሬያዊ ፍቺ---ትዳር፣ የሰው ልጅ ጠቅላላ ኑሮ

## መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ በሰንጠረዡ ውስጥ በቀረበው ምሳሌ መሰረት አስቀምጡ፡፡

| ቃል | እማሬያዊ ፍቺ | ፍካሬያዊ ፍቺ |
|---|---|---|
| ንብ | ማር አምራች በራሪ ፍጡር | ታታሪ፣ ትጉህ፣ ሰራተኛ |
| ዱባ | | |
| ቋንጣ | | |
| አንበሳ | | |
| ተልባ | | |
| እንጀራ | | |

# ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

## ማታወሻ

### ገቢርና ተገብሮ ግሶች

ገቢር ግሶች አንድ ሰው የሚፈጽመውን ድርጊት (ተግባር) የሚገልፁ ናቸው፡፡

አምዱ ምንም አይነት ቅጥያ የማይጨመርበት ሲሆን የተፈፀመ ድርጊትን የሚጠቁም በመሆኑ ሃላፊ አምድ ነው፡፡

ምሳሌ፡- ነገረ፣ ሰበረ፣ በጠሰ፣ ለወጠ፣ ቀደደ ወዘተ.

በእምነት መስኮት ሰበረ፡፡

ሰፊው ልብስ ቀደደ፡፡

በጉ የታሰረበትን ገመድ በጠሰ፡፡

ተገብሮ ግሶች፡- የእርስ በርስ ድርጊትን የሚያመለክት ሲሆን ገቢር አምድ ላይ በምትቀጠል (ተ-) ምዕላድ የሚፈጠር አምድ ነው፡፡ አምዱ አንድ የተፈፀመ ድርጊት የተፈፀመበትን ነገር የሚጠቁም ነው፡፡

ምሳሌ፡- ተነገረ፣ ተሰበረ፣ ተበጠሰ፣ ተለወጠ፣ ተቀደደ ወዘተ.

መስኮቱ በኤፍሬም ተሰበረ፡፡

ገመዱ በበጉ ተበጠሰ፡፡

ልብሱ በሰፊው ተቀደደ፡፡

## ተግባር

የሚከተሉትን ቃላት ተጠቅማችሁ ገቢርና ተገብሮ አረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

፩. ገደለ
ተገደለ

፪. ወደደ
ተወደደ

፫. ለበሰ
ተለበሰ

፬. ቀመሰ
ተቀመሰ

፭. ጠበሰ
ተጠበሰ

፮. ጨረሰ
ተጨረሰ

፯. ፈለገ
ተፈለገ

# ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ስላለፈ ድርጊት የሚተርክ ወይም የሚያትት ጽሑፍ ተራኪ ድርሰት ተብሎ እንደሚጠራ አይተናል። በተጨማሪም የቃላት እማሬያዊ ፍቺማለት የቃላት የተለመደ ወይም የተዘወተረ ትርጉም እንደሆነና ፍካሬያዊ ፍቺማለት ደግሞ የቃላት ድብቅ ወይም ስውር ፍቺ መሆኑን ተረድተናል።

በመጨረሻም ገቢር ግሶች አንድ ሰው የሚፈጽመውን ድርጊት ወይም ተግባር የሚገልፁ ሲሆኑ፣ ተገብሮ ግሶች ደግሞ ገቢር አምድ ላይ በምትቀጠል (ተ-) ምዕላድ የሚፈጠር አምድ መሆናቸውንተመልክተናል።

# የክለሳ ጥያቄዎች

## መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን አረፍተነገሮች ገቢርና ተገብሮ አረፍተነገር እያላችሁ ለዩ።

፩. ቡሎ እንሰት ተከለ።

፪. እንሰቱ በቡሎ ተተከለ።

፫. ሔኖክ እስክርቢቶ ደበቀ።

፬. እስክርቢቶው በሔኖክ ተደበቀ።

## መልመጃ ሁለት

የሚከተሉትን ግሶች ተጠቅማችሁ ገቢርና ተገብሮ አረፍተነገሮችን ስሩ።

፩. ደረበ ፪. ተደረበ ፫. ከፈለ ፬. ተከፈለ

## መልመጃ ሶስት

የሚከተሉትን ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺበአረፍተ ነገር አሳዩ።

፩. ፍየል ፪. ቆቅ ፫. በግ

# ምዕራፍ ስድስት

## በረሃማነት

### የሚጠበቁ ውጤቶች፣

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ፡-

- አዳምጣችሁ እየተነተናችሁ ትመዝናላችሁ፤
- የበረሃማነትን መንስዔ ትገልፃላችሁ፤
- በረሃማነት የሚያሳድረውን ተጽዕኖ ታብራራላችሁ፤
- የተሰጣችሁንጽሑፍ በማንበብ ማጠቃለያ ትሰጣላችሁ፤

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### የምድራችን ጀግና



## ቅድመ ማዳመጥ

### ተግባር

፩. በረሃማነት ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?
፪. እጽዋትንና የሰውን ልጅ ሕይወት የሚያገናኛቸው ምን ይመስላችኋል?
፫. በረሃማነትን ለመከላከል ምን ምን ተግባራት ይከናወናሉ?

## ድህረ ማዳመጥ

### መልመጃ አንድ

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክለኛ መልስ ስጡ፡፡

፩. በአሁኑ ሰዓት በብዝኃ ሕይወት አጠባበቅ ላይ እየተሰራ ያለውን ስራ እንዴት ታዩታላችሁ?
፪. ዶክተር ተወልደ የምድራችን ጀግና የሚል ስያሜን ያገኙት ምን ስለሰሩ ነው?
፫. የቻይናና በኢኮኖሚ የበለፀጉ ሀገሮች የማደግ ምስጢር ምንድን ነው?
፬. ዶክተር ተወልደ አፍሪካን ወክለው ንግግር ያደረጉት በየትኛው ጉባኤ ነው?
፭. የዕጽዋት ስያሜ ፕሮጀክት ተግባራዊ እንዲሆን ዶክተር ተወልደ ምን ሰሩ?
፮. የምንባቡን አጠቃላይ ሀሳብ ምን እንደሆነ በቃል ተናገሩ፡፡

### መልመጃ ሁለት

የምድራችን ጀግና በሚል ርዕስ ከቀረበላችሁ ምንባብ ለወጡ ቃላት ዐውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡

ሀ. ምድረ በዳ
ለ. ቀናዒነት
ሐ. ረባዳ
መ. ተበተበ
ሠ. ፊር

# ክፍል ሁለት፡- መናገር

## ማስታወሻ

### ውይይት

ውይይት አላማ ያለው ጊዜና ቦታ ተወስኖለት አንድና ከአንድ በላይ በሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ሰዎች ሀሳባቸውን የሚለዋወጡበትና ከጋራ መግባባት ላይ የሚደርሱበት ተግባር ነው፡፡ ውይይት ለማከናወን ውይይት በሚደረግበት ጽንሰ ሀሳብ ዙሪያ በሚገባ መዘጋጀት በመጨረሻ ለሚጠበቀው ውጤት እውን መሆን የራሱ የሆኑ አስተዋጽኦዎች ይኖሩታል፡፡

- የውይይት ዝግጅት
- የመወያያ ርእሰ ጉዳይ መምረጥ
- ርዕሰ ጉዳዩን በሚገባ መረዳት
- ርዕሰ ጉዳዩን በተመለከተ ትክክለኛ መረጃ መሰብሰብ
- በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ ዋና ዋና ነጥቦችን መለየት
- በየትኛውም ጉዳይ የተሰበሰቡትን መረጃዎች ታዳሚዎችን የሚመጥን መሆኑን ማረጋገጥ
- ፍሬ ሀሳቦችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥና በቂ ዝግጅት ማድረግ
- የውይይት አቀራረብ
- አለባበስንና ንጽህናን ጠብቆ መገኘት
- የመወያያ ርዕሰ ጉዳዮችን ማስተዋወቅ
- ተራን ጠብቆ መናገር፣
- የሌሎችን ሀሳብ ማክበር፣
- ያልተንዛዛና የተመጠነ ሀሳብን በቅደም ተከተል ማቅረብ
- ሲናገሩ ድምጽን መመጠን፣
- ፍርሃትና ግድየለሽነትን ማስወገድ
- ፍሬ ሀሳቦችን በምሳሌና ማስረጃ ማስደገፍ
- ተገቢ አገላለጽ ስልት መከተልና አንደበትን ማስላት
- ከታዳሚዎች የሚመጡ አስተያየቶችንና ጥያቄዎችን መቀበል
- የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በአግባቡ አዳምጦ ምላሽ መስጠት

### ተግባር

ከዚህ በታች በቀረቡላችሁ አንቀፆች ላይ ተወያይታችሁ የተረዳችሁትን ሀሳብ በተወካያችሁ አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ።

---ደራሲነት ከባድ ስራ ነው፤ ሰው የሚመስሉ ገፀባህርያት ለመፍጠር ሰውን ማጥናት፣ ሰውን በውል መረዳት፣ ተፈጥሮንና ማህበረሰቡን ማወቅ ያስፈልጋል። እውነተኛ ደራሲ ማህበረሰቡ ሲጨነቅ የሚጨነቅ፣ ሲያዝን የሚያዝን፣ ሲፈነድቅ ደግሞ አብሮ የሚፈነድቅ፣ የሰው ልጅ ፍቅር ያለው ለየት ያለ ፍጡር ነው---።


(ዘሪሁን አስፋው፣ 1998 ዓ.ም፣ ገጽ 58 ያልታተመ)

---ትክክለኛ የወግ ፀሀፊ ገና ብዕሩን ሲጨብጥ የቃላት ዓይነቶች ከነምስላቸው ይኸጎደጎዱለታል። ዓላማው በምናቡ አግዝፎ የሚያየውን ጉዳይ በጥሩ አቀራረብ አቀናጅቶ ወረቀት ላይ መቅረጽ ነው። ርዕሱ ወደሚመራው አቅጣጫ ትንሽ፣ ትልቅ ሳይል በነፃ መንፈስ፣ በምናባዊ እይታው ጭልጥ ብሎ ይነጉዳል----።

(መስፍን ሀ/ማርያም፣ 1992፣ ገጽ 6)

## ክፍል ሶስት ፡- ማንበብ

### ተፈጥሮን የመመለስ ስራ







## ቅድመ ንባብ

**ተግባር**

፩. በረሃማነት የሚያሳድረው ተጽዕኖ ምንድን ነው?

፪. ተፈጥሮን በመንከባከብ በረሃማነትን እንዴት መከላከል የሚቻል ይመስላችኋል?

፫. የቀረበውን ስዕል አይታችሁ የተረዳችሁትን ግለፁ፡፡

## ተፈጥሮን የመመለስ ስራ

በሀገራችን የሚካሄደው የተፈጥሮ ጥበቃ ስራ ብዙ ርቀት መሄድ ያለበት በመሆኑ ለረዥም አመታት በተከታታይ ሳይቋረጡ የተሰሩት ስራዎች ከፍተኛ ለውጥና ውጤት አስገኝተዋል፡፡ ድርቅንና የተፈጥሮ አየር መዛባትን በዘላቂነት ለመከላከልና ለመመከት የሚቻልበት ብቸኛው መፍትሔም የተፈጥሮ ጥበቃ ስራን አጠናክሮ መቀጠል ነው፡፡ በመሰረቱ ለድርቅና ለረሀብ፣ እንዲሁም ለተለያዩ ተፈጥሮአዊ አደጋዎች መከሰት ዋናው ተጠያቂ የሰው ልጅ ነው፡፡ ጫካዎችንና ደኖችን ከመመንጠር ጀምሮ መሬቶችን በማራቆት ወደ በረሀማነት እንዲለወጡ ከማድረጉ ባለፈ ከኢንዱስትሪዎች የሚለቀቀው በካይ የኬሚካል ጋዝ በአየር ንብረት ላይ ይህ ቀረው የማይባል መዛባትና አደጋ እንዲከሰት ምክንያት ሆኗል፡፡ በዚህ የተነሳም ታዳጊ ሀገራት ከበለጸጉና ካደጉ ሀገራት ጋር በአለም ላይ እየተከሰተ ስላለው የአየር ንብረት መዛባትና እሱን ተከትሎ ስለመጣው የሰው ልጅ የከፋ አደጋ ምክክርና ድርድር ውስጥ ገብተዋል፡፡

በእኛ ሀገርም የነበረው የደን ሽፋን ተመናምኖ እና መሬቱ ወደ በረሀማነት ተለውጦ እያስከተለ ያለው ችግር በቀላሉ የሚፈታ መሆን አልቻለም፡፡ በደኖች መመንጠርና

መመናመን ምክንያት የዱር አራዊት፣ እንስሳትና አዕዋፋት ጭምር መኖሪያቸውን ለቀው ወደ ጎረቤት ሀገራት ተሰደዋል፤ ከየተራራው ስር ይፈልቁ የነበሩትና ትውልድን ያጠግቡ የነበሩት ምንጮች ደርቀዋል፤ ሰብል ዘርቶ ለማብቀል አዳጋች ሆኗል። ይህ ደግሞ የአየር ንብረት መዛባት ከፈጠረው አደገኛ ችግር ጋር የተያያዘና የተቆራኘ ነው። ይህንን የአየር ንብረት መዛባት ችግር ዘለቄታዊ በሆነ መንገድ መቅረፍ የሚቻለው የተፈጥሮ ጥበቃ ስራን አጎልብቶ በመስራት ብቻ ነው።

ለድርቅና ለረሀብ ዋነኛው ተጠያቂ የሰው ልጅ ነው የተባለው ለምንድን ነው?

ተፈጥሮ ወደ ነበረችበት እንድትመለስ የሰው ልጅ ምን ምን ነገሮችን መስራት የሚኖርበት ይመስላችኋል?

ተፈጥሮ በራሷ መንገድ ከምትፈጥረው ጫና ውጪ በአብዛኛው ለድርቅና ለረሀብ ምክንያቱ የሰው ልጅ በራሱ የሚፈጥረው ችግር ነው። በተለይም ከበካይ የከባድ ኢንዱስትሪዎች ጭስ ልቀት ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ ችግሮች ሰፊ ናቸው። ይህንን ለመከላከል የሚቻለውም ጥንት ወደ ነበረችበት አረንጓዴነት ለመመለስ በመስራትና በመንከባከብ ብቻ ነው።

"በሀገራችን በሁሉም ክልሎች በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠረውን ሕዝብ በማስተባበርና በማሰማራት ሰፊና ግዙፍ የተፈጥሮ ጥበቃ ስራ እየተሰራ ይገኛል። በዚህም ምክንያት የተራቆቱ መሬቶችን እንዲያገግሙ እና ወደ ቀድሞ ገጽታቸው እንዲመለሱ ጥረት እየተደረገ ነው። ይሄው የተፈጥሮ ጥበቃ ስራ በአዲስ አበባ፤ በአማራ፤ በኦሮሚያ፤ በትግራይ፤ በደቡብ፤ በአፋር፣ በቤኒሻንጉልና በሌሎችም ክልሎች ጭምር በስፋት እየተሰራ ይገኛል። የአፈር መሸርሸርን ለመግታት የእርከን ስራ፤ የችግኝ ተከላ፤ የመስኖ ልማት ስራዎች ሁሉ እየተሰሩ ነው።

በሀገራችን አርሶ አደሩንና አርብቶ አደሩን የዕለታዊ የአየር ንብረት ትንበያዎች ተጠቃሚ እንዲሆን ማስተማርና ማሳወቅ ሊፈጠር ከሚችለው የአየር ንብረት አደጋ ግንዛቤ እንዲያገኝና እንዲጠነቀቅ ያስችለዋል። የተፈጥሮ ኃብት ልማት ስራዎች በመላው ሀገሪቱ በስፋትና በጥልቀት መካሄድ ከጀመሩበት ግዜ ጀምሮ የተራቆቱ ተራሮችና መሬቶች ወደ ቀደመው መልካቸው እየተመለሱ ይገኛሉ፤ ጠፍተው የነበሩ እጽዋት ተመልሰው በመብቀል ላይ ሲገኙ፤ ተሰውረው የነበሩ አዕዋፋትና የዱርእንስሳትም ወደ ቦታቸው መመለስ ይዘዋል። ይህ ደግሞ ትልቅ ለውጥና ስኬት ነው።

(ከዋልታ ቲቪ፤ ሚያዝያ 25/2009 ዓ.ም፤ ለማስተማሪያነት ተሻሽሎ የተወሰደ)

## ድህረ ንባብ

### መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆኑ "እውነት"፣ ስህተት ከሆኑ "ሀሰት" በማለት መልሱ።

፩. የተፈጥሮ ጥበቃ ስራን በተመለከተ የተሰሩ ስራዎች ከፍተኛ ለውጥና ውጤት አስገኝተዋል፡

፪. ለድርቅ፣ ለረሀብና ለተለያዩ የተፈጥሮ አደጋዎች መከሰት ዋናው ተጠያቂ የሰው ልጅ ነው።

፫. በሀገራችን ምንም እንኳ የደኖች መመንጠርና መመናመን የነበረ ቢሆንም የዱር አራዊቱ፣ እንስሳቱና አዕዋፋቱ ቦታ እንዲቀይሩ አላስገደዳቸውም።

፬. የአየር ንብረት መዛባት ችግርን ዘለቄታዊ በሆነ መንገድ መቅረፍ የሚቻለው የተፈጥሮ ጥበቃ ስራን አጎልብቶ በመስራት ብቻ ነው።

፭. በሀገራችን በሁሉም አካባቢዎች የተፈጥሮ ጥበቃ ስራ ተጠናክሮ እንደቀጠለ ነው።

### መልመጃ ሁለት

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ በቃል ስጡ።

፩. የሰው ልጅ በተፈጥሮ ላይ የሚያደርሳቸው ጥፋቶች ምን ምን ናቸው?

፪. ድርቅንና የተፈጥሮ አየር መዛባትን በዘላቂነት ለመከላከል ምን መደረግ አለበት?

፫. ምድርን ቀድሞ ወደነበረችበት አረንጓዴነት መመለስ ሲባል ምን ማለት ነው?

፬. "በረሃማነት" የሚለውን ምንባብ በራሳችሁ አባባል በአንድ አንቀጽ አሳጥራችሁ ፃፉት።

## ክፍል አራት፡- መጻፍ

**ማስታወሻ**

**ገላጭ ድርሰት**

ገላጭ ወይም አስረጅ ድርሰት አንድ ነገር አሰራር፣ አፈፃፀም፣ ምንነት፣ ባህርያት፣ ቅርጽ፣ አይነት፣ መጠን፣ አገኛኘት፣ ጠቀሜታ ወይም ጉዳት ወዘተ. ለማብራራት የሚፃፍ የድርሰት አይነት ነው።

ምሳሌ አንድ፡- በእስልምና ሀይማኖት በደማቅ ሁኔታ ከሚከበሩ በዓላት መካከል የኢድ-አል አድሃ(አረፋ) በዓል አንዱ ነው። በዓሉ የእርድ ወይም የመስዋዕትነት በዓል በመባል ይታወቃል። ይህ ክብረ በዓል የሚከበረው በኢስላማዊ ዘመን አቆጣጠር በአስራ ሁለተኛው ወር ዙልሂጃ ላይ ነው። ለበዓሉ የሚታረደው ስጋ አንድ ሶስተኛው በቀጥታ ለድሆች የሚከፋፈል ሲሆን ሌላኛው አንድ ሶስተኛ ደግሞ ለዘመድና ለወዳጅ የሚሰጥ ይሆናል። ቀሪው አንድ ሶስተኛ ግን ለቤተሰብ አገልግሎት የሚውል ይሆናል።

**ምሳሌ ሁለት፡- የዶሮ ወጥ አሰራር**

የዶሮ ወጥ ለመስራት መጀመሪያ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችንና ቅመሞችን እናዘጋጃለን። እነዚህ ግብዓቶችም፡- ሽንኩርት፣ የተበለተ የዶሮ ስጋ፣ ዘይት፣ ጨው፣ የሀበሻ ቅቤ፣ ጥቁር ቅመም፣ መከለሻ፣ የተቀቀለ እንቁላልና እንደየሰው ፍላጎት ሌሎች ቅመማ ቅመሞችም ይገባሉ። አሰራሩን በተመለከተ በመጀመሪያ ሽንኩርቱ ተልጦ ይከተፋል። በመቀጠልም ተለቅ ባለ ሸክላ ድስት ወይም ብረት ድስት ተጥዶ በደንብ ይበስላል። ሽንኩርቱ በሚገባ ከበሰለ በኋላ ዘይት ወይም ቅቤ እና በርበሬ እንደየቀደም ተከተሉ በማስገባት በደንብ ይቁላላል። ሽንኩርቱ ከበርበሬው ጋር እየተቁላላ የተበለተው ዶሮ ስጋ በሎሚና በጨው ተዘፍዝፎ በደንብ ይታጠባል። ቁሌቱ ላይ ጥቁር ቅመም ይገባል። ስጋው በንፁህ ውሃ በደንብ ከተለቀለቀ በኋላ በቢላዋ ምልክት እየተደረገበት ቁሌቱ ውስጥ ይጨመራል። የዶሮው ስጋ እስኪበስል የተቀቀለውን እንቁላል በመላጥ እናዘጋጀዋለን። ስጋው ትንሽ በሰል ሲል በሙቅ ውሃ ከልሰን በደንብ ከተንተከተከ በኋላ መከለሻ ቅመም፣ ልጠን ያዘጋጀነውን እንቁላል፣ ጨው እና ቅቤ በመጨመር አውጥተን ለምግብነት እናውለዋለን።

**ተግባር**

፩. የሰው ልጅ ከልደት እስከሞት የሚያልፍባቸውን ሂደቶች በቅደም ተከተል ገለፃዊ በሆነ መንገድ ፃፉ።

፪. የፃፋችሁትን ጽሑፍ እርስ በእርስ በመቀያየር ከገላጭ ጽሑፍ ቅርጽ አንፃር እርስ በእርስ ተራረሙ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ

#### መልመጃ አንድ

በምሳሌው መሰረት የሚከተሉትን ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ አረፍተ ነገር ሰርታችሁ አመልክቱ፡፡

ምሳሌ፡- እርግብ

እማሬያዊ ፍቺ፡- እርግብ በራሪ የወፍ ዝርያ ናት፡፡

ፍካሬያዊ ፍቺ፡- ቤተልሄም እርግብ ናት፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፩. | መሬት | | |
| ፪. | ምስጥ | | |
| ፫. | ጉቶ | | |
| ፬. | እርጥብ | | |
| ፭. | ምላጭ | | |
| ፮. | እሳት | | |

#### መልመጃ ሁለት

ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት ቀጥተኛ ፍቺ ከመዝገበ ቃላት ፈልጋችሁ በደብተራችሁ አስፍሩና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

፩. ትንቢት
፪. መባቻ
፫. ማግስት
፬. በለተ
፭. አዛውንት
፮. ቀጠሮ
፯. ማነጽ

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

### ማስታወሻ

#### አረፍተ ነገር

አረፍተ ነገር ከአገልግሎት ወይም ከአላማ አንፃር በአራት ይከፈላል፡፡ እነሱም፡-

፩. ጥያቄያዊ ዓ.ነገር፡- መጠይቃዊ ቃላትን በተዋቃሪነት በውስጡ ይይዛል፡፡

**ምሳሌ፡-** ወዴት ትሔዳለህ?

፪. ትዕዛዛዊ ዓ.ነገር፡- ትእዛዝን የሚያሳይ ዓ.ነገራዊ ቅርጽ እና ይዘት አለው

**ምሳሌ፡-** -የቤት ስራችሁን በአግባቡ ሰርታችሁ ኑ!

፫. ሀተታዊ ዓ.ነገር፡- በአሉታዊ ወይም በአወንታዊ መልክ የሚቀርብ ነው

ሀ. አዎንታዊ ዓ.ነገር

**ምሳሌ፡-** ተስፋዬ ለልጁ ደብተር ገዛ፡፡

ለ. አሉታዊ ዓ.ነገር

**ምሳሌ፡-** ተስፋዬ ለልጁ ደብተር አልገዛም፡፡

፬. አጋናኝ ዓ.ነገር፡- ነገሮችን አግዝፎ ወይም በጣም አሳንሶ የሚያቀርብ የዓ.ነገር አይነት ነው፡፡

**ምሳሌ፡-** ትናንት የበላሁት እንጀራ እፍ ቢሉት ጎንደር ይገባል!

### መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች ጥያቄያዊ፣ ትዕዛዛዊ፣ ሀተታዊ እና አጋናኝ በማለት መልሱ፡፡

ሀ. ጎበዝ ተማሪ በርትቶ ያጠናል፡፡

ለ. የቤት ስራህን ስራ!

ሐ. ለምን ሁልጊዜ ትረብሻለህ?

መ. ልጁ ትናንት ደብተር አልገዛም፡፡

ሰ. ፎዝያ የሰማይ ስባሪ የሚያክል ዳቦ ሰጠችኝ!

**ተግባር**

የአረፍተ ነገሮችን አገልግሎት የሚያሳዩ ሶስት ሶስት አረፍተ ነገሮች ስሩ፡፡

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ገላጭ ወይም አስረጅ ድርሰት የአንድን ነገር አሰራር፣ አፈፃፀም፣ ምንነት፣ ባህርያት፣ ቅርጽ፣ አይነት፣ መጠን፣ አገኛኘት፣ ጠቀሜታ ወይም ጉዳት ወዘተ. ለማብራራት የሚፃፍ የድርሰት አይነት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በተጨማሪም የቃላትን እማሬያዊ ፍቺማለት የቃላት የተለመደ ወይም የተዘወተረ ትርጉም እንደሆነና ፍካሬያዊ ፍቺማለት ደግሞ የቃላት ድብቅ ወይም ስውር ፍቺ መሆኑን ተረድተናል፡፡በመጨረሻም አረፍተ ነገር ከአገልግሎት አንፃር ጥያቄያዊ፣ ትዕዛዛዊ፣ ሀተታዊ እና አጋናኝ ተብሎ እንደሚከፈል ተምረናል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ በአረፍተ ነገር አሳዩ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. ነብር | ሐ. ውሻ | ሠ. ብረት | ሰ. ባህር |
| ለ. ጎጆ | መ. አባት | ረ. ደረቅ | ሸ. እናት |

### መልመጃ ሁለት

የሚከተሉትን አረፍተነገሮች ጥያቄያዊ፣ ትዕዛዛዊ፣ ሀተታዊ እና አጋናኝ በማለት መልሱ፡፡

ሀ. የወርቅ ሀብሌን ማን ወሰደው?

ለ. ትምህርትህን አጥና!

ሐ. ሀኪሞቹ ሆስፒታል ውስጥ አልተገኙም፡፡

መ. ሞሎሮ ትምህርት ቤት ገብቷል፡፡

ሠ. የነጫሚሶ ቤት ፈረስ ያስጋልባል!

# ምዕራፍ ሰባት

## የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ

### የሚጠበቁ ውጤቶች፣

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ፡-

- መረጃ ሰጪ ጽሑፍን ታዳምጣላችሁ፤
- የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ምንነትና የሚያስከትለውን ውጤት ትገልጻላችሁ፤
- በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ትወያያላችሁ፤
- የአረፍተ ነገሮችን ተግባር ታነጻጽራላችሁ፤

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛና ሕገ ወጥ ዝውውር በከተማችን





## ቅድመ ማዳመጥ

### ተግባር

፩. ስለ ሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ምንነት የምታውቁትን ተናገሩ?
፪. ህገ ወጥ የሕጻናት ዝውውር ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል?
፫. አንዳንድ ወላጆች ለሕጻናት የህገ ወጥ ዝውውር አስተዋጽኦ የሚያደርጉት በምን አይነት መንገድ ነው? እንዴት?
፬. ስዕሉን በመመልከት የተረዳችሁትን ነገር አብራሩ፡፡

## ድህረ ማዳመጥ

### መልመጃ አንድ

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ካዳመጣችሁት ምንባብ በመነሳት ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡

፩. ሕጻናት በአቅማቸው መስራት አለባቸው ሲባል ምን ማለት ነው?
፪. ሕጻናትን ለጉልበት ብዝበዛና ለህገወጥ ዝውውር የሚዳርጉ መንስኤዎች ምን ምን ናቸው?
፫. የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ከተለያዩ ወንጀሎች ጋር ይያያዛል ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ነው?
፬. የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛና ህገ ወጥ ዝውውር በሕጻናቱ ላይ የሚያስከትሏቸው አሉታዊ ተጽዕኖዎች ምን ምን ናቸው?
፭. ለህገ ወጥ ዝውውር የሚዳረጉ ሴት ሕጻናት ለተለያዩ ችግሮች ይዳረጋሉ ሲል ምን ማለቱ ነው?
፮. ሕጻናት ከወላጆቻቸው ማግኘት ያለባቸው ነገር ምንድን ነው?
፯. የሕጻናት መብት ድንጋጌዎች ላይ የሰፈሩት ሀሳቦች ምንድን ናቸው?

### መልመጃ ሁለት

በ "ሀ" አምድስር የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት በ"ለ"አምድ ስር ካሉት ፍችዎቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| ፩. መገናኛ ብዙሃን | ሀ. ዋጋ |
| ፪. መታነጽ | ለ. መሰደድ፣ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ |
| ፫. ክስተት | ሐ. ተጫዋች |
| ፬. እሴት | መ. አዲስ ነገር |
| ፭. ሞግዚት | ሠ. መልዕክት ማሰራጫ |
| ፮. መፍለስ | ረ. ተንከባካቢ |
| ፯. ተዋናይ | ሰ. መቀረጽ፣ መገንባት |

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ተግባር

በሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ አራት አራት በመሆን ተወያይታችሁ ከስምምነት ላይ የደረሳችሁበትን ሀሳብ በተወካዮቻችሁ አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንግግር አቅርቡ፡፡

፩. የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛን ለመከላከል ከባለድርሻ አካላት ምን ይጠበቃል?

፪. ለህገ ወጥ ዝውውር ተጋላጭ የሆኑ ህፃናት ምን ምን ችግሮች የሚያጋጥሟቸው ይመስላችኋል?

፫. ሕጻናት የራሳቸውን መብት ማስከበር የሚችሉ ይመስላችኋል? እንዴት?

## ክፍል ሶስት፡- ማንበብ

### የቤና እና የመሰሎቿ ፍዳ



## ቅድመ ንባብ

**ተግባር**

፩. ርዕሱንና ስዕሉን በማየት ምንባቡ ስለምን ሊያወራ እንደሚችል ገምቱ፡፡

፪. ልጆች ቤተሰቦቻቸውን ማገዝ ያለባቸው እንዴት ይመስላችኋል?

## የቤና እና የመሰሎቿ ፍዳ

ቤና በለጠ ተወልዳ ካደገችበት ቡሌ ከተማ ከመጣች ሁለት ዓመት ሊሞላት ጥቂት ቀናት ብቻ እንደቀራት ነገረችኝ፡፡ ከሰውነት ጎዳና የወጣ ፊቷ በድካም የመወየብ ምልክቶች ቢታዩበትም ጠይምና መልከመልካም ናት፡፡ 13 ዓመት ሆኗታል፡፡ ያገኘኋት አርባ ምንጭ አካባቢ ነው፡፡ በቡሌ ከተማ እስከ ሁለተኛ ክፍል ተምሬያለሁ ያለችኝ ልበ ገሯ ቤና፤ ከቡሌ ይዛት የመጣችው አክስቷ ወደ አረብ ሃገር ስትሄድ ለአባቷ ዘመዶች ሰጥታት እንደሄደች አጫወተችኝ፡፡ ነገር ግን አክስቷም ሆነች አሁን የምትኖርባቸው ዘመዶቿ "የተሻለ ትምህርት ቤት እናስገባሻለን" ቢሏትም የትምህርት ቤት ደጃፍን ከረገጠች ድፍን ሁለት ዓመት ሊሆናት ነው፡፡ በዚህም ሁል ጊዜ ሆድ ስለሚብሳት ታለቅሳለች፤ ስለትምህርትም ሲጠይቋት፣ በርዕሱ መነሳት ደስተኛ እንዳልሆነች የሚሸሽኝ አይኗ ያሳብቃል፡፡

የምትኖርባቸው ዘመዶቿ በዕድሜ ከዕሷ የሚያንሱ ሶስት ልጆች እንዳሏቸው የገለጸችልኝ ቤና እሷግን ቤት ውስጥ ምግብ መስራት፣ ቤት ማጽዳት፣ ልብስ ማጠብ፣ ልጆችን መንከባከብ፣ ትምህርት ቤት ሲሄዱ ምሳ መቋጠር ወዘተ. የዕለት ተዕለት ህይወቷ መሆኑን ድካም ባዛለው ድምጿ ነገረችኝ፡፡

ይህ የቤና ታሪክ የአርባ ምንጭን ከተማ ብቻ ሳይሆን በርካታ የክልል ከተሞችንም የሚነካ እውነታ ነው፡፡ በኢትዮጵያ አሁንም በገጠር ያለው ድህነት ከከተማው የከፋ ነው፡፡ ከኢኮኖሚ ባለፈ ገጠሬው በማህበራዊ አገልግሎቶትም በከተሜው የሚመራ መሆኑ ደግሞ ከድጡ ወደማጡ ሆኖ በርካታ የቤና እኩዮች ከተማን እንዲናፍቁ አስገድዷቸዋል፡፡ እኛ ኢትዮጵያውያን ማህበራዊ ትስስራችን ጠንካራ በመሆኑ ልጅን ከተማ ያለ ቤተ-ዘመድ ጋር ልኮ ማስተማር የተለመደ ነው፡፡

**በምንባቡ መሰረት ቤና ለደረሰባት ችግር ተጠያቂው ማን ነው?**

**የቤና ሕይወት መጨረሻው ምን የሚሆን ይመስላችኋል?**

የወላጅን አደራ ተቀብለው የሚያስተምሩ በርካቶች መኖራቸው የማያጠራጥር ቢሆንም የቤና ዘመዶች አይነት በገጠር አልያም በአነስተኛ ከተሞች ያለቤተ-ዘመድን አቅም ማጣት ምክንያት አድርገው የልጆቻቸውን እኩዮች ጉልበት የሚበዘብዙም ቁጥራቸው ቀላል የሚባሉ አይደሉም፡፡

ቤና በጠዋት ተነስታ ወደ ትምህርት ቤትየሚወስዳቸውን አውቶብስ አንድ ሰዓት ላይ ለሚጠብቁት ሶስት ታዳጊዎች ልብስ ማልበስ፣ ቁርስ ማዘጋጀትና ምሳ መቋጠር ይጠበቅባታል፡፡ በተጨማሪም ነውር ጌጡ ለሆኑት የቤቱ ጌቶችም ምግብ ማዘጋጀት፣ ቤት ማጽዳት፣ ልብስ ማጠብ ወዘተ. ደግሞ በተከታታይ የሚጠብቋት ተግባራት ናቸው፡፡ ስለዚህ እንደ ጋራ ፊቷ የተቆለለው ስራ ካላለቀ የሚደርስባትን የቁጣ ውርጅብኝ ሽሽት ያለ እረፍት ስትባትል ትውላለች፡፡ ገና በለጋነቷ አምስት አባላት ያለውን ቤተሰብ፣ የዕለት ተዕለት ስራ የተሸከመችው ቤና፤ የልጅነት ወዟ እየተመጠጠ መሆኑን እረፍት የራቀውና በስራ ብዛት የደቀቀው ሰውነቷ ይጠቁማል፡፡

ቤና ምንም እንኳን ሰማይ ስለተደፋባት በምትኖረው ኑሮ ደስተኛ ባትሆንም አድሮ ቃሪያ የሆነው ሕይወቷ አንድ ቀን ለውጥ ይኖርና ያልፍልኛል በሚል ተስፋ ኑሮዋን መግፋቷ ግን አልቀረም፡፡ የቤናና መሰሎቿን ህይወት መቀየር የሚቻለው በህፃናት እና በሴቶች ላይ ከፍተኛ ጫና ባለባቸው አካባቢዎች፣ የማኅበረሰቡንግንዛቤ በማሳደግ፤ እንደትምህርትና ጤና የመሳሰሉ ማኅበራዊ አገልግሎቶችን በማስፋፋትነው፡፡

## ድህረ ንባብ

### መልመጃ አንድ

የሚከተሉት ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ ትክክል ከሆኑ "እውነት"፣ ስህተት ከሆኑ ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡

፩. ቤና ከተወለደች ጀምሮ የትምህርት ቤትን ደጅ ረግጣ አታውቅም፡፡

፪. በምንባቡ አንቀጽ ሁለት ላይቤና የምትኖረው የተደላደለ ኑሮ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

፫. የወላጅን አደራ ተቀብለው ልጆችን በአግባቡ የሚያሳድጉና የሚያስተምሩ ሰዎች አሉ፡፡

፬. በኢትዮጵያ ውስጥ በገጠር ያለው ድህነት ከከተማው እንደሚብስ የሚያስረዳው ሶስተኛው አንቀጽ ነው፡፡

፭. የቤናንና የመሰሎቿን ሕይወት ለመቀየር ከተፈለገ የማኅበረሰቡ ግንዛቤ ማደግ ይኖርበታል፡፡

፮. ጽሑፉን እየተረከች ያቀረበችው ራሷ ቤና ናት፡፡

## መልመጃ ሁለት

በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ፍቺየሚሆኑትን ምረጡ፡

፩. የትምህርት ቤቱን ደጃፍ ከረገጠች ድፍን ሁለት ዓመት ሊሆናት ነው፡፡

ሀ. ሰፈር ለ. በራፍ ሐ. አደባባይ መ. ክፍል

፪. ስለትምህርቷ ሲነሳ ደስተኛ እንዳልሆነች የሚሸሸኝ አይኗ ያሳብቃል፡፡

ሀ. ይናገራል ለ. ይደብቃል ሐ. ይስቃል መ. ይለምናል

፫. እንደጋራ ፊቷ የተቆለለው ስራ ካላለቀ የቁጣ መዓት ይወርድባታል፡፡

ሀ. የተሰበሰበው ሐ. የተከመረው
ለ. የተበተነው መ. ሀናሐ

፬. የልጅነት ፊቷ እየተመጠጠ መሆኑን ሰውነቷ ይጠቁማል፡፡

ሀ. እያማረበት ሐ. ወዙ እየጠፋ
ለ. እየፈካ መ. እየደረቀ

፭. ከሰውነት ጎዳና የወጣው ፊቷ የመወየብ ምልክት ቢታይበትም ጠይምና መልከመልካም ናት፡፡

ሀ. የመቅላት ሐ. የመገርጣት
ለ. የመዋብ መ. የመክሳት

፮. የዕለት ከዕለት ህይወቷ ቤተሰቡን መንከባከብ እንደሆነ በዛለው ድምጿ ነገረችኝ፡

ሀ. በደከመ  ለ. በበረታ  ሐ. ባማረ  መ. በቀጠነ

፯. በርካታ የቤና እኩዮች ከተማን እንዲናፍቁ አስገድዷቸዋል፡፡

ሀ. ባልደረቦች  ለ. ቤተሰቦች  ሐ. ዘመዶች  መ. መሰሎች

፰. ልጅን ከተማ ያለ ዘመድ ጋር ልኮ ማስተማር የተለመደ ነው፡፡

ሀ. አስገብቶ  ለ. ሰዶ  ሐ. አስተላልፎ  መ. አምጥቶ

፱. የሚደርስባትን የቁጣ ውርጅብኝ ሽሽት ያለ እረፍት ስትባትል ትውላለች፡፡

ሀ. ስትለፋ  ለ. ስትሰራ  ሐ. ስትደክም  መ. ሁሉም

፲. ቤና ገና በለጋነቷ አምስት አባላት ያለውን ቤተሰብ ስራ ተሸከመች፡፡

ሀ. በህፃንነቷ  ሐ. በጮርቃነቷ

ለ. በወጣትነቷ  መ. በቀንበጥነቷ

## መልመጃ ሶስት

በምንባቡ ውስጥ ያሉ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን በማውጣት ትርጉማቸውን ጻፉ፡፡

## መልመጃ አራት

በ "ሀ" አምድ ስር ላሉ ፈሊጣዊ አነጋገሮች በ "ለ" አምድ ስር ካሉት ፍችዎቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| ፩. ቃሉን ሰጠ | ሀ. ሊቅ፣ አዋቂ፣ ተመራማሪ |
| ፪. ቀንበር ሰበረ | ለ. የሰሚ ሰሚ፣ ጭምጭምታ |
| ፫. ነጭ ለባሽ | ሐ. ሀጢያት |
| ፬. የቀለም ቀንድ | መ. ስማኝ፣ አዳምጠኝ |
| ፭. የወሬ ወሬ | ሠ. መሰከረ |
| ፮. ደዌ ነፍስ | ረ. ህግ ተላለፈ |
| ፯. ውሃ መውቀጥ | ሰ. የመንግስት ሰላይ |
| ፰. የልጅ አዋቂ | ሸ. ከንቱ ልፋት |
| ፱. ድንጋይ ኳሱ | ቀ. አስተዋይ፣ ቁምነገረኛ |
| ፲. ጆሮ ስጠኝ | በ. ደፋር፣ ለምንም ነገር የማይበገር |

ተ. ፈሪ፣ እርብትብት
ቸ. የቀለም መበጥበጫ

## ክፍል አራት፡- መጻፍ

### መልመጃ አንድ

በጅምር የቀረቡትን አንቀፆች በሚሚላት አንቀጽ ጻፉ፡፡

፩. አንድ የራበው መንገደኛ ቤት ያንኳኳና የቤቱ ባለቤት ሲከፍትለት የራበኝ መንገደኛ ነኝ እባካችሁ የሚበላ ነገር ብሎ ጠየቀው፡፡ የቤቱ ባለቤት ግን ገና እንዳየው ሚስቱ አንገቷ ላይ እባጭ ታማ ተጨንቆ ነበርና የራበው መንገደኛ እባክህ መድሀኒት ታውቅ እንዴሁ ብሎ ጠየቀው፡፡ መንገደኛው አዎ በደንብ አውቃለሁ በማለት ወደግቢ ገባ፡፡ ከዚያም እንዳክማት ከፈለጋችሁ ልትወጡ ይገባል በማለት አዘዛቸው፡፡ ቤት ውስጥ የነበሩት ሰዎችም ከበሽተኛዋ ጋር ትተውት ወጡ፡፡ መንገደኛውም በሽተኛዋን ----------------------------------------
-----------------------------------------------------------------------------------------

፪. ጋን በገል ይታጠናል ይባላል፡፡ ጋንና ገል በሸክላነታቸው አንድ ናቸው፡፡ አንድ ትንሽ ሸክላ አንድን ትልቅ ሸክላ የቃና ለውጥ እንዲያደርግ ማጠኛ ይሆናል፡፡ ከማህበረሰብዓዊ ግንኙነት አንፃር ሲታይ አንድ ግለሰብ አንድ ማህበረሰብ ከአንድ አይነት ይዞታ እና ሁኔታ ወደ ሌላ የተሻለ ይዞታ እና ሁኔታ እንዲለወጥ ምክንያት ወይም መሳሪያ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህን ለማድረግ ግለሰቡ የማህበረሰቡን ስርዓትና መለያ ባህርያት በወጉ መገንዘብ አለበት፡፡ ግንዛቤው በከፊል ከማህበረሰቡ የወል ግንዛቤ፣ ባህርይና ተግባር ያፈነገጠ ሊሆን ይገባል፡፡ እንደዚህ ያለ አፈንጋጭ ግንዛቤ የያዘ ግለሰብ፤ ይዋል ይደር እንጂ ግንዛቤው ሌላውን የህብረተሰብ ክፍል ማዳረሱ አይቀርም -----------------
-----------------------------------------------------------------------------------------

### መልመጃ ሁለት

የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ በሕጻናት ላይ የሚያስከትለው አካላዊና ሥነ-ልቦናዊ ችግር የሚመለከት ባለ አምስት አንቀጽ ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

# ክፍል አምስት፡-ቃላት

## ተቃራኒ ፍቺ

### መልመጃ አንድ

ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ከተሰጡት አማራጮች መካከል በመምረጥ መልሱ፡፡

፩. ጉዳት

ሀ. ህመም ለ. መከፋት ሐ.ጥቅም መ. ችግር

፪. የግል

ሀ. የጋራ ለ. የሰው ሐ. የአንድ መ. የነጠላ

፫. ጥፋት

ሀ. ክፋት ለ. ልማት ሐ. እድገት መ.ሀብት

፬. እኩይ

ሀ. ሰናይ ለ. መጥፎ ሐ. አስቸጋሪ መ. ሀይለኛ

፭. ቅንነት

ሀ. መልካምነት ሐ. ሰናይ

ለ. ጥሩ መ. ክፋት

፮. ሙቅ

ሀ. ለሰስ ያለ ሐ. የሚያቃጥል

ለ. ቀዝቃዛ መ. የማይታኘክ

፯. ህቡዕ

ሀ. ድብቅ ሐ. ሚስጥራዊ

ለ. ስውር መ. ግልጽ

፰. ሁከት

ሀ. ሰላም ሐ. ነውጥ

ለ. ብጥብጥ መ. ሽብር

፱. ቧልት

ሀ. ፌዝ　　ለ. ቀልድ　　ሐ. ቁምነገር　　መ.ተረብ

፲. ኢምንት

ሀ. ቅንጣት　　ለ. ትንሽ　　ሐ. ጥቂት　　መ. ብዙ

## መልመጃ ሁለት

ከታች በአረፍተ ነገር ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ተቃራኒ ፍቺየሚሆኑትን ከሰንጠረዡ እየመረጣችሁ ተኩ።

| | | |
|---|---|---|
| ተጎጂ | ንፉግ | ያፋጥናሉ |
| መቀራረብ | መጥፎ | ሕይወት |
| ምድረ በዳ | ወረዛ | ጥብቅ |

፩. የኤልሳቤጥ አባት ለጋስ ናቸው።

፪. በዝናብ እጥረት የተነሳ መሬቱ ደረቀ።

፫. የነሙስጠፋ መንደር ነዋሪዎች የመስኖ ተጠቃሚ ናቸው።

፬. ልማዳዊ እና ጎጂ ድርጊቶች የአንድን ሀገር እድገት ያጓትታሉ።

፭. የእንጦጦ ጫካ ወደ መዝናኛነት ተቀይሯል።

፮. የቤተሰብ መራራቅ ለህፃናት ስነ ልቦና ጉዳት አለው።

፯. የክፍላችን አለቃ ፀባየ ሰናይ ነው።

፰. የሁለቱ አረፍተ ነገሮች ቁርኝት ልል ነው።

## መልመጃ ሶስት፡-

ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ቃላት መካከል ልዩ የሆነውን ምረጡ።

፩. ሀ. ተልባ　　ለ. ሱፍ　　ሐ. ኑግ　　መ. ሽንብራ

፪. ሀ. ክራር　　ለ. ዋሽንት　　ሐ. በገና　　መ. ማሲንቆ

፫. ሀ. ደቦል　　ለ. ሙጭሊት　　ሐ. ውርንጭላ　　መ. ቡችላ

፬. ሀ. ጀበና　　ለ. ድስት　　ሐ. ቅል　　መ. እንስራ

፭. ሀ. ጎመን　　ለ. ሰላጣ　　ሐ. ማንጎ　　መ. ቆስጣ

፮. ሀ. ጋቢ ለ. ፎጣ ሐ. ነጠላ መ. ኩታ

፯. ሀ. ሞፈር ለ. ቀንበር ሐ. ድግር መ. መንሽ

፰. ሀ. ጤፍ ለ. ዘንጋዳ ሐ. ማሽላ መ. በቆሎ

፱. ሀ. ባዝራ ለ. ቄብ ሐ. ጊደር መ. ኮረዳ

፲. ሀ. ሒስ ለ. ትችት ሐ. ነቀፋ መ. ዘለፋ

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

### መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን አረፍተነገሮች ሀተታዊ (አሉታዊ፣ አዎንታዊ)፣ ትዕዛዛዊ፣ እና መጠይቃዊ በማለት መልሱ።

፩. ያንን ጫማ ማን ገዛልሽ?

፪. ወጣቶቹ አውሬውን ገደሉት።

፫. ተማሪዎች ወደ ትምህርትቤት እንዳይመጡ!

፬. ደመወዝ ተቀበልክ እንዴ?

፭. ወለሉን ጥረጊ!

፮. ሕጻኗ ምንድን ነው የሰበረችው?

፯. መቅደስ ትናንት የወርቅ ቀለበት ገዛች።

፰. ባለፈው የተመረቀው ልጅ ልብስ አልተገዛለትም።

፱. ልብስ አትጠቡ!

፲. ለበሽተኛው መድኃኒት ተገዛለት።

### መልመጃ ሁለት

በ “ሀ” አምድ ያሉትን የአረፍተ ነገር አይነቶች በ “ለ” አምድ ካለው አገልግሎታቸው ጋር አዛምዱ።

| “ሀ” | “ለ” |
| --- | --- |
| ፩. ሀተታዊ አረፍተ ነገር | ሀ. ነገሮችን አግዝፎ (አሳንሶ) ያቀርባል |
| ፪. ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገር | ለ. መጠይቃዊ ቃላትን በተዋቃሪነት ይይዛል |
| ፫. መጠይቃዊ አረፍተ ነገር | ሐ. በአሉታዊና በአዎንታዊ መልክ ይቀርባል |
| ፬. አጋናኝ አረፍተ ነገር | መ. ትዕዛዝን የሚያሳይ አረፍተ ነገር |

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የቃላት ተቃራኒን ምንነት ተረድተን ቃላትን ከተቃራኒዎቻቸው ጋር አዛምደናል፡፡ በመቀጠልም አረፍተ ነገር ከአገልግሎት አንፃር ጥያቄያዊ፣ ትዕዛዛዊ፣ ሀተታዊ እና አጋናኝ ተብሎ እንደሚከፈል አስታውሰን አረፍተነገሮችን ከአገልግሎታቸው ጋር ለማዛመድ ችለናል፡፡

በአዎንታዊ ወይም በዓሉታዊ መልክ የሚቀርብ አረፍተ ነገር ሀተታዊ አረፍተ ነገር ሲባል፣ ትዕዛዝን ለማመልከት የምንጠቀምበት አረፍተ ነገር ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገር እንደሚባል አይተናል፡፡ በተጨማሪም መጠይቃዊ ቃላትን በተዋቃሪነት የያዘ አረፍተነገር ጥያቄያዊ አረፍተ ነገር ሲባል ነገሮችን አግዝፎ ወይም አሳንሶ ለማቅረብ የሚያገለግል አረፍተነገር አጋናኝ አረፍተ ነገር እንደሚባል ተገንዝበናል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ፈሊጣዊ አነጋገሮች ፍቺ ፃፉ፡፡

፩. እንጀራ ወጣለት

፪. ጭራው ጮሌ

፫. የግንባር ስጋ

፬. ገመና ከታች

፭. ጉልበት አወጣ

፮. ደግ ዋለለት

## መልመጃ ሁለት

የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች ሀተታዊ (አዎንታዊ፣ አሉታዊ)፣ ትዕዛዛዊ፣ መጠይቃዊና አጋናኝ በማለት ለዩ፡፡

፩. የሂሩት ልጅ ትናንት አገባ፡፡

፪. ትምህርት ቤቱ መቼ ተከፈተ?

፫. እንግዶቹ ከሄዱበት አልተመለሱም፡፡

፬. አርፈሽ ትምህርትሽን አጥኚ!

፭. ጉዮ ሰማይ ጠቀስ ፎቅ ሰራ!

# ምዕራፍ ስምንት

## ሰላም

### የሚጠበቁ ውጤቶች፣

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ፡-

- አዳምጣችሁ ጽሑፉን ትተነትናላችሁ፤
- የሰላምን አስፈላጊነት ትገልፃላችሁ፤
- አንብባችሁ የጽሑፉን ሀሳብ አጠቃላችሁ ትጽፋላችሁ፤
- በጽሑፍ ውስጥ ተገቢውን ሥርዓተ ነጥብ ትጠቀማላችሁ፤

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### ሰላምን ፍለጋ



## ቅድመ ማዳመጥ

### ተግባር

፩. ሰላምን ፈልጎ ማግኘት የሚቻል ይመስላችኋል? እንዴት?

፪. የሰላምን አስፈላጊነት ግለፁ።

፫. ስዕሉን በመመልከት የተረዳችሁትን ነገር አብራሩ።

## ድህረ ማዳመጥ

### መልመጃ አንድ

ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክል ከሆኑ "እውነት" ስህተት ከሆኑ ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልሱ።

፩. ሰዎች ብዙ ደክመውም ቢሆን ሰላምን ፈልገው ማግኘት ችለዋል።

፪. ሰላምን መፈለግ ብቻውን የሰላም ማስፈኛ መሳሪያ ነው።

፫. በአሁኑ ሰዓት የሰላም መደፍረስ ምክንያት ከወትሮው ይልቅ ቀላል፣ ለመፍታት ግን አስቸጋሪ ነው።

፬. የዓለም መንግስታት የሰላም ማስጠበቅ ስምምነት ሰነድ በመፈራረማቸው ሰላምን ማስፈን ችለዋል።

፭. ሰላም የእያንዳንዱን ግለሰብ በጎ ፈቃድና ትብብር የሚጠይቅ ነው።

፮. ከራሱ ጋር ሰላም ያላወረደ ግለሰብ ከሌላው ማህበረሰብ ጋር በሰላም ለመኖር አይቸገርም።

### መልመጃ ሁለት

ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

፩. ከሚከተሉት አንዱ ሰላምን በተመለከተ የወጣ ስያሜ አይደለም።

ሀ. ደብረ ሰላም　　　　ሐ. ፍቅረ ሰላም

ለ. ሀገረ ሰላም　　　　መ. መልስ አልተሰጠም

፪. ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት በሰላም ለመኖር የማያስፈልገው የትኛው ነው?

ሀ. ከጦርነት የፀዳ አካባቢ

ለ. ከሁከትና ብጥብጥ የተቆጠበ አንደበት

ሐ. ከራስ በላይ ሰማይ የሚል አመለካከት

መ. ከግጭት ነፃ የሆነ ህይወት

፫. ከሚከተሉት አንዱ አብሮ ለመኖር አስፈላጊ አይደለም።

ሀ. መተሳሰብ | ሐ. መቻቻል

ለ. መናናቅ | መ. መደጋገፍ

፬. ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ሰላምን ለማግኘት ከተሰሩ ስራዎች ውስጥ ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. መንፈሳዊ ጉዞ ማድረግ | ሐ. የሰዎች ከሀገር መሰደድ

ለ. የደራስያን ጽሁፍ | መ. ለራስ ብቻ መጨነቅ

፭. "ጉንጭ ማልፋት ቢሆንም ቅሉ" ሲል ምን ማለቱ ይመስላችኋል?

ሀ. ከንቱ ልፋት | ሐ. ስኬታማ ጥረት

ለ. ጉንጭ ማሸት | መ. ጉንጭ መምታት

፮. ለሰላም መታሰቢያነት በአገራት ባንዲራ ጎን የሚቀረፀው የምን ምስል ነው?

ሀ. የግመል | ሐ. የአንበሳ

ለ. የዕርግብ | መ. የንስር

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ትዕዛዝ

በሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያይታችሁ ከስምምነት ላይ የደረሳችሁበትን ሀሳብ በተወካያችሁ አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

፩. ሰላም ምንድን ነው?

፪. የሰላም መኖር ለእድገት ያለውን አስተዋጽኦ እንዴት ትገልፁታላችሁ?

፫. ሰላምን ማስጠበቅ የማን ሀላፊነት ይመስላችኋል?

፬. በአንድ ሀገር ሰላም ከሌለ ተጎጅዎች እነማን ይመስሏችኋል?

# ክፍል ሶስት፡- ማንበብ

## ሰላም ለዕድገታችን

### ቅድመ ንባብ

**ተግባር**

፩. ለሰላም እጦት ምክንያት የሚሆኑ ጉዳዮችን ዘርዝሩ፡፡

፪. የሰላም ዕጦት በአንድ ሀገር ላይ ምን አይነት ጉዳት የሚያስከትል ይመስላችኋል?

፫. ከዚህ በታች ያለውን ስዕል አይታችሁ ምን እንደተረዳችሁ ግለፁ፡፡






## ሰላም ለዕድገታችን

ሰላም የህይወት ዋስትና የእድገት መሰረት ነው፡፡ የአንድነት፣ የፍቅርና የደስታ ምንጭም ነው፡፡ ሰላም እያንዳንዱ ጤናማ ሰው ምንጊዜም በየትም ቦታ ሆኖ የሚመኘው ነው፡፡ ሰላምና እፎይታ ያላጀበው ኑሮ መሰረቱ የተናጋ ነው፡፡ ውጤቱም ለፖለቲካ ቀውስ፣ ለኢኮኖሚ ድቀትና ለተለያዩ ማህበራዊ ችግሮች የሚዳርግ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ለትውልድ የሚተርፍ ጠቃሚ ነገር የለውም፡፡

ሰላም ለህብረተሰብ ኑሮ ዋልታና ማገር ነው፡፡ በመሆኑም ሰርቶ ለመኖር ሰላም፣ ወጥቶ ለመመለስ፣ ተወልዶ ለማደግ፣ ተምሮ ለሀገርና ለወገን ቤዛ ለመሆን ሰላም፣ በአጠቃላይ የአዕምሮ እፎይታና የመንፈስ እርካታ አግኝቶ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ግኝቶች እየተጠቀሙ እድገትን በማፋጠን ረገድ ሰላም ወደር የለሽ ሚና ይጫወታል፡፡ በተለይ ሰፊው ህዝብ ከጦርነት ይልቅ ሰላምን ይሻል፤ ምክንያቱም በማንኛውም ጊዜ በሚቀሰቀስ ችግር ግንባር ቀደም ተጠቂ ሆኖ ጉዳት የሚደርስበት በመሆኑ ነው፡፡

በምንባቡ መሰረት "ሰላም የህይወት ዋስትና ነው" ሲባል ምን ማለት ነው?

ሰላም ሲደፈርስ ምን ምን ችግሮች የሚፈጠሩ ይመስላችኋል?

በሌላ በኩል ደግሞ ሰላም ሲደፈርስ ጦርነቶችና የዕርስ በዕርስ ግጭቶች ይፈጠራሉ፡ አምራቹ ዜጋ በጦርነት እንዲሰለፍ ይደረጋል፡፡ ሀገሪቱ ያፈራችውም ጥሪት ለጦርነት መሳሪያ መግዣ ይውላል፡፡ ከዚህም የተነሳ ሰፊው ሕዝብ በተጎሳቆለ ህይወት ውስጥ እንዲኖር ይገደዳል፡፡ ጦርነትን የሚጭሩ ወይም የሚቀሰቅሱ ኃይሎች ከሰላምና ከዴሞክራሲ ይልቅ ጦርነትን በማስቀደም ጥቅማቸውን ያሳድዳሉ፡፡ የሚያቀጣጥሉት ጦርነት ግን ይህ ነው የማይባል የህይወትና የንብረት ጥፋት የሚያስከትል መሆኑን ይዘነጋሉ፡፡

በሀገሮች መካከል ጦርነት ሲኖር ተጠቂው ሰፊው ሕዝብ መሆኑ እርግጥ ነው፡ በመሆኑም አስገዳጅ ሁኔታ ካላጋጠመው በስተቀር ጦርነትን የሚናፍቅ ሕዝብ የለም፡፡ በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለው ፍላጎት በአገሪቱ ሙሉ ለሙሉ ሰላም ሰፍኖ በህዝብ ፈቃደኝነት አንድነቷ የፀና፣ ፍትህና እኩልነት የሰፈነባት ኢትዮጵያን ማየት ነው፡፡ ፍትህና እኩልነት በሀገራችን ሲሰፍን የጋራ ችግሮቻችንን በመቀራረብ፣ በመግባባትና በውይይት በመፍታት ለሀገራችን ዘላቂና አስተማማኝ ሰላም ለመፍጠር እንደሚቻል ይታመናል፡፡ ለዚህ ዓላማ ግብ መምታት የአንድ ወገን ጥረት ብቻ ሳይሆን የሁላችንንም ጥረት የሚጠይቅ ጉዳይ መሆኑ መታወቅ አለበት፡፡

ያለ ሰላም ወጥቶ መግባት፣ ወልዶ መሳም፣ ነግዶ ማትረፍ፣ ዘርቶ መቃም ወዘተ. አይታሰብምና እያንዳንዱ ዜጋ ለሰላም ዘብ መቆም ይኖርበታል፡፡

(ከቀድሞው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ተሻሽሎ የተወሰደ)

## ድህረ ንባብ

### መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆኑ "እውነት" ስህተት ከሆኑ ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡

፩. የአንድ ሀገር እድገት የሚረጋገጠው ሰላም ሲኖር ብቻ ነው፡፡

፪. ሁልጊዜም ሰላም ሊገኝ የሚችለው ተመራማሪዎች በሚያደርጉት ጥናትና ምርምር ነው፡፡

፫. ፍትሕና እኩልነት የሰፈነባት ኢትዮጵያን ማየት የሕዝቦች ምኞት ነው፡፡

፬. አስተማማኝ ሰላም ዘላቂነት ያለውና በሕዝቦች በጎ ፈቃድ ሊፈጠር የሚችል አይደለም፡፡

፭. ጦርነት ሁልጊዜ አስከፊ ገጽታ ነው ያለው ማለት አይቻልም፡፡

፮. በሀገራት መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶች ከሕዝቦች መጠላላት የመነጩ አይደሉም የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡

፯. ማንኛውም ህዝብ ጦርነትን አይደግፍም፡፡

፰. ጦርነት ባለበት ዴሞክራሲ፣ ዴሞክራሲ ባለበት ጦርነት አይታሰብም፡፡

፱. ከሰላም የተሻለ ኑሮ ሲገኝ፤ ከጦርነት ግን የሚገኘው እልቂት፣ ፍጅት፣ ረሀብና እርዛት ነው፡፡

፲. "ጦርነትን ለማስወገድ ለጦርነት ጆሮህን አትስጥ" የሚለው አባባል ትክክል ይመስላል፡፡

### መልመጃ ሁለት

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

፩. ከሚከተሉት ውስጥ ሰላምን በተመለከተ ትክክል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ሰላም የፍቅርና የደስታ ምንጭ ነው፡፡

ለ. ሰላም የህይወት ዋስትና ነው፡፡

ሐ. ሰላም የዕድገት መሰረት ነው፡፡

መ. ሁሉም

፪. በምንባቡ አንቀጽ አንድ ላይ "ሰላምና እፎይታ ያላጀበው ኑሮ መሰረቱ የተናጋ ነው" ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ. የተረጋጋ                ሐ. የተቃወሰ

ለ. የተስተካከለ              መ. የተደላደለ

፫. በአንድ ሀገር ሰላም ሲደፈርስ ምን ይከሰታል?

ሀ. አምራቹ ዜጋ ለጦርነት እንዲሰለፍ ይደረጋል

ለ. የህዝቡ ኑሮ ይሻሻላል

ሐ. ፍትህና እኩልነት ይሰፍናል

መ. ሰርቶ መለወጥ ቀላል ይሆናል

፬. የኢትዮጵያ ህዝብ በአሁኑ ወቅት ያለው ፍላጎት-----------------------ነው፡፡

ሀ. ልማት     ለ. ጦርነት     ሐ. እድገት     መ. ሀ እናሐ

፭. ጦርነት ---------------------------------ነው፡፡

ሀ. ፀረ እድገት              ሐ. ፀረ ሰላም

ለ. ፀረ ሕዝብ               መ. ሁሉም

፮. በምንባቡ አንቀጽ አራት ላይ "ፍትህና እኩልነት የሰፈነባት ኢትዮጵያን ማየት" ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ. ያልተዛባና ከአድሎ የፀዳች              ሐ. በድህነት የተራቀቀች

ለ. በዕድገት ያዘገመች                  መ. በቴክኖሎጂ የበለፀገች

፯. በምንባቡ ሊተላለፍ የተፈለገው መልዕክት ምንድን ነው?

ሀ. ጦርነት ለሀገር እድገት ወሳኝ መሆኑን

ለ. ሰላም ለሀገር ብልጽግና የማይተካ ሚና ያለው መሆኑን

ሐ. ያለጦርነት ሰላም ሊሰፍን የማይችል መሆኑን

መ. ጦርነት ከሰላም የሚመነጭ መሆኑን

## መልመጃ ሶስት

"ሰላም" በሚል ርዕስ የቀረበውን ግጥም በደንብ አንብቡና መልዕክቱን በአንድ አንቀጽ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

### ሰላም

አንዱ ለፀሎተ ውዳሴው፤
ሌላው ለፍሬከርስኪ ጉባዔው፤
ደሞ ሌላው ... ለነገር ማጣፈጫ፤

ለፈራጅ አዕምሮ መቀጣጫ፣
ለአምባ-ገነን ሥልጣን መጨበጫ፣
ስንቱ ለከንቱ በከንቱ ያነሳሻል፣
አንስቶ ... ክቦ ... ክቦ ... ይጥልሻል፡፡
...
ከልጅነቴ ጀምሮ የምሰማት፣
ልጅ፣ ሽማግሌው የሚወዳት፣
የማትለወጥ ጣፋጭ ቃል፣
"ሰላም" የምትባል፣
ትርጉሟ ጠፍቶብኛል፡፡
እባካችሁ የገባችሁ አስረዱኝ፣
ሰላም ምንድን ናት ንገሩኝ፡፡
...
በኢራን፣ በኢራቅ፣ በጋዛ ሠርጥ፣ ካምቦዲያ፣
ኒካራጓ፣ ደቡብ ሱዳን፣ ናሚቢያ፣
በሰሜን ሕንድ፣ በአፍጋኒስታን፣ በኢትዮጵያ፣
ያለሽ እናት፣ ያለህ ወገን፣
ያለህ ሕፃን፣
ሰላም ምን ማለት ነው ንገረኝ፣
ዋጋዋ ምን ያህል ነው አስረዳኝ፣
አንተም የአውሮፓው ሰው ንገረኝ፣
ስንት ነብስ፣ ስንት ሀብት፣ ስንት ጥይት ነው፣
ሰላምን ገዝቶ ለማቆየት "ሚከፈለው?

(ከታደሰ ብሩ፣ ሕዳር 1982)

## መልመጃ አራት

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በግጥሙ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

፩. የሰላም ዋጋዋ ስንት ነው?

ሀ. በሚሊዮን የሚቆጠር ነው    ለ. እልፍ ነው

ሐ. በገንዘብ የሚተመን አይደለም    መ. በገንዘብ መተመን ቀላል ነው

፪. የሰላም መኖር አስፈላጊነቱ ለማን ነው?

ሀ. ለእኔ
ለ. ለአንተ
ሐ. ለእንች
መ. ለሁላችንም

፫. ገጣሚው ከልጅነቱ ጀምሮ ይሰማት የነበረችው ቃል ምንድን ናት?

ሀ. እኩልነት
ለ. ሰላም
ሐ. ዴሞክራሲ
መ. ፍትሃዊነት

፬. ሰላምን አንግሶ ለማቆየት የሚያስፈልገው ምንድን ነው?

ሀ. ገንዘብ
ለ. ጤና
ሐ. ጊዜ
መ. መልስ የለም

፭. ሰላምን ማስፈን የሚችለው ማን ነው?

ሀ. ግለሰብ
ለ. ማህበረሰብ
ሐ. መንግስት
መ. ሁሉም

፮. በግጥሙ ሁለተኛ ስንኝ ላይ "ፍሬ ከርስኪ" የሚለው ቃል ትርጉሙ ምንድን ነው?

ሀ. እርባና ቢስ
ለ. ቁምነገር አዘል
ሐ. ጠቃሚ ነገር
መ. ፍሬ ነገር



## ክፍል አራት፡- መጻፍ

### መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ሥርዓተ ነጥብ ነክ ጥያቄዎች እንደ አጠያየቃቸው መልስ ስጡ፡፡

፩. የመስሪያ ቤት ደብዳቤዎችን ስንጽፍ መለያ ቁጥሮችንና ዓመተ ምህረትን ለመለየት የምንጠቀምበት ሥርዓተ ነጥብ የትኛው ነው?

ሀ. ቅንፍ
ለ. ነጠላሰረዝ
ሐ. እዝባር
መ. ሁለት ነጥብ

፪. ትክክለኛውን የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም የተከተለው አረፍተነገር የትኛው ነው?

ሀ. "ዛሬ ትምህርት እንዴት ነበር?" አለው አባት "በጣም ጥሩ ነበር።" ሲል ልጅ መለሰ።

ለ. "ዛሬ ትምህርት እንዴት ነበር አለው?" አባት "በጣም ጥሩ ነበር።" ሲል ልጅ መለሰ።

ሐ. "ዛሬ ትምህርት እንዴት ነበር!" አለው አባት "በጣም ጥሩ ነበር" ሲል ልጅ መለሰ።

መ. "ዛሬ ትምህርት እንዴት ነበር?" አለው አባት በጣም "ጥሩ" ነበር ሲል ልጅ መለሰ።

፫. ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ቃላት ተከታትለው ሲመጡ ለመለየት የምንጠቀመው ስርዓተ ነጥብ የትኛው ነው?

ሀ. ድርብ ሰረዝ ሐ. ጥያቄ ምልክት

ለ. ነጠላ ሰረዝ መ. ቅንፍ

፬. ሊቁ እንዲህ ብሏል፤ የማውቀው አለማወቄን ነው። በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ የሚገባው ሀሳብ የትኛው ነው?

ሀ. እንዲህ ብሏል ሐ. አለማወቄን ነው

ለ. ሊቁ እንዲህ ብሏል መ. የማውቀው አለማወቄን ነው

፭. ኤልዳና በትምህርቷ ጎበዝ ናት---------ሆኖም ትበጠብጣለች። በባዶ ቦታው የሚገባው ስርዓተ ነጥብ የትኛው ነው?

ሀ. ፣ ለ. " " ሐ. ፤ መ. …

## መልመጃ ሁለት

ከሚከተሉት ሥርዓተ ነጥቦች መካከል ተገቢ የሆኑትን መርጣችሁ በአንቀፁ ውስጥ ያሉትን ቁጥሮች ተኩ።

| | |
|---|---|
| አራት ነጥብ (።) | ድርብ ትዕምርተ ጥቅስ (" ") |
| ነጠላ ሰረዝ (፣) | ነጠላት ዕምርተ ጥቅስ (' ') |
| ድርብ ስዝ (፤) | ጥያቄ ምልካት (?) |
| ቃለ አጋኖ (!) | ሁለት ነጥብ ከሰረዝ (፡-) |

**ጥያቄ፡-** ፩. 1 ጥበቡ በለጠ 2 ድንቅ ተማሪ ነው 3 የመሐመድ ኪጴማ አይነገርም 4 ሲል መምህሩ ተናገረ 5

**ጥያቄ፡-** ፪. የክብር እንግዳው ንግግራቸውን ቀጥለዋል 1 2 ሀገር ከባለሀገሩ ተለይታ እንዴት መታየት ትችላለች 3 4 ሀገሬ ለእኔ ምን አደረገችልኝ ሳይሆን እኔ ለሀገሬ ምን አደረኩላት 4 እንደሚባለው 5 እያንዳንዱ ዜጋ ራሱን ሊጠይቅና የዜግነት ግዴታውን ሊወጣ ይገባል 6 2

## መልመጃ ሶስት፡-

በ "ሀ" አምድ ስር ላሉ ሥርዓተ ነጥቦች በ "ለ" አምድ ስር ካሉት አቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| ፩. አንድ ነጥብ (.) | ሀ. የቃለ አጋኖ ምልክት |
| ፪. ሁለት ነጥብ (:) | ለ. የጥቅስ ምልክት |
| ፫. ትዕምርተ አንክሮ (!) | ሐ. ይዘት |
| ፬. እዝባር (/) | መ. አቆልቋይ |
| ፭. ሰረዝ (-) | ሠ. ቃልን ከቃል ይለያል |
| ፮. እሩይ (=) | ረ. የኮከብ ምልክት |
| ፯. ረድፍ (***) | ሰ. ወይም |
| ፰. አብይ ሰረዝ (—) | ሸ. እኩል ይሆናል |
| ፱. ቅንፍ ( ) | ቀ. ጭረት |
| ፲. ትዕምርተ ስላቅ (¡) | በ. እስከ |
| | ተ. ምፀትን፣ ማሾፍንና ስላቅን ያመለክታል |

# ክፍል አምስት፡- ቃላት

## አውዳዊ ፍቺ

## መልመጃ አንድ

በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡

፩. ሄኖክ ለእናት ሀገር ጥሪ ወደ ድንበር ገሰገሰ፡፡

፪. እሱባለው ብዕሩን አልሰጥም አለ፡፡

፫. ኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ሙሌት በሰላም መጠናቀቁን አስመልክታ ለዓለም ሀገራት ደስታዋን አበሰረች፡፡

፬. ለሁሉም ነገር የሚሻለው በህብረት መቆም ነው፡፡

፭. ስነቃል በባህርዩ ተለዋዋጭ ነው፡፡

፮. በስርዓት የሚሰደሩ ድምፆች ስብስብ ቃል ይባላል፡፡

## መልመጃ ሁለት

የሚከተሉትን ቃላት አውዳዊ ፍቺ ተጠቅማችሁ አረፍተ ነገር ስሩ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፩. ባህል | ፬. አሸን | ፯. ሀሴት | ፲. አባይ |
| ፪. ጠላት | ፭. አዛውንት | ፰. ሙስና | |
| ፫. ንዋይ | ፮. ፋይዳ | ፱. ዋና | |

## መልመጃ ሶስት

የሚከተሉትን ቃላት መዝገበ ቃላት ተጠቅማችሁ ፍቺቻውን ስጡ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፩. ተደራሲ | ፬. ፋና | ፰. አልፋ | ፲. አደብ |
| ፪. ታዳሚ | ፭. በየነ | ፱. ኩታገጠም | |
| ፫. አብነት | ፮. ምንዳ | ፯. ህፀጽ | |

# ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

## ማስታወሻ

### አረፍተ ነገር

አረፍተ ነገሮች በውስጣቸው ከሚይዙት የግስ ብዛት አንፃር በሁለት ይከፈላሉ፡፡

**፩. ነጠላ አረፍተ ነገር:-** አንድ ግስ ብቻ ያለው ዓ.ነገር ነጠላ ዓ.ነገር ተብሎ ይጠራል፡፡

**ምሳሌ:-** አልማዝ ጫማና ቦርሳ ገዛች፡፡

ህፃን ልጅ ወተት ይወዳል፡፡

ልጁ መጣ፡፡

**፪. ውስብስብ አረፍተ ነገር:-** ከአንድ በላይ ግስ ያለው ዓ.ነገር ውስብስብ ዓ.ነገር ይባላል፡፡

**ምሳሌ:-** ደቻሳ እያወራ ይበላል፡፡

በድርያ ስለምትፈራ ችግሯን አትናገርም፡፡

ፌትያ ወንድሟ ወደውጭ ሀገር ስለሄደ አዘነች፡፡

## መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች ነጠላ እና ውስብስብ አረፍተ ነገር እያላችሁ ለዩ፡፡

፩. አብዱ ዛሬ ብዙ ጥያቄ አቀረበልኝ፡፡
፪. ጨዋታውን ፊት ለፊት በማየቴ ደስ አለኝ፡፡
፫. ዳንቺሌ እስር ቤት ሂዳ እህቷን ጠየቀች፡፡
፬. ዘበርጋ ፊቱን ታጠበና ቁርሱን በላ፡፡
፭. ሀሰን ቁልፍ ወስዶ በሩን ከፈተ፡፡
፮. እውቀት ከጥበብ ጋር ትምህርት ቤት ሄደች፡፡
፯. አቤኔዘር የክፍል ስራውን ሰርቶ አሳረመ፡፡
፰. ሁንዴ ከመኝታው ተነስቶ አልጋ አነጠፈ፡፡
፱. የሀሰን ወንድም ቁምሳጥኑን ከፈተ፡፡
፲. ፍቅር ዛሬ ጠዋት ትምህርት ቤት ሄደ፡፡

## መልመጃ ሁለት

አምስት አምስት ተራ እና ውስብስብ አረፍተ ነገሮች ጻፉና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

# ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ስርዓተ ነጥብ በወረቀት ላይ የሰፈረ ሀሳብ መልዕክቱ ግልጽ ሆኖ እንዲተላለፍ የሚያደርግ እንደሆነ አይተን የተለያዩ የስርዓተ ነጥብ አይነቶችን ጠቀሜታ ለመረዳት ችለናል፡፡

በመጨረሻም አንድ ግስ ብቻ ያለው አረፍተ ነገር ነጠላ አረፍተ ነገር ሲባል ከአንድ በላይ ግሶችን ያካተተ አረፍተ ነገር ደግሞ ውስብስብ አረፍተ ነገር እንደሚባል ተረድተናል፡፡

# የክለሳ ጥያቄዎች

## መልመጃ አንድ

ከሚከተሉት ስርዓተ ነጥቦች መካከል ተገቢ የሆኑትን መርጣችሁ በአንቀፁ ውስጥ ባሉት ክፍት ቦታዎች አስገቡ፡፡

| | |
|---|---|
| ድርብ ትዕምርተ ጥቅስ | ነጠላ ሰረዝ |
| አራት ነጥብ | ጥያቄ ምልክት |
| ድርብ ሰረዝ | ነጠላ ትዕምርተ ጥቅስ |
| ሁለት ነጥብ | ሁለት ነጥብ ከሰረዝ |

____________ የተወለደባት ሀገር ላንድ ሰው ባንድ ቃል ሕይወቱ ናት ስለዚህ ድንበሯን የሚደፍር________መሬቷን የሚነጥቅና የሚቃወም ጠላት ሲነሳ ወይም ሲመጣ ማን ዝም ይላል________ ዜጎቿ ይቆሙላታል________ከምድሯ የተገኘውን ፍሬ በልተውና ውሀዋን ጠጥተው የሚኖሩት ሁሉ በጋራ ይጠብቋታል ________ ያገር ህልውና ሲከበር ህዝብ ይሰራል________ ያመርታል________ በነፃነትም ይኖራል፡፡________

## መልመጃ ሁለት

ሶስት ሶስት ነጠላ እና ውስብስብ አረፍተ ነገሮች ፃፉ፡፡

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## አየር ንብረት

### የሚጠበቁ ውጤቶች፣


ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ፡-

- የጽሑፉን ሀሳብ አዳምጣችሁ ትገመግማላችሁ፤
- የአየር ንብረትን ምንነት ትገልፃላችሁ፤
- የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትለውን ውጤት ታብራራላችሁ፤
- ለተለያየ አላማ ታነባላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### የአየር ንብረትና የአካባቢ ብክለት





## ቅድመ ማዳመጥ

**ተግባር**

፩. ከፋብሪካዎች የሚወጣ ጭስ ለአየር ንብረት ለውጥ እንዴት መንስኤ ሊሆን የሚችል ይመስላችኋል?

፪. ሰዎች አካባቢያቸው እንዳይበከል ካደረጉ ምን ምን ጥቅም የሚያገኙ ይመስላችኋል?

፫. የአካባቢ ብክለትና የአየር ንብረት ለውጥ ያላቸው ግንኙነት ምንድን ነው?

፬. ስዕሉን በማየት የተረዳችሁትን ግለፁ።

## ድህረ ማዳመጥ

### መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት በጽሑፍ መልሱ።

፩. የሰው ልጅ ከሚኖርበት አካባቢ ጋር ያለው ግንኙነት ምንድን ነው?

፪. የተፈጥሮ ሀብቶች የምንላቸው ምን ምን ናቸው?

፫. የአካባቢ ብክለት ጉዳትን በቶሎ የምንገነዘበው አይደለም ሲባል ምን ማለት ነው?

፬. የአየር ብክለት ከገጠርና ከከተማ በየትኛው ጎልቶ ይታያል? ለምን?

፭. የኦዞን ሽፋን መሳሳት በከባቢ አየር ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ምንድን ነው?

፮. ውሃ ሲበከል ጉዳት የሚደርስባቸው አካላት እነማን ናቸው?

፯. ብዙዎቹ ፋብሪካዎች ከወንዝ አጠገብ የሚገነቡት ለምንድን ነው?

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### መልመጃ አንድ

በሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ሶስት ሶስት ሆናችሁ በመወያየት የደረሳችሁበትን የመፍትሄ ሀሳብ በተወካዮቻችሁ አማካኝነት ለክፍል

ጓደኞቻችሁ በንግግር አቅርቡላቸው፡፡

፩. የአየር ንብረት ለውጥን ለመቅረፍ ከህብረተሰቡ የሚጠበቀው ምንድን ነው?

፪. አካባቢያቸውን ከብክለት ለመታደግ ሰዎች ምን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል?

፫. የአየር ንብረት ለውጥን ለመግታት የበለጸጉ ከሚባሉ ሀገራት ምን ይጠበቃል? ከታዳጊዎችስ?

## መልመጃ ሁለት

ለሚከተሉት ቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ስጡ፡፡

ሀ. በከለ

ለ. ሸፈነ

ሐ. መሸሸት

መ. ጠንቅ

ሠ. ዝቃጭ

### ማስታወሻ

### የክርክር መመሪያ

ክርክር አንድና ከዚያ በላይ በሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ተቃራኒ አስተሳሰብ ባላቸው ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ቡድኖች መካከል የሚካሄድ ሙግት፣ ፍትጊያና ሰጣ ገባ ነው፡፡ ክርክር ሲካሄድ የተሟጋቾችን ሀሳብ መዝነው ፍርድ የሚሰጡ ዳኞች ይኖራሉ፡፡ ተከራካሪዎች ደግሞ ደንብና መመሪያዎችን ጠብቀው በቂ ዝግጅት አድርገው ይቀርባሉ፡፡

፩. የክርክር ዝግጅት

- የመከራከሪያ ርዕሰ ጉዳይ መለየትና መወሰን
- ርዕሱን በሚመለከት ከተለያዩ መረጃ ምንጮች መረጃ መሰብሰብ
- ከተሰበሰቡት መረጃዎች ለክርክሩ የሚመጥኑትን መምረጥ
- ክርክሩ የሚቀርብበትን ቅደም ተከተል መወሰን
- ለክርክር ከመቅረባችን በፊት በቂ ልምምድ ማድረግ
- በክርክሩ ላይ አለባበስንና ንጽህናን ጠብቆ መገኘት
- በስርዓትና ጨዋነት በተሞላበት መንገድ ዝግጁ ሆኖ መቅረብ

፪. የክርክር አቀራረብ

- ራስንና የመከራከሪያ ርዕሱን ለአድማጮች ማስተዋወቅ
- በተዘጋጁት መሰረት በልበ ሙሉነትና በተረጋጋ ሁኔታ በቅደም ተከተል በቃል ማቅረብ
- ክርክሩን  አስፈላጊ በሆኑ አካላዊ እንቅስቃሴ ማጀብ
- ተቃዋሚዎች የሚያነሱትን ሀሳብ በትክክል በመመዝገብ ተገቢ ግብረ መልስ መስጠት
- ለክርክሩ የተመደበውን ጊዜ በአግባቡ መጠቀምና ማክበር
- ከመከራከሪያ ርዕስ ጉዳዩ ላለማፈንገጥ መሞከር
- በመጨረሻም አድማጭን ማመስገን

# ክፍል ሶስት፡- ማንበብ

## የአየር ንብረት ለውጥና ችግሮቹ




### ቅድመ ንባብ

**ተግባር**

፩. አየር ንብረትለውጥ እንዴት የሚከሰት ይመስላችኋል?

፪. ስዕሉንና  የምንባቡን ርዕስ በማየት ጽሑፉ ስለምን  እንደሚናገር ገምቱ

# የአየር ንብረት ለውጥና ችግሮቹ

የአየር ሁኔታ በየቀኑና በየሳምንቱ የተመዘገበን የሙቀት፣ የደመና፣ የዝናብ፣ የንፋስና የቅዝቃዜ ወዘተ. ሁኔታዎችን ለመግለጽ የምንጠቀምበት አገላለጽ ሲሆን የአየር ንብረት ደግሞ በአንድ አካባቢ ለረጅም ጊዜ የተመዘገበ የአየር ሙቀት፣ የዝናብ መጠን፣ የአየር እርጥበትና የንፋስ ፍጥነት ወዘተ. የመሳሰሉት አማካይ ውጤት ነው። የአየር ንብረት ለውጥእንዲሁለበርካታ አመታት የተመዘገበ የአየር ንብረት መቀየርን የሚያመለክት ነው።

የአየር ንብረት ለውጥ ለረዥም ዓመታት የተመዘገቡ አጠቃላይ የእርጥበት፣ የቅዝቃዜ፣ የሙቀት፣ የንፋስ አቅጣጫ የአየር ግፊት ወዘተ የመሳሰሉት ባህሪያት መለወጥ ነው። የአየር ንብረት ለውጥ በረጅም ጊዜ የሚከሰት ነው። ሰፊ መልክዓ ምድራዊ ሽፋንም ያለው ነው። በሌላ በኩል የአየር ጠባይ ለውጥ የምንለው በቀናትና በወራት የሚቀያየር የንፋስ፣ የዝናብ፣ የሙቀትና የቅዝቃዜ ለውጥ ሲሆን ለውጡም የሚገለጸው በአነስተኛ መልክዓ ምድር ላይ ነው።

ለአየር ንብረት ለውጥ ምክንያቶቹ በከባቢ አየር ውስጥ የሚገኙ ሙቀት አማቂ ጋዞች ከመጠን በላይ መከማቸታቸው ነው። የሙቀት አማቂ ጋዞችን ክምችት ያባባሰውና ለአየር ንብረት ለውጥ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረገው የሰው ልጅ የድንጋይ ከሰልን፣ የተፈጥሮ ነዳጅና ጋዝን በሰፊው በመጠቀሙ ምክንያት ካርቦን ዳይ ኦክሳይድ የተባለውን ጋዝ ወደ አየር በመልቀቅ ቀድሞ የነበረውን የአካባቢ አየር ተፈጥሯዊ ሁኔታ እንዲዛባ ምክንያት በመሆኑ ነው። ይሁን እንጂ የሰው ልጅ አሁን እየገጠመው ያለው ፈተና በሰው ሰራሽ ምክንያት በከባቢ አየር ውስጥ ባሉ የሙቀት አማቂ ጋዞች ለውጥ ሳቢያ እየተከሰተ ያለው አየር ንብረት ለውጥ ነው፡ ይህ ማለት ግን ተፈጥሮ በራሷ ለአየር ንብረት ለውጥ አስተዋጽኦ አታደርግም ማለት አይደለም።

በተጨማሪም እሳተ ገሞራና ተፈጥሯዊ የሰደድ እሳትም ለአየር ንብረት ለውጥ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። ለአየር ንብረት ለውጥ መንስኤ የሆኑ ሁነቶች በተከሰቱበት አካባቢ ብቻ ተወስነው የሚቀሩ ሳይሆን ድንበር ተሻጋሪዎችም ናቸው፡ በዚህ ምክንያት ለአየር ንብረት ለውጥ ብዙም ድርሻ የሌላቸው የታዳጊ ሀገራት ህዝቦች የበለጸጉ ሀገራት ሲያከማቹ በኖሩት የሙቀት አማቂ ጋዝ ጥርቅም ሳቢያ በሚከሰተው የአየር ንብረት ለውጥ ይበልጥ ተጎጂዎች ናቸው።

የአየር ንብረትና የአየር ሁኔታ ልዩነት ምንድን ነው?

የአየር ንብረት ለውጥ ምን ምን ችግሮች የሚያስከትል ይመስላችኋል?

የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትላቸው ዋና ዋና ችግሮች የግብርና መሬት መቀነስ፡- አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚተዳደረው በግብርና መሆኑ ይታወቃል፡ ፡ የህዝቧም ቁጥር በፍጥነት እየጨመረ ነው፡፡ የህዝብ ቁጥር መጨመር ደግሞ የምግብ አቅርቦትን የሚጠይቅ ነው፡፡ ስለዚህ የምግብ ፍላጎትን ለማሟላት ሲባል በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ አካባቢ ላይ ተጽዕኖ ማድረሱ የማይቀር ነው፡፡ በአካባቢ ላይ ጫና ሲደርስ ደግሞ የግብርናው ዘርፍ ምርታማነት ስለሚቀንስ ቁጥሩ እያደገ የሚገኘውን ህዝብ መመገብ አዳጋች ይሆናል፡፡

የመሬት መሸርሸር፡- የኢትዮጵያ መልክዓ ምድር በተፈጥሮው ተራራ፣ ኮረብታማ እንዲሁም ዝቅተኛ ቦታዎችና ሜዳዎች የሚበዙበት ነው፡፡ እንደሚታወቀው ታላላቅ ወንዞችና ጅረቶች መነሻቸው ከደጋማው አካባቢ ነው፡፡ የመሬቱ አቀማመጥ ከወንዞች የፍሰት አቅጣጫ ጋር ተዳምሮ ለአፈር መሸርሸር የተመቸ አድርጎታል፡፡ በዚህም ምክንያት አፈሯ እየታጠበ ወደ ጎረቤት ሀገር መጓጓዙ የተለመደ ሆኗል፡፡ ለአፈር መሸርሸር ዋና ዋናዎቹ ምክንያቶች ደግሞ ወራጅ ውሃ እና በደረቅ ወቅትና በሞቃታማው አካባቢ የሚከሰተው አውሎ ንፋስ ናቸው፡፡ እነዚህ ምክንያቶችም የአየር ንብረት ለውጥን ከማባባሳቸው በተጨማሪ ለድርቅ መከሰት፣ ለበረሃማነት መስፋፋት፣ ለግብርና ምርት መቀነስና ለመሳሰሉት ሁነቶች መሰረት ይሆናሉ፡፡

የሰውና የእንስሳት ጤና ችግር፡- የአየር ንብረት ለውጥ የሚፈጥረው የጤና ችግር በሰው ዘር ላይ ብቻ አይደለም፡፡ እንደ ሰው ልጅ ሁሉ የቤትና የዱር እንስሳትም የአየር ንብረት ለውጥ በሚፈጥረው የጤና ችግር ተጠቂዎች ናቸው፡፡ አሁን አሁን ደግሞ በቆላማውና በበረሃማው የሀገራችን ክፍል ተወስነው የነበሩ በሽታዎች ወደ ደጋማው አካባቢ በመሸጋገር ችግር በመፍጠር ላይ ይገኛሉ፡፡ ለአብነት ወባና የገንዲ በሽታ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

የገጸ ምድርና የከርሰ ምድር ውሃ መጠን መቀነስ፡- የውሃ መጠን ማነስና የጥራት መጓደል የሰብል ምርትንና ብዝሃ ሕይወትን ይጎዳል፡፡ ሀገራችንን ይበልጥ እየጎዳት የሚገኘው የኢኮኖሚ አቅማችን አናሳ በመሆኑና ትላልቅ ወንዞችን ጠልፎ የመጠጥ ውሃ ማቅረብ አለመቻሉ ነው፡፡ "የአባይን ልጅ ውሃ ጠማው" የሚለው አባባልም ከዚሁ የመነጨ ይመስላል፡፡ በአጠቃላይ የአየር ንብረት ለውጥ በሀገር ኢኮኖሚያዊ ግንባታ ላይ ጉልህ የሆነ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡ ማህበራዊ ችግሮችን በማባባስ አለመረጋጋት፣ ስደት፣ ረሃብ፣ ጦርነትና የመሳሰሉት ሁነቶች እንዲነግሱ ያደርጋል፡

(ከአብክመየአካ/የደንናየዱርእንስሳትጥበቃናልማትባለስልጣንየኮሙኒኬሽንጉዳዮችዳ ይሬክቶሬት፣ ለማስተማሪያነት ተሻሽሎ የተወሰደ)

# ድህረ ንባብ

## መልመጃ አንድ

ቀጥሎ የቀረቡት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክል ከሆኑ "እውነት"፣ ስህተት ከሆኑ ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልሱ።

፩. ተፈጥሮ በራሷ ለአየር ንብረት ለውጥ አስተዋጽኦ አታደርግም።

፪. እሳተ ገሞራ እና ተፈጥሯዊ የሰደድ እሳት በአየር ንብረት ለውጥ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራሉ።

፫. ለአየር ንብረት ለውጥ መንስኤ የሆኑ ሁነቶች በተከሰቱበት አካባቢ ብቻ ተወስነው የሚቀሩ ናቸው።

፬. የኢትዮጵያ መልክዓ ምድር በተፈጥሮው ተራራ፣ ኮረብታና ዝቅተኛ ቦታዎች የሚበዙበት ነው።

፭. ከኢትዮጵያ ምንም አይነት አፈር ወደ ጎረቤት ሀገራት አይሄድም።

፮. በአየር ንብረት ለውጥ ተጠቂው የሰው ዘር ብቻ አይደለም።

፯. የአየር ንብረት ለውጥ በአጭር ጊዜ የሚከሰት ነው።

## መልመጃ ሁለት

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልሱ።

፩. በአንቀጽ አንድ መሰረትበየቀኑና በየሳምንቱ የተመዘገበን የሙቀት፣ የደመና፣ የዝናብ፣ የንፋስና የቅዝቃዜ ወዘተ. ሁኔታዎችን ለመግለጽ የምንጠቀምበት አገላለጽ ምን ይባላል?

ሀ. የአየር ሁኔታ

ለ. የአየር ንብረት

ሐ. የአየር ፀባይ

መ. የአየር ለውጥ

፪. በጽሑፉ መሰረት ለአየር ንብረት ለውጥ በምክንያትነት የሚጠቀሰው ምንድን ነው?

ሀ. ሙቀት አማቂ ጋዞች ከመጠን በላይ መከማቸት

ለ. የድንጋይ ከሰልንና የተፈጥሮ ጋዝን በሰፊው መጠቀም

ሐ. ካርቦን ዳይ ኦክሳይድ የተባለውን ጋዝ ወደ አየር መልቀቅ

መ. ሁሉም መልስ ናቸው።

፫. የበለጸጉ ሀገራት ባከማቹት ሙቀት አማቂ ጋዝ ጥርቅም የተነሳ ለአየር ንብረት ለውጡ ብዙም ድርሻ የሌላቸው ታዳጊ ሀገራት ይበልጥ ተጎጂ የሆኑት ለምንድን ነው፡፡

ሀ. ደሃ ስለሆኑና ለመከላከል ፍላጎት ስለሌላቸው

ለ. የአየር ንብረት ለውጥ ድንበር ተሻጋሪ ስለሆነ

ሐ. የአየር ንብረት ለውጡ የፈጣሪ ቁጣ ስለሆነ

መ. አየር ንብረት ጊዜውን ጠብቆ መለወጡ ስለማይቀር

፬. እንደ ጽሑፉ ገለፃ ከሆነ እየተከሰተ ላለው የአፈር መሸርሸር አደጋ ዋና ምክንያቱ _______________ ነው፡፡

ሀ. አውሎ ነፋስ

ሐ. ወራጅ ውሃ

ለ. ለም አፈር

መ. ሀና ሐ

፭. በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት በቆላማውም ሆነ በደጋማው የሀገራችን ክፍል ችግር እየፈጠሩ ካሉ በሽታዎች ውስጥ የማይካተተው የትኛው ነው?

ሀ. ወባ

ሐ. ኤች አይቪ

ለ. ገንዲ

መ. ሁሉም

፮. ከሚከተሉት አንዱ ለበርካታ ዓመታት የተመዘገበን የአየር ንብረት መቀየር የሚመለከት ነው?

ሀ. የአየር ሁኔታ

ሐ. የአየር ንብረት

ለ. የአየር ንብረት ለውጥ

መ. የዝናብ መጠን

፯. የኢትዮጵያ ታላላቅ ወንዞችና ጅረቶች መነሻቸው ከየት ነው?

ሀ. ከደጋ | ለ. ከበረሀ | ሐ. ከቆላ | መ. ከአባይ

፰. “የአባይን ልጅ ውሀ ጠማው” ከሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር በፍቺተመሳሳይ የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. የተኳኙን ልጅ ውሀ ወሰደው

ሐ. የላጭን ልጅ ቅማል በላው

ለ. የባሮን ወንዝ አውሬ ጠጣው

መ. የድመትን ልጅ ውሻ በላው

፱. የዚህ ምንባብ አብይ መልዕክት ምንድን ነው?

ሀ. በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት በዓለም ላይ የተለያዩ ችግሮች እየተከሰቱ መሆኑን ማሳየት

ለ. ለአየር ንብረት ለውጥ ግንባር ቀደም ተዋናዮቹ በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት መሆናቸውን ማስረዳት

ሐ. የበለፀጉ ሀገራት በአየር ንብረት ለውጥ ላይ ምንም አይነት አስተዋጽኦ እንደማያደርጉ ማተት

መ. ውሀ ከደጋማው ቦታ በመነሳት ወደ በረሃማው ቦታ እንደሚፈስ መግለጽ

## መልመጃ ሶስት

**ከዚህ በታች የቀረበላችሁን ግጥም በጥሞና አንብቡና ለጥያቄዎቹ ከቀደመ እውቀታችሁ በመነሳት ምላሽ ስጡ።**

ይኸው እንደ ዋዛ
ይኸው እንደዋዛ!
ተራሮች ፈለሱ
ኮረብታዎች ተወሰዱ
ውሆች ተወሰዱ
ማነን? ብንላቸው
ፈጽመው ረሱን
በ'ኛ ተሰይመው
ዛሬ 'ኛን ስም ነሱን።

ይኸው እንደዋዛ!
ባለበት እንዲገኝ
መሬት መች ታመነ
መሀል የነበረው
ዳርቻችን ኾነ።

ይኸው እንደዋዛ!
አራሹ ሳይለግም
ሳይሳሳ ደመና
ህላዌን ድርቅ መታት
ዘር መውደቂያ አጣና።

(በዕውቀቱ ስዩም፣ 2001 ዓ.ም፣ ስብስብ ግጥሞች)

፩. ግጥሙ ባለስንት አርኬ ነው?

ሀ. ሁለት　　ሐ. ዘጠኝ

ለ. ሶስት　　መ. አስራ ስምንት

፪. በግጥሙ የመጀመሪያው አርኬ ላይ “ማነን? ብንላቸው ፈጽመው ረሱን” የተባሉት እነማን ናቸው?

ሀ. ተራሮች　　ሐ. ኮረብታዎች

ለ. ውሀዎች　　መ. ሁሉም

፫. በግጥሙ መሰረት መሬት ያልታመነው በምንድን ነው?

ሀ. እህል ባለመቀበል

ለ. ቤት መስርያ ባለመሆን

ሐ. ባለበት ባለመገኘት

መ. መዝናኛ ባለመሆን

፬. ከሚከተሉት አንዱ አማርኛ ቋንቋ ከግዕዝ የተዋሰው ቃል ነው።

ሀ. ህላዌ　　ሐ. ሳይሳሳ

ለ. አጣና　　መ. ዳርቻ

፭. በግጥሙ መሰረት ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ገበሬዎች እርሻቸውን እያረሱ ነው።

ለ. ሰማይ ዝናብ መስጠቱን አላቆመም።

ሐ. መሬት ባለበት እየቀጠለ አይደለም።

መ. የሰው ልጅ በርሃብና በችግር እየተመታ ነው።

## ክፍል አራት፡- መጻፍ

### ትዕዛዝ፡-

፩. በክፍል ሶስት ላይ የቀረበውን ስዕል ከዚህ በታች ከቀረበው ጋር በማነጻጸር ጥልቅ የሆነ ትንታኔ በጽሑፍ ስጡ።

፪. የጻፋችሁትን ጥልቅ ማብራሪያ እርስ በዕርስ በመቀያየር ተራረሙ።



## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### ዐውዳዊ ፍቺ

#### መልመጃ አንድ

ከዚህ በታች በሰንጠረዥ የቀረቡትን ቃላት ዐውዳዊ ፍቻቸውን መሰረት አድርጋችሁ በባዶ ቦታው ውስጥ በማስገባት አረፍተነገሩን አሟልታችሁ ጻፉ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዳጎስ | ወላፈን | ሳንካ | ሀገረ ሰብዓዊ |
| መሻሻል | አዘቦት | ቤተ ምርምር | ማዕረግ |

፩. ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚከበሩ ____________ ክብረ በዓላት መካከል የወላይታ ህዝብ የዘመን መለወጫ "ጊፋታ" አንዱ ነው፡፡

፪. የእሳቱ______________ ዳር ያሉትን ሰዎች ሁሉ ገረፋቸው፡፡

፫. የመስሪያ ቤቱ ኃላፊ ባለፈው ዓመት ላስመዘገቡት አመርቂ ውጤት ________ ያለ ሽልማት ተበረከተላቸው፡፡

፬. የአንዲት ሀገር ማሕበራዊ ኑሮ_____________የሚችለው ሕዝቡ በትምህርት የታነጸ ከሆነ ነው፡፡

፭. ኮቪድ 19 (ኮሮና ቫይረስ) ለሀገራችን ዕድገት _________ ከሆኑ ጉዳዮች አንዱ ነው፡፡

፮. በሣይንስና ቴክኖሎጂ ጥበብ የበለጸጉት ሀገሮች አሁን ከደረሱበት የዕድገት ደረጃ ላይ ሊደርሱ የቻሉት የ_________ ጥናታቸውን በማጠናከራቸው ነው፡፡

፯. ዘምዘም በበዓላት ቀን ይቅርና ለ __________ቀን የምታዘጋጀው ምግብ ጣት ያስቆረጥማል፡፡

፰. ወንጀለኞችን በቁጥጥር ስር ያዋለው ፖሊስ የ ___________ ዕድገት አገኘ፡፡

## መልመጃ ሁለት

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን በመምረጥ መልሱ፡፡

፩. ሰዎች ከደረሱበት ከፍተኛ ደረጃ ለመድረስ ከተፈለገ በወጣትነት ዕድሜ ሳሉ በስርዓትና በበጎ ምግባር --------------------ያስፈልጋል፡፡

ሀ. መታነጽ　　ሐ. መሰናዳት

ለ. መዘጋጀት　　መ. መጠበቅ

፪. ህፃኑ የፈለገው ነገር ስለተሟላለት በደስታ --------------------፡፡

ሀ. አማረ　　ለ. ቦረቀ　　ሐ. ዘለለ　　መ. ለ ና ሐ

፫. መብራት በመጥፋቱ የተነሳ ከተማውን --------------ውጦታል፡፡

ሀ. ብቸኝነት　　ሐ. ጽልመት

ለ. ድፍረት　　መ. አውሬ

፬. የሰራነው ስራ ጥሩ ስለነበር ነፍሳችን-------------አደረገች፡፡

ሀ. ሀዘን　　ለ. ሀሴት　　ሐ. ክፋት　　መ. ስብሰባ

፭. ሁልጊዜ አንድ ዓለማ ይኑርህ፣ ዓላማህ ግቡን እንዲመታ ደግሞ-------------ጥረት አድርግ፡፡

ሀ. ያልተመጣጠነ　　ሐ. ያላሰለሰ

ለ. ያልተደጋገመ　　መ. ያሰለሰለ

፮. የስራ ባልደረባዬ ----------------ስለሆነ ችግሬን ፊት ለፊት ከመንገር ይልቅ ወሬ ለአለቃ ማሳበቅ ይወዳል፡፡

ሀ. መሰሪ　　ለ. ቀና　　ሐ. መልካም　　መ. ጥሩ

፯. የራስን የአሰራር ዘዴ ከሌሎች የአሠራር ስልት ጋር---------------መቻል ራስን ለማስተካከል ቁልፍ መሳሪያ ነው፡፡

ሀ. ማነፃፀር　　ሐ. ማመሳከር

ለ. ማወዳደር　　መ. ሁሉም

## መልመጃ ሶስት

በ"ሀ" ስር የቀረቡትን ያልተለመዱ ቃላት በ"ለ" ስር ከቀረቡት ፍቺዎቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| ፩. ሞግዚት | ሀ. መንቀጥቀጥ |
| ፪. ገርበብ | ለ. መከልከል |
| ፫. ስርቅታ | ሐ. መባከን |
| ፬. ማሞናደል | መ. ማቃጠል |
| ፭. መክላት | ሠ. ተንከባካቢ |
| ፮. ቅራተኛ | ረ. ከፊት |
| ፯. መዋተት | ሰ. ከብት ጠባቂ |
| ፰. መፋጀት | ሸ. ማቀማጠል |
| | ቀ. ህቅታ |
| | በ. ማስወገድ |

# ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

## መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች ነጠላ ወይም ውስብስብ አርፍተ ነገር በማለት መልሱ፡፡

፩. በሪቴ የገዛችው ቀሚስ ያምራል፡፡

፪. የጀቦ እናት ከገበያ ሽንኩርት፣ቃሪያና ቲማቲም ገዙ፡፡

፫. ሰዓዳ የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪ ናት፡፡

፬. ብርጭቆውን የሰበረው ልጅ በእናቱ ተገረፈ፡፡

፭. ከወልቂጤ የመጣው ሰውዬ ትናንት ወደ ጨንቻ ተጓዘ፡፡

፮. እነ ጨበሶ አዳኙ ውሻ አላቸው፡፡

፯. ሐና ያዘጋጀችው ምግብ በጣም ይጣፍጣል፡፡

፰. በእውቀቱ ከሁሉም ተማሪዎች አንደኛ በመውጣት የትምህርት ቤቱን ዋንጫ ወሰደ፡፡

፱. ሰለሞን ባረጋ የአስር ሺህ ሜትር የሩጫ ውድድር አሸነፈ፡፡

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ክርክር አንድና ከዚያ በላይ በሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ተቃራኒ አስተሳሰብ ባላቸው ቡድኖች መካከል የሚካሄድ ሙግት፣ ፍትጊያና እሰጣገባ መሆኑን አይተናል፡፡ በመቀጠልም ያልተለመዱ ቃላት የሚባሉት በእለት ከዕለት የቋንቋ አጠቃቀማችን ውስጥ የማንጠቀማቸው አዳዲስ ቃላት እንደሆኑ ተመልክተናል፡፡

በመጨረሻም በውስጡ አንድ ግስ ብቻ የያዘ አረፍተነገር ነጠላ አረፍተ ነገር ሲባል ሁለትና ከዚያ በላይ ግሶችን ያካተተ አረፍተ ነገር ውስብስብ አረፍተነገር እንደሚባል ተምረናል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

ለሚከተሉት ያልተለመዱ ቃላት መዝገበቃላዊ ፍቺ ስጡ፡፡

፩. ጨመተ

፪. አዋይ

፫. እኩይ

፬. አክንባሎ

፭. በትር

፮. ወረንታ

፯. ጠማሪ

፰. ዐጸድ

# ምዕራፍ አስር

## ተውኔት

### የሚጠበቁ ውጤቶች፣

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ፡-

- የጽሑፉን ሀሳብ አዳምጣችሁ ትተነትናላችሁ፤
- ስለ ተውኔት ምንነት ብያኔ ትሰጣላችሁ፤
- የተውኔት አላባውያንን ትዘረዝራላችሁ፤
- በጽሑፍ ውስጥ የተለያዩ አያያዦችን ትጠቀማላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### ለሁሉም ጊዜ አለው!



## ቅድመ ማዳመጥ

### ተግባር

፩. "ለሁሉም ጊዜ አለው" በሚል ርዕስ በተጻፈ ተውኔት ምን ምን ርዕሰ ጉዳዮች የሚዳሰሱ ይመስላችኋል?

፪. ከአሁን በፊት በራድዮ ካዳመጣችሁት ወይም በቴሌቪዥን ከተመለከታችሁት ወዘተ. ተውኔት ገጸባህሪያት በመጥቀስ ለምን ማስታወስ እንደቻላችሁ ተናገሩ፡፡

፫. የሚከተለውን ስዕል አይታችሁ የተረዳችሁትን ነገር ግለፁ፡፡

## ድህረ ማዳመጥ

### መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በተውኔቱ መሰረት በቃል መልሱ፡፡

፩. ከተውኔቱ የተማራችሁት ምንድን ነው?

፪. መዓዛ በማትያስ የተናደደችው ለምንድን ነው?

፫. አበበች መዓዛን "ለሰው መድኃኒቱ ሰው ነው ስትላት"፣ "አጥፊውም እኮ ሰው ነው" ያለቻት መዓዛ ምን ለማለት ፈልጋ ነው?

፬. አበበች መዓዛን ይቅርታ መጠየቋ አግባብ ነው ብላችሁ ታምናላችሁ? እንዴት?

### መልመጃ ሁለት

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልሱ፡፡

፩. የዚህ ተውኔት መቼቱ የት ነው?

ሀ. ቤት ውስጥ ምሳ ሰዓት ላይ

ለ. መዝናኛ ቦታ እረፍት ሰዓት ላይ

ሐ. ትምህርት ቤት ግቢ ረፍት ሰዓት ላይ

መ. ትምህርት ቤት ግቢ ምሳ ሰዓት ላይ

፪. መዓዛ "ማስተዋል የጎደላቸው ሰዎች የሰውን ሕይወት ከመጉዳት አይመለሱም" ያለችው ምን ለማለት ፈልጋ ነው?

ሀ. ማየት የማይችሉ ሰዎች ሰውን ይጎዳሉ

ለ. ነገሮችን ማመዛዘን የማይችሉ ሰዎች፣ ለጓደኞቻቸው ጠንቅ ናቸው

ሐ. የማመዛዘን አቅም የሌላቸው ሰዎች፣ ሰውን ሊጎዱ አይችሉም

መ. የሰውን ህይወት ለመጉዳት ማስተዋል አስፈላጊ ነው

፫. አበበችና መዓዛ የስንተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው?

ሀ. የሰባተኛ

ለ. የአስረኛ

ሐ. የስድስተኛ

መ. የስምንተኛ

፬. መዓዛ አበበችን "ለሁሉም ጊዜ አለው" ሲባል አልሰማሽም ያለቻት ምን ልታስረዳት ፈልጋ ነው?

ሀ. እድሜያቸው ገና ለአቅመ ሔዋን አለመድረሱን

ለ. ያሉበት የትምህርት ደረጃ ስለፍቅር የሚያስቡበት አለመሆኑን

ሐ. ፍቅር ጊዜያቸውን ጠብቀው የሚደርሱበት መሆናቸውን

መ. ሁሉም

፭. አበበችና መዓዛን ግጭት ውስጥ ያስገባቸው ጉዳይ ምንድን ነው?

ሀ. ማትያስ ለመዓዛ የፃፈው የፍቅር ደብዳቤ

ለ. ማትያስ ለአበበች የፃፈው የፍቅር ደብዳቤ

ሐ. አበበች ለማትያስ የፃፈችው የፍቅር ደብዳቤ

መ. መዓዛ ለማትያስ የፃፈችው የፍቅር ደብዳቤ

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### መልመጃ አንድ

በቡድን ተወያይታችሁ ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡

፩. ተውኔት ምንድን ነው?

፪. ተውኔት ልቦለዳዊ ወይስ ኢ-ልቦለዳዊ ጽሑፍ ይመስላችኋል? እንዴት?

፫. የተውኔት አላባውያን  የሚባሉትን ዘርዝሩ፡፡

## መልመጃ ሁለት

**ከዚህ በታች የቀረበውን ቃለ ምልልስ ጥንድ ጥንድ ሁናችሁ በማጥናት ክፍል ውስጥ በቃላችሁ አቅርቡ።**

**ጋዜጠኛ:-** እንደምን አላችሁ ተማሪዎች? አሁን አንድ እንግዳ ስለምጋብዝላችሁ በጥሞና ተከታተሉ።

- እሽ እንግዳዬ በቅድሚያ ጥሪዬን አክብረው እዚህ ስለተገኙ ከልብ አመሰግናለሁ።

**ወ/ሪት ኦብሴ:-** እኔም ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ።

**ጋዜጠኛ:-** እስኪ በመጀመሪያ ራስዎን ያስተዋውቁ

ወ/ሪት ኦብሴ:- ኦብሴ ሞገስ እባላለሁ፤ የእውቀት ለብርሃን የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት የልዩ ፍላጎት ባለሙያ ነኝ።

**ጋዜጠኛ:-** እሺ ወ/ሪት ኦብሴ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ማለት ምን ማለት ነው?

**ወ/ሪት ኦብሴ:-** የልዩ ፍላጎት ትምህርት ማለት ከመደበኛ ትምህርታቸው በተለየ ሁኔታ ልዩ ትምህርት ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች የሚሰጥ ትምህርት ነው።

**ጋዜጠኛ:-** የልዩ ፍላጎት ትምህርት አሰጣጥ እንዴት ነው።

**ወ/ሪት ኦብሴ:-** የልዩ ፍላጎት ትምህርት ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች በልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህራን አማካኝነት የሚሰጥ የትምህርት አይነት ነው።

**ጋዜጠኛ:-** የልዩ ፍላጎት ትምህርት የሚያስፈልጋቸው ምን አይነት ተማሪዎች ናቸው?

**ወ/ሪት ኦብሴ:-** አይነ ስውራን፣ መስማት የተሳናቸው፣ የአዕምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው፣ የባህርይ ችግር ያለባቸው፣ የአካል ጉዳት ያለባቸው ወይም ደግሞ የተለየ ተሠጥኦ ያላቸው ተማሪዎች ወዘተ. ሊሆኑ ይችላሉ።

**ጋዜጠኛ:-** እሺ ወ/ሪት ኦብሴለሰጡን ማብራሪያ በጣም እናመሰግናለን። በመጨረሻም የሚሉት ነገር ካለ እድሉን ልስጥዎ!

**ወ/ሪት ኦብሴ:-** እሺ! ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ትንሽ ድጋፍ ከተደረገላቸው እንደማንኛውም ተማሪ ውጤታማ መሆን ይችላሉ። ስለዚህ እነዚህን ልጆች ፍቅር እየሰጠን ውጤታማ እንዲሆኑ ማድረግ የሁላችንም ሀላፊነት መሆኑን አውቀን

ለተግባራዊነቱ ልንተጋ ይገባል፡፡

**ጋዜጠኛ:-** እሺ ወ/ሪት ኦብሴ በጣም አመሰግናለሁ፡፡

**ወ/ሪት ኦብሴ:-** እኔም በጣም አመሰግናለሁ

## ክፍል ሶስት፡- ማንበብ



### ጠልፎ በኪሴ

### ቅድመ ንባብ

**ተግባር**

፩. "ጠልፎ በኪሴ" በሚል ርዕስ በተጻፈ ተውኔት ምን ርዕሰ ጉዳይ የሚነሳ ይመስላችኋል?

፪. በሲኒማ የታየውን ነገር ሁሉ በተግባር ለማዋል መሞከር አግባብ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? እንዴት?

፫. ከላይ ያለውን ስዕል አይታችሁ የተረዳችሁትን ነገር ግለፁ፡፡

## ጠልፎ በኪሴ

ስምንት ሰዓት አካባቢ ነው፤ ሰፊ ቤት ሰፊ ሳሎን ውስጥ የተለያዩ የቤት እቃዎች ይታያሉ፡፡ ወልደ ጨርቆስ በዝርግ ሰሀን ብርጭቆ ይዞ ይደረድራል፡፡ ገላግሌ እና ይስሀቅ ደግሞ ሶፋ ላይ ቁጭ ብለው ጠረጴዛ ላይ ካርታ በመደርደር ይጫወታሉ፡

በዛብህ ፈንጠር ብሎ ጋዜጣ እያነበበ ሲሆን ወንዳየሁ በበኩሉ በበዛብህ ተቃራኒ በኩል ቁጭ ብሎ የሙዚቃ ሽክላ እየደበደበ እየዘፈነ ነው። በር የተቆለፈባት ታፈሰች ደግሞ ክፈቱ እያለች በሩን በሀይል ትደበድባለች፡፡

**በዛብህ:-** ጥልፊያ አያስፈልግም ወይም አይረባም የምትል ይመስላል ገላግሌ!

**ወልደ ጨርቆስ:-** (ወልደ ጨርቆስ በዝርግ ሰሃን የታጠቡ ብርጭቆዎች ይዞ ገብቶ ይደረድራል) ምን ልታዘዝ ጌቶቼ?.... የለም? መልካም፣ በቃ ሄድኩላችሁ ተጫወቱ፡ (ይወጣል)

**ገላግሌ:-** አዎን-በዛብህ፡፡ የተሰራው ስራ በመሰረተ ሀሳቡ አይረባም ባይ ነኝ፡፡

**ይስሃቅ:-** በሃሳቡ መሰረትስ?

**በዛብህ:-** ተወው ይናገር፡፡ የሚለውን እንስማ፡፡ አዲስ ሀሳብ ከሆነ ማድመጥ ግዴታችን ነው፡፡

**ገላግሌ:-** ምን ይታወቃል? ስህተታችሁን ስታውቁት ትመለሱ ይሆናል፡፡

**በዛብህ:-** (ይግላል) ሀሳብህ ምንድን ነው?

**ይስሃቅ:-** ተንፍሰው - ይውጣልህ፡፡

**ገላግሌ:-** እግዜር አይወደውም ነው የምለው፡፡ ሌላ አይደለም፡፡

**በዛብህ:-** (በጩኸት) ማስረጃ ነው የሚያስፈልገው-ማስረጃ!

**ይስሃቅ:-** መጣባችሁ እንግዲህ! ጨዋታ ሲከር ክርክር ይሆናል፡፡

**ገላግሌ:-** የምን ማስረጃ ትፈልጋለህ? ያረመኔ ስራ ነው፡፡ ተምሬያለሁ የሚል የሰለጠነ ሰው ይህን አያደርግም፡፡

**በዛብህ:-** ደሞሳ? ቀጥል...

**ገላግሌ:-** ከደንደር በለስ አይቀሰምም፡፡ በግድ በጉልበት የተቋቋመ ጋብቻ ሲጸና፣ ደስታን ሊያስገኝ እንዴት ይችላል?

**ይስሃቅ:-** ለጽጌሬዳ እሾህ የላትም በለኛ!

**በዛብህ:-** (በንቀት) ገላግሌ ምስኪን ነህ፡፡ ያንተ ቢጤዎች ከዚህ ዓለም ተለይተዋል፡ ፡ የሰማይቤቱን ስትሰብኩ ዋናውን ነገር ረስታችሁታል!

**ገላግሌ:-** የአዲሱ ዘመን ጋብቻ ከድሮው ልዩ መሆኑን ማወቅ አለብህ፡፡ መለያው

ፍቅር ነው። ከመጋባት አስቀድሞ መግባባት ያስፈልጋል። ያለ ፍቅር ጋብቻ ደግሞ ሙት ነው።

**ይስሃቅ፡-** ላይጋቡ መፋቀርም በዝቷል- ያለመጠን በዝቷል በዘመናችን። አትርሳ፣ ገላግሌ!

**ገላግሌ፡-** ከቁም ነገር እየገባህ አትበጥብጥ። ነገሬ ካንተ አይደለም ካጫፋሪው ከበዛብህ ነው- አንድ ሰው አይቷት የማያውቃትን ልጅ በምን መሰረት አገባኋት ይላል? የጥልፊያ ጋብቻ ጋብቻ ነው ከተባለም ቂልነት ነው። እመኑኝ-ምን አለ በሉኝ- ኋላ ጸጸት ነው ትርፉ።

**በዛብህ፡-** (በማቃለል) የኋላ ኋላ... በወዲያኛው ዓለም ማለትህ ነው?

**ገላግሌ፡-** እንዴት አንድ የተማረች ልጅ፣ ያዲሱ ዘመን ወጣት፣ እንዴት በጥልፊያ...

**ይስሃቅ፡-** አዎ- የከንፈሯን ቀለም፣ የአምባሩን፣ የጉትቻውን፣ የጌጧን፣ የፈርጧን አይተናል። እንዲህ አርጎም መማር መሰልጠን የለም!

**ገላግሌ፡-** አታቋርጠኝ ብዬሃለሁ...መዋደዱማ፣ ፍቅሩማ ይቅር...አይኑን አይታው ከማታውቀው ሰው! እንዴት ደስ ብሏት ልትኖር ትችላለች? ብታውቀው ይሻላል፣ በዛብህ ቶሪ። ብስጭት ተላላፊ በሽታ ነው፣ ሚስትን ከያዘ ባሏን አይምርም።

**በዛብህ፡-** ደሞሳ?

**ገላግሌ፡-** (ይበርዳል) ሳውቀው ባልነግራችሁ፣ አብሬያችሁ እየሳቅሁ ገደል ስትገቡ ዝም ብዬ ባያችሁ፣ ይህ ጓደኝነት አይባልም። ልጅቱን ካመጣችሁበት መልሱ። ከደሙ ንጹህ ነኝ። እጄን ታጥቤአለሁ። (ይቀመጣል)

**ይስሃቅ፡-** እባክህ ተወኝ ወንድሜ...የፈሰሰ ውሃ አይታፈስም። እናትሽ ቢቆጡ ቢፈርጡ እንደምቧይ የፈሰሰ ውሃ ይታፈሳል ወይ?... (ወንዳየሁ የሙዚቃ ሸክላ ይዞ እየዘፈነ ይገባል)

**በዛብህ፡-**ቀጥል ገላግሌ! (ጋዜጣውን በሀይል ወርውሮ ይነሳና በመስኮት ውጭ ውጭ ያያል)

**ገላግሌ፡-** ያለኝን ወርውሬያለሁ፡-...እነ ይስሃቅ ሳቁ- ምናለ፣ ሳቁ (እዚህ ላይ በር ይመታል። ጸጥታ ይሰፍናል። በር ዳግመኛ ይመታል፤ ይተያያሉ።)

**ገላግሌ፡-** (በትካዜ ራሱን ይደፋል። ወንዳየሁ ሸክላውን እንደጨበጠ ቆሞ ይቀራል)

**ወንዳየሁ፡-** አሁን ደሞ አረጋ ይሆናል ቀልደኛው...

**የልጅቱ ድምጽ፡-** ክፈቱ ኂላ ልባርጉ!... (እፎይ ይላሉ፡፡ በዛብህ ግን ዘወር እንኳ አላለም)

**ይስሃቅ፡-** እሷው ኖራለች ያቺ ግስላ፡፡ ምኗ አስደንጋጯ ነች በሉ?

የልጅቱ ድምጽ፡- ክፈቱ ዛሬ!... (መዝጊያውን በጡጫ ትወርድበታለች)

**ይስሃቅ፡-** ልጅቱ አበደችና አረፈችው!...ምን ይጠበስ ነው? ብይ፣ አሻፈረኝ፡፡ ጠጪ፣ አሻፈረኝ፡፡ (ይስቃል) (መዝጊያውን ሲንኳኳ ያደነቁራቸዋል)

**በዛብህ፡-** (ትዕግስቱ አልቋል) ወንዳየሁ - ክፈትላት፡፡

**ወንዳየሁ፡-** (ያወላውላል) ይከፈትላት? (መልስ ስላልተሰጠው፣ሊከፍት ይሄዳል፡ ይስሀቅ ካርታውን ይሰበስባል፡፡ ልጂቱ ስትገባ የተቀመጡት ይነሳሉ፡፡ ገላግሌ አይነሣም፤ጠጉሯ ከመበታተኑም በላይ ቁጣዋና እልኳ ካረማመዷ ይታያል፡፡ ስትናገር ግምባሯን ኮስትራ ነው፡፡)

**ታፈሰች፡-** ...እስካሁን ቀልዳችኋል፣ይበቃል፡፡ በናንተ ቤት አባቷ ነጋድራስ ወርቅነህ ብሩ ባለጸጋ ነጋዴ ናቸውና አንድ ልጃቸውን አፍነን ብንደብቃት ብር ይከፍላሉ ነው፡፡ እንደዚህ ያለ ጀብዱ ሲሰራ በሲኒማ ታይቶልኛል! ቂሎች በሲኒማ የታየው ሁሉ እውነት ይመስላችኋል? (ይስሃቅና ወንዳየሁ ሳቃቸው ይመጣና አፋቸውን ያፍናሉ) ፖሊስ አሁን ሲይዛችሁ የሳቃችሁትን ያህል ታለቅሷታላችሁ፡፡

**በዛብህ፡-** ታዲያ ምን ይደረግ ነው?

**ታፈሰች፡-** (በንቀትና በጥላቻ ዓይነት ታያቸዋለች) አሁን ቀስ በሉና እቤቴ መልሱኝ፡ እኔን ደብቆ ካባባ ገንዘብ እበላለሁ ማለት ዘበት ነው፡፡ (በትዕቢት እጇን አጣምራ ትቆማለች)

**በዛብህ፡-** ንገራት፣ ወንዳየሁ፡፡ ለማኞች ወይንም አጭበርባሪዎች አይደለንም፤ገንዘብ አንፈልግም፡፡ ንገራት፡፡

**ወንዳየሁ፡-** ምን ብዬ ልንገራት? እኔ አይሆንልኝም፡፡ ገላግሌ ንገራት፣ በዕድሜም አንተ ትበልጣለህ፡፡ (ገላግሌ ሳይመልስ ይነሳና ወደ መኝታ ቤት ይገባል)

**በዛብህ፡-** ይስሃቅ፣ ንገራት፡፡

ይስሃቅ፡- እኔም ቃል ያጥረኛል፡፡... ሰማዩ ሰሌዳ፣ ውቅያኖሱ ቀለም ቢሆን እንኳ የዛሬን ቀን ታምራት ለመጻፊያ አይበቃም፡፡ ከታዘዝኩ ግን፣ ምን አደርጋለሁ?

(ሊደሰኩር ይታጠቃል) እምህህ ..ህ..ህህ...! ከሁሉ አስቀድሜ ልናገር የምፈልገው ነገር ጥልቀቱ ከባሕር ውቅያኖስ፣ ርቀቱ ከነፋስ፣ ምጥቀቱ ከራስ ዳሽን ተራራ የበለጠ መሆኑን ስገልጽልዎ በደስታ ነው፡፡

**ታፈሰች፡-** (በማመናጨቅ ታቋርጠዋለች) ፍሬ ነገሩን እባክህ ጃል፣ ሌላውን ለበኋላ አቆየው፡፡

**ይስሃቅ፡-** ፍሬ ነገሩን ካሉ ፍሬ ነገሩን እሺ፡፡ ... በዓሉ ሰርግ ነው፡፡ ከሰርገኞቹ ላስተዋውቅዎ ...(እያመለከተ) እኔ ይስሃቅ ነኝ፣ ያ ወጣቱ በዛብህ ቶሪ ነው፡፡ ይኸ ወንዳየሁ ነው፡፡ አንደኛው ሚዜ አረጋ ሲሆን ከምሳ በኋላ ጥቂት ማንቀላፋት ልማዱ ስለሆነ ተኝቷል፡፡

**ታፈሰች፡-** ሰክሯል መሰለኝ!

**ወንዳየሁ፡-** አልገባዎትም፡፡ እርስዎ፣ እሜቴ፣ ተጠልፈዋል ነው የምለው፡፡

**ይስሀቅ፡-** (እጅ ይነሳል) ይመኑኝ እሜቴ፣ የተጠለፉት ለተቀደሰው ጋብቻ የተገቡና የታጩ ስለሆነ ነው እንጂ ለሌላ አይደለም፡፡

**ወንዳየሁ፡-** የነጋድራስ ወርቅነህ ብሩ ልጅ መሆንዎን ያወቀ የለም፡፡

**ይስሃቅ፡-** (ደግሞ እጅ ይነሳል) እርስዎ እሜቴ ሙሽራይቱ ሲሆኑ እኛ ደግሞ ሚዜዎች ነን፡፡

**ታፈሰች፡-** (አትበገርም) እኔ እቸኩላለሁ ቀልዳችሁ ቅጥ አጣ ... ገና ሾላ ሚካኤል ሳንደርስ ነው የሚመሸው በኋላ፡፡

**ይስሃቅ፡-** ቢያምኑም ባያምኑም እቅጩ ይኸው ነው፡፡

**በዛብህ፡-** ሌላ ጥያቄ ከሌላት አስገቡና ቆልፉባት፡፡ (ይወጣል) (ቤቱ ጸጥ ይላል፡፡ ታፈሰች በድንጋጤ ዓይኗ ፍጥጥ ይላል፡፡ ይስሃቅና ወንዳየሁ እጅና እጇን ይዘው ሲወስዷት ልጅቷ ትታገላለች፣ ትጮሃለች)

(መንግስቱ ለማ፤ ጠልፎ በኪሴ፤1953፣26-33)

## ድህረ ንባብ

### መልመጃ አንድ፡

ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በተውኔቱ መሰረት ትክክል ከሆኑ "እውነት"

ስህተት ከሆኑ ደግሞ “ሀሰት” በማለት መልሱ።

፩. ገላግሌ የጠለፉ ጋብቻ አስፈላጊ እንደሆነ አያምንም።

፪. በተውኔቱ ከንፈር መቀባባት፣ አምባር፣ ጉትቻ እና የተለያዩ ጌጣጌጦች ማድረግ የመማር ምልክት እንደሆነ ተገልጿል።

፫. አንድ ሰው ጓደኛው ያልሆነ ስራ ሲሰራ እያየ ማለፍ ተገቢ አይደለም።

፬. የበዛብህና የገላግሌ ግጭት እያደገ ሂዶ እርስ በዕርስ ለመሰነዛዘር ዳርጓቸዋል።

፭. ተውኔቱ የተካሄደበት መቼት በውል አይታወቅም።

## መልመጃ ሁለት

በተውኔቱ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልሱ።

፩. ተውኔቱ የተካሄደበት መቼት የት ነው?

ሀ. የሰፊ ቤት ሳሎን ስምንት ሰዓት አካባቢ

ለ. የትምህርት ቤት ግቢ ስድስት ሰዓት አካባቢ

ሐ. የመዝናኛ ቦታ አራት ሰዓት አካባቢ

መ. የሰፊ ቤት ሳሎን ሁለት ሰዓት አካባቢ

፪. ጋዜጣ እያነበበ ፈንጠር ብሎ የተቀመጠው ገፀባህርይ ማን ነው?

ሀ. ገላግሌ ለ. በዛብህ ሐ. ይስሀቅ መ. ወንድዬ

፫. ታፈሰች በተባለችው ተዋናይ ላይ የተፈፀመው ድርጊት ምንድን ነው?

ሀ. ዘረፋ ለ. መደፈር ሐ. ጠለፋ መ. ንጥቂያ

፬. “በግድ፣ በጉልበት የተቋቋመ ጋብቻ ሊፀና፣ ደስታንም ሊያስገኝ አይችልም” ያለው ተዋናይ ማን ነው?

ሀ. በዛብህ ሐ. ወልደጨርቆስ

ለ. አራጋው መ. ገላግሌ

፭. ይስሃቅ “ለጽጌረዳ እሾህ የላትም በለኛ!” ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ. ተግባራችን ከንቱ ልፋት ነው

ለ. ጽጌረዳ እሾህ አልባ ናት

ሐ. ተግባራችን ፍሬያማ ነው

መ. እሾህና ጽጌረዳ ግንኙነት የላቸውም

## ማስታወሻ

### ተውኔት

ተዋንያን የሌሎችን ሰዎች ባህርይ ወርሰው ክዋኔን ከቋንቋ ጋር በማዋሀድ መድረክ ላይ የሚያቀርቡት የስነ ጽሁፍ ዘርፍ ነው፡፡

በተዋንያን ተጠንቶና በብዙ ባለሙያዎች ትብብር ተዘጋጅቶ በመድረክ ላይ ይታይ ዘንድ የተፃፈ ድርሰትም ነው፡፡

### የተውኔት ሙያዊ ቃላት

**ተዋንያን:-** ገፀባህርያትን ተላብሰው የሚጫወቱት የጥበብ ሰዎች ናቸው፡፡

**ቃለ ተውኔት፡-**በተዋንያን መካከል የሚደረግ የንግግር ቅብብሎሽ ወይም ምልልስ ነው፡፡

**ትዕይንት:-** የመጋረጃ መዘጋት የማያስፈልገው አንድ የተውኔት ንዑስ አሀድ የገቢር ክፋይ ነው፡፡

**ገቢር:-** የተውኔት አንድ አብይ ክፍል ወይም ምዕራፍ ነው፡፡

**መነባንብ /ንባበ አዕምሮ/:-** አንድ ተዋናይ ሌሎች ተዋንያን በሌሉበት ለብቻ የሚያደርገው ንግግር ነው፡፡

**የተውኔት አላባውያን:-** ልክ እንደ ልቦለድ ሁሉ ተውኔትም አይቀሬ የሆኑ አላባዊያን አሉት፡፡ እነዚህም፡- መድረክ (መቼት)፣ ጭብጥ፣ ተዋንያን (ገፀባህርይ)፣ ታሪክ፣ ትልም/ሴራ እና ቋንቋ ናቸው፡፡

### መልመጃ ሰስት

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

፩. ተዋንያን የሌሎችን ሰዎች ባህርይ ወርሰው ክዋኔን ከቋንቋ ጋር በማዋሀድ መድረክ ላይ የሚቀርብ የስነጽሁፍ ዘርፍ ምን ይባላል?

ሀ. ግጥም　　ሐ. ልቦለድ

ለ. ተውኔት　　መ. ስነቃል

፪. ከሚከተሉት አንዱ የተውኔት ባህርይ አይደለም፡፡

ሀ. መድረክ ላይ ሲቀርብ በግልጽ የሚታይ ነው

ለ. ገፀባህርያቱ ምናባዊ ሳይሆኑ ገሀዳዊ ናቸው

ሐ. በተለያዩ ባለሙያዎች ትብብር የሚዘጋጅ ነው

መ. ገፀባህርያቱ ገሀዳዊ ሳይሆኑ ምናባዊ ናቸው

፫. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የተውኔት ሙያዊ ቃል አይደለም፡፡

ሀ. ትዕይንት | ሐ. ስንኝ
ለ. ገቢር | መ. ቃለተውኔት

፬. ከተውኔት አላባውያን መካከል ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ጭብጥ | ሐ. ቋንቋ
ለ. ገፀባህርይ | መ. መልስ አልተሰጠም

## ክፍል አራት:- መጻፍ

### መልመጃ አንድ

፩. “ጠልፎ በኪሴ” የሚለውን ተውኔት ሀሳብ በመረዳት በሁለት አንቀጽ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

፪. አንድ የተውኔት ርዕስ መርጣችሁ አጭር ተውኔት በጽሁፍ አዘጋጁ፡፡

## ክፍል አምስት:- ቃላት

### ዘይቤያዊ ቃላት

**ማስታወሻ**

**ዘይቤ**

ዘይቤ የቋንቋ ለዛ ማለት ነው፡፡ ለአገላለፃችን ጥንካሬ በመስጠት የምናስተላልፈው መልዕክት ጎልቶ ወይም ግልጽ ሆኖ እንዲታይ ለማድረግ የምንጠቀምበት አገላለጽ ወይም የአነጋገር ስልት ነው፡፡ የዘይቤ አይነቶች ብዙ ናቸው፡፡ ዋና ዋናዎቹ ግን የሚከተሉት ናቸው፡፡

| | |
|---|---|
| ፩. አነፃፃሪ | ፪. ተለዋጭ ዘይቤ |
| ፫. ሰውኛ ዘይቤ | ፬. እንቶኔ ዘይቤ |
| ፩. አያዎ ዘይቤ | ፮. ምፀት ዘይቤ |
| ፮. ግነት ዘይቤ | |

## መልመጃ አንድ

በሚከተሉት አረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን የዘይቤ አይነቶች ፃፉ።

፩. የሰማይ ስባሪ የሚያክል ዳቦ ሰጠኝ።

፪. አጫውተኝ እንጅ ተራራው!

፫. ሕይወት ያለው በድን

፬. ብዕር አለቀሰ።

፩. እጁ በረዶ ሆነ።

፮. ሄለን እብድ ይመስል ጨርቋን ጣለች።

# ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

## ማስታወሻ

### መስተፃምር

**መስተፃምር** ቃላትን፣ ሀረጋትንና አረፍተ ነገሮችን በአንድ ላይ የሚያያይዝ ወይም የሚያጣምር አያያዥ ቃል ነው።

ምሳሌ፡- እና፣ ስለሆነም፣ ወይም፣ እንደ፣ እንዲሁም፣ ስለዚህ፣ እስከ፣ ሆኖም፣ ምክንያቱም፣ ወዲያውኑ፣ በኋላ፣ ቢሆንም ወዘተ. ናቸው።

እነዚህን አያያዥ ቃላት በአረፍተነገር ውስጥ እንደሚከተለው መጠቀም ይቻላል።

**ምሳሌ፡-** ቆሎ <u>እና</u> ክትፎ የምወዳቸው ምግቦች ናቸው።

አሽብር ሲያዩት ጨካኝ <u>ይመስላል</u>፤ ልቡ ግን ሩህሩህ ነው።

ቀኑ ፀሀያማ ነው፤ <u>ስለዚህ</u> እረፍት ማድረግ አለብኝ።

አባትህ ተመልሶ <u>እስኪሚመጣድረስ</u> እዚህ መጠበቅ አለብህ።

## መልመጃ አንድ

ከዚህ በታች በሰንጠረዥ ከቀረቡት አያያዥ ቃላት መካከል ተገቢ የሆኑትን በመምረጥ ከታች ያሉትን አረፍተ ነገሮች አሟልታችሁ ፃፉ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| እንዲሁ | ግን | አለበለዚያ |
| ስለሆነ | ነገር ግን | ወይም |
| ስለ | ቢሆንም | ይሁንእንጂ |

፩. ያሬድ የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪ ____________ ማጥናት አይወድም፡፡

፪. ጀማል ይመጣ____________አላወኩም፡፡

፫. ልጁ ታማኝ____________አምነዋለሁ፡፡

፬. ሀምዛ ብዙ አጥንቶ ነበር፤____________ፈተናውን አላለፈም፡፡

፭. የገና ጨዋታ ማየት ደስ ይለኛል፤ መጫወት____________አልችልም፡፡

፮. ማንበብ አለብህ____________ፈተናውን ልትወድቅ ትችላለህ፡፡

፯. መጽሐፉን መግዛት____________ከቤተመጻሕፍት መዋስ ትችላለህ፡፡

፰. ውጭው በጣም ____________ ሚቀዘቅዝ ጃኬት አመጣሁልህ፡፡

# ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ተዋንያን የሌሎችን ሰዎች ባህርይ ወርሰው ክዋኔን ከቋንቋ ጋር በማዋሀድ መድረክ ላይ የሚያቀርቡት የሥነጽሁፍ ዘርፍ ተውኔት ሲባል የተውኔት ሙያዊ ቃላት የሚባሉት ተዋንያን፣ ቃለተውኔት፣ ትዕይንት፣ ገቢር፣ መነባንብ እና ጎንታ መሆናቸውን አይተናል፡፡ የተውኔት ዓላባውያን የሚባሉት ደግሞ መቼት፣ ገፀባህርይ፣ ሴራ፣ ቋንቋ እና ጭብጥ እንደሆኑ ተመልክተናል፡፡

በሌላ በኩል ለአገላለፃችን ጥንካሬ በመስጠት የምናስተላልፈው መልዕክት ጎልቶ ወይም ግልጽ ሆኖ እንዲታይ ለማድረግ የምንጠቀምበት አባባል ወይም የአነጋገር ስልት ዘይቤ ሲባል አይነቶችም ተነፃፃሪ፣ ሰውኛ፣ ተለዋጭ፣ እንቶኔ፣ ምፀት፣ አያዎ እና ግነት ዘይቤ መሆናቸውን ተምረናል፡፡

በተጨማሪም ቃልን ከቃል፣ ሀረግን ከሀረግ፣ አረፍተነገርን ከአረፍተነገር ለማያያዝ የሚያገለግሉ አያያዥ ቃላት መስተፃምር እንደሚባሉ መረዳት ችለናል፡፡

# የክለሳ ጥያቄዎች

## መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን አያያዥ ቃላት ተጠቅማችሁ አረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

ሀ. እንደ

ለ. እስከ

ሐ. ሆኖም

መ. ምክንያቱም

ሠ. ወዲያውኑ

ረ. በኋላ

## መልመጃ ሁለት

በሚከተሉት አረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን የዘይቤ አይነቶች ጻፉ፡፡

ሀ. ፊቱ ተነቅሎ የተቀመጠ የአረም ቅጠል ይመስላል፡፡

ለ. ኢትዮጵያውያን እናት ሀገራቸውን አረንጓዴ ሻማ ለማልበስ ደፋ ቀና እያሉ ነው፡፡

ሐ. የጨረቃዋ ብርሃን ጤፍ ያስለቅማል፡፡

መ. ሕይወቱን እያቃጠለ ለሰው ልጆች የነፃነት ብርሃን የሚያሳይ የነፃነት ጧፍ ነው፡፡

# የቃላት ፍች

| ቃል | ፍች |
|---|---|
| ሙልሙል | ዳቦ፣ጢቢኛ፣ለከት |
| መዘላበድ | መቀባጠር፣ መቀላመድ |
| ሚዜ | የቅርብ ጓደኛ፣ በጋብቻ ጊዜ ምስጢር አዋቂ |
| ራሮት | ሀዘኔታ፣ ሀዘን |
| ቀቢጸተስፋ | ተስፋ መቁረጥ |
| ቀትር | እኩለቀን፣ የቀን ግማሽ፣ ተሲያት |
| ቃለ ተውኔት | በሰዎች መካከል የሚደረግ የፊት ለፊት ንግግር |
| ቆሌ | አድባር፣ አውልያ፣ውቃቢ፣ ጠባቂ |
| ቋንጣ | በቀጫጭኑ ተዘልዝሎ የደረቀ ስጋ |
| ቡሃ | ነጭ እከክ፣ለምጽ፣መላጣ |
| ቤተ መዘክር | ልዩ ልዩ ጥናታዊና ታሪካዊ ቅርሶች የሚገኙበት |
| ብራና | ከበግ (ፍየል)ቆዳ የሚሰራ እንደ ወረቀት የሚያገለግል |
| ነጋድራስ | የነጋዴዎች ግብር የሚሰበስብ የመንግስት ሹም |
| አማት | የሚስት(የባል) እናት ወይም አባት |
| አምባር | ከአልማዝ፣ ከወርቅ... የሚሰራ ክንድ ላይ የሚደረግ ጌጥ |
| አውታር | የድንኳን መወጠሪያ ገመድ ወይም የበገና፣ የክራር ጅማት |
| አዕላፍ | ብዙ፣ አያሌ |
| አጋፋሪ | አስተናጋጅ፣ አስተናባሪ |
| እደጥበብ | የእጅ ስራ ውጤት |
| ዋልጌ | በስራው ላይ የማይገኝ፣ ወስላታ |
| ዘረመል | ተወራራሽ ባህርይያትን የሚያስተላልፍ በማንኛውም ሕይወት ያለው ነገር ውስጥ የሚገኝ ኬሚካል |
| የታጨ | ቃል ያሰረ፣ ለማግባት የተስማማ |
| ደንደር | ኮሸሽላ፣ ሁለንተናው እሾህ የሆነ እንጨት |
| ጆሮ ደግፍ | አጣዳፊ ተላላፊ የመንጋጭላ እጢ (እብጠት) |
| ገመገም | እንደ ሰንሰለት የተያያዘ ተራራ |

| | |
|---|---|
| ገቢር | የተውኔት አብይ ክፍል |
| ገጽለገጽ | ፊት ለፊት |
| ጉትቻ | ከወርቅ (ብር) የሚሰራ የጆሮ ጌጥ |
| ጉፍታ | በራስ በጀርባ ላይ ጣል የሚደረግ ነጠላ (ልብስ) |
| ግብዓተ መሬት | ቀብር |
| ጎንታ | ገጸ ባሕሪያት ለራሳቸው የሚያደርጉት ንግግር |
| ጥልፊያ | በሃይል አስገድዶ መውሰድ፣መንጠቅ |
| ጥሩር | የወታደር የብረት ልብስ |
| ጥሪት | ቅርስ፣ ገንዘብ፣ ሀብት ንብረት |
| ፈታሂ | ፈራጅ፣ ፍርድ ሰጪ |
| ፍርደ ገምድል | አድሏዊ ፍርድ የሚሰጥ |

# ዋቢጽሑፎች


- ሕይወት እምሻው። 2010። ፍቅፋቂ ። አ.አ፤ፋር ኢስት አሳታሚ ድርጅት።
- መስፍን ሀ/ማርያም።1976። የቡና ቤት ሥዕሎችና ሌሎችም ወጎች። አ.አ፤የኢትዮጵያ መጻህፍት ድርጅት።
- መንግስቱ ለማ ።1953። የተውኔት ጉባዔ። አ.አ፤ ተራመድ ማተሚያ ቤት።
- ምህረት ሞገስ። አዲስ ዘመን፤ ጥር 25/ 2012።
- ምስራቅ ተረፈ። 2009። ጨው በረንዳ።ፋር ኢስት ማተሚያ ድርጅት።
- ሰለሞን ሀለፎም።1997። የድርሰት አጻጻፍ። አ.አ፤ ብራና ማተሚያ ድርጅት።
- ሲሣይ መንግስቴ።2006። ለባሕልና ቱሪዝም ኢንስቲቱት የፓናል ውይይት የቀረበጥናታዊ ጽሁፍ፤ያልታተመ።
- ሳህሉ አክሊሉ እና ፋንቱ ደምሴ። 1997። የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪመጽሀፍ አስረኛ ክፍል። አዲስ አበባ፤ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት።
- በዕውቀቱ ስዩም ። 2001። ስብስብ ግጥሞች። አ.አ፤ ፋርኢስት ትሬዲንግ።
- በድሉ ዋቅጅራ።2009። ያልተከፈለ ስለት። አ.አ፤ እሌኒ ማተሚያ ድርጅት።
- ባየ ይማም። 2002። አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው። አ.አ፤ አልፋ አታሚዎች።
- ታሪኩ ፋንታዬ። 2001። አማርኛ ሁሉ ለሁሉ። አ.አ፤ ዜድ.ኤ ማተሚያ ቤት
- አለም እሸቱ እና ግርማ አውግቸው። 1998። የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪ መጽሃፍ አስራ ሁለተኛ ክፍል። አዲስ አበባ፤ኩራዝአሳታሚ ድርጅት፡
- አምሳሉ አክሊሉ እና ዳኛቸው ወርቁ። 1993። የአማርኛ ፈሊጦች። አ.አ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት።
- አብክመ ፕላን ኮሚሽን። 2012 የስነ ህዝብና ልማት ቅንጅት ዳይሬክቶሬት፤ ያልታተመ።
- አብክመ ። የአካባቢ የደንና የዱር እንስሳት ጥበቃና ልማት ባለስልጣን የኮሚኒኬሽንጉዳዮች ዳይሬክቶሬት፤ ያልታተመ።
- አ.አ.ከ.አ. ት/ቢሮ። 2007። የህጻናት ጉልበት ብዝበዛና ህገ ወጥ ዝውውርን ለመከላከል የተዘጋጀ መጽሃፈ ዕድ፤ ያልታተመ።
- ዘሪሁን አስፋው ።1998። የስነጽሁፍ መሰረታውያን። አ.አ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።
- የሺጥላ መንግስቴ ።2004። የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪ መጽሀፍአስራ አንደኛ ክፍል። አዲስ አበባ፤ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት።

- የሻው ተሰማ ። 1996። ልሳነ ብዕር ከመ ልሳነ ሰብዕ። አ.አ ፣ብራና ማተሚያ ድርጅት።
- 1998። የተውኔት አጽናፍ መነጽር ።አ.አ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።
- ድንቄሳ ደሬሳ እና ጽጌ አበበ። 1999። የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪ መጽሀፍ አስራ አንደኛ ክፍል። አዲስ አበባ፣ ኩራዝአሳታሚ ድርጅት።
- ጌታሁን አማረ።1989። የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ። አ.አ ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።
- ጽጌሬዳ ጫንያለው ። አዲስ ዘመን፣ ነሀሴ 12 /2011።


# የአማርኛ የፊደል ገበታ

| ግዕዝ | ካዕብ | ሣልስ | ራብዕ | ኃምስ | ሳድስ | ሳብዕ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ጽ | ፆ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |
| ቨ | ቩ | ቪ | ቫ | ቬ | ቭ | ቮ |

# የኢትዮጵያ ቁጥሮች

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ | 1 | ፪ | 2 | ፫ | 3 | ፬ | 4 | ፭ | 5 | ፮ | 6 | ፯ | 7 | ፰ | 8 | ፱ | 9 | ፲ | 10 |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፲፩ | ፲፪ | ፲፫ | ፲፬ | ፲፭ | ፲፮ | ፲፯ | ፲፰ | ፲፱ | ፳ | 20 |
| ፳፩ | ፳፪ | ፳፫ | ፳፬ | ፳፭ | ፳፮ | ፳፯ | ፳፰ | ፳፱ | ፴ | 30 |
| ፴፩ | ፴፪ | ፴፫ | ፴፬ | ፴፭ | ፴፮ | ፴፯ | ፴፰ | ፴፱ | ፵ | 40 |
| ፵፩ | ፵፪ | ፵፫ | ፵፬ | ፵፭ | ፵፮ | ፵፯ | ፵፰ | ፵፱ | ፶ | 50 |
| ፶፩ | ፶፪ | ፶፫ | ፶፬ | ፶፭ | ፶፮ | ፶፯ | ፶፰ | ፶፱ | ፷ | 60 |
| ፷፩ | ፷፪ | ፷፫ | ፷፬ | ፷፭ | ፷፮ | ፷፯ | ፷፰ | ፷፱ | ፸ | 70 |
| ፸፩ | ፸፪ | ፸፫ | ፸፬ | ፸፭ | ፸፮ | ፸፯ | ፸፰ | ፸፱ | ፹ | 80 |
| ፹፩ | ፹፪ | ፹፫ | ፹፬ | ፹፭ | ፹፮ | ፹፯ | ፹፰ | ፹፱ | ፺ | 90 |
| ፺፩ | ፺፪ | ፺፫ | ፺፬ | ፺፭ | ፺፮ | ፺፯ | ፺፰ | ፺፱ | ፻ | 100 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፪፻ | 200 | ፫፻ | 300 | ፬፻ | 400 | ፭፻ | 500 | ፮፻ | 600 |
| ፯፻ | 700 | ፰፻ | 800 | ፱፻ | 900 | ፲፻ | 1000 | ፳፻ | 2000 |
| ፴፻ | 3000 | ፵፻ | 4000 | ፶፻ | 5000 | ፷፻ | 6000 | ፸፻ | 7000 |
| ፹፻ | 8000 | ፺፻ | 9000 | ፻፻ | 10000 | | | | |